من هو عيسى (عليه السلام)

(٣٠٣) أسئلة

# ክርስቶስ ማነው?
# 303 ወሳኝ ጥያቄዎች



الأمهرية

# ክርስቶስ ማነው?

# 303

# ወሳኝ ጥያቄዎች

አዘጋጅ፦-አህመዲን ጀበል

ታህሳስ 2001

አዲስ አበባ፤

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ

1. መቅድም..........3

2. መግቢያ..........8

3. ምዕራፍ አንድ፡- የኢየሱስ ማንነት ጉዳይ..........17

4. ምዕራፍ ሁለት፡- የኢየሱስ መወለድና የሚነሱ ጥያቄዎች..........51

5. ምዕራፍ ሦስት፡- እምላክ ሥጋ ለብሶ ሰው ሆኗልን?..........54

6. ምዕራፍ አራት፡- የኢየሱስ አስተምህሮ ምን ነበር?..........59

7. ምዕራፍ አምስት፡- ‹ሚስጢረ ሥላሴ› ሚስጥር..........66

8. ምዕራፍ ስድስት፡- ‹ለኃጢአታችን ሲል ተሰቀለ፤ዳንን›!..........77

9. ምዕራፍ ሰባ ፡- ኢየሱስ ማነው ብለው አመኑበት?..........92

10. ምዕራፍ ስምንት፡- ኢየሱስ ስለራሱ ምን እምነት ነበረው?..........98

11. ምዕራፍ ዘጠኝ፡- እዉን እነዚህ የአምላክ ባህሪያት ናቸውን?..........100

12. ምዕራፍ አስር፡- የመጽሐፍ ቅዱስ ሕልውና..........107

13. ማስተንተን ይበጃል!..........127

14. ምዕራፍ አስራ አንድ፡- ታዲያ ክርስቶስ ማነው?..........132

ዋቢ መጻሕፍት..........138

## መቅድም

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርኅሩኅ በጣም አዛኝ በሆኸነው ነው።**

ዛሬ ዓለማችን እንደ አንድ መንደር በተገናኘችበት ዘመን ማንኛውም ማህበረሰብ ከሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ተገንጥሎ ለብቻው መኖር አይችልም።ግሎባላይዜሽን(ሉላዊነት) በሸቀጥ ብቻ ሣይሆን በአስተሳሰብም ጭምር የእያንዳንዱን ቤት እያንኳኳ ነው። ‹‹የእኔ እገሌን እምነትም ሆነ አመለካከት መስማትም ማወቅም አልፈልግም፤የራሴን ለነርሱ አላካፍልም›› ብሎ መቀመጥ ፈፅሞ የማይታሠብበት ደረጃ ላይ ደርሠናል።አንድ ሰው የራሱን እምነት ለሌሎች መግለፅ ባይፈልግ እንኳ ሌሎች በሩን አንኳኩተው መምጣታቸው አይቀርም።ታዲያ ይህ ግለሰብ ያለው አማራጭ አንድም የመጡበትን ወገኖች በአግባቡ ማስተናገድ አሊያም በግልምጫና በቁጣ (ጩኸት) መሸኘት ነው።በአገራችን ያለውን ተጨባጭ ስንመለከት የየትኛውም ሃይማኖት ተከታይ የሌሎች ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ሰዎች ቀርበውት ስለሃይማኖታቸው ለማስረዳት ሲሞክሩ በቅንነት ከማዳመጥ ይልቅ ለስድብና ዱላ መጋበዙ ሲበዛ የተለመደ ነው።ምክንያቱ ደግሞ ሌላ ሣይሆን የሁሉም ሃይማኖት ተከታዮች ማለት ይቻላል ስለራሳቸው እምነትም ይሁን ስለሌሎች እምነት በቅጡ አለማወቃቸው ነው።ስለዚህ እነዚህ ወገኖች ረጋ ብለው የሁለቱን ሃይማኖቶች ልዩነት አስረድተው እነሱ የያዙትን እምነት ለምን እንደመረጡትና ከሌሎች የቀረበላቸውን ደግሞ ለምን እንደማይከተሉት ምክንያታዊ በሆነ መልኩ በማስረዳት ፈንታ አምባጓሮ ፈጥረው ሰዎቹን ከአጠገባቸው ማራቅን ይመርጣሉ።ይህ ዓይነቱ አካሄድ አሁን ባለንበት ተጨባጭ ምን ያህል ያስኬደናል የሚለው ግን አጠያያቂ ነው።

ዛሬ የተለያዩ የመረጃ ምንጮች ሳንወድ በግድ በራችንን እንኳ ማንኳኳት ሳያሻቸው ጓዳችን ድረስ ዘልቀው መግባት እየቻሉ ነው። በሌላው ዓለም

ያሉት እንቅስቃሴዎች አገር ላይ ባለው ተጨባጭ ላይ የራሣቸው የሆነ አሉታዊም ይሁን አዎንታዊ ተፅዕኖ ማሣደራቸው የማይቀር ነው። ለምሣሌ በአሁኑ ወቅት  የሁሉንም ሃይማኖት ተከታዮች እንቅስቃሴን ዘልቀን ብንመለከት የተለያዩ ሃይማኖታዊ መረጃዎችን መጀመሪያ ከተዘጋጁባቸው ቋንቋዎች ወደ አገርኛ ቋንቋ በመመለስ የተከታዮቻቸውን እምነት ለማጠናከርና ሌሎችን ወደራሳቸው እምነት ለመሳብ የተለያዩ ሙከራዎችን ሲያደርጉ እናገኛለን።ስለዚህ ወደድንም ጠላንም የሌላውን ዓለም ተፅዕኖ መቀበላችን የግድ ነው።ይህን ስንል ደግሞ ከሌላው የሚመጣውን ነገር ሁሉ አግበስብሰን እንቀበል ማለት አይደለም።አነርሱም እንደኛው ሰዎች እንደመሆናቸው መጠን ጠንካራና ደካማ ጎን ይኖቸዋልና ጠንካራ ተሞክሮ ዎቻቸውን በመውሰድ ደካማውን መተው እንችላለን። ሀተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ውስጥ ከምናገኛቸው ጥሩ ተሞክሮዎች ውስጥ የተለያዩ የሃይማኖት አባቶችና ምሁራንን በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ ሠላማዊ በሆነ መልኩ ስለ ሃይማኖታቸው ገለፃ የሚሰጡበትንና ከህብረተሰቡ የሚቀርብላቸውን ጥያቄዎች በአግባቡ የሚመልሡባቸውን መድረኮችን ማመቻቸት ነው።ለዚህ ዓይነቱ ተሞክሮ አገራችን ባዕድ ብትሆንም የሁሉም ሃይማኖት አባቶች ዘንድ ቅንነቱ ካለ መድረኩን ማመቻቸት ቀላል ነው።ይህ ደግሞ የአገራችንን የሃይማኖት መቻቻል ተምሣሌትነት ይበልጥ ያጠናክረዋል እንጂ አያጠፋውም።

ዛሬ በአገራችን ስላለው የሃይማኖት መቻቻል ብዙ ይነገራል።ነገር ግን እስካሁን ያለው የሃይማኖት መቻቻል በምን ላይ የተመሠረተ ነው? ብሎ የሚጠይቅ ወገን ብዙም የለም። የአገራችንን የሃይማኖት መቻቻል መሠረት ካየነው በአስቂኝ ነገሮች ላይ የተገነባ ነው። ለምሣሌ ሁለት ፍፁም ተቃራኒ የሆኑ ሃይማኖቶች እንከተላለን የሚሉ ወገኖች ‹‹እኛም እናንተም ልክ ነን!

እናንተ አላህ ትላላችሁ! እኛ ደግሞ እግዚአብሔር እንላለን! ያው ነው እኮ! ቢላዋ ብቻ ነው የሚለየን! አንድነን!›› ...ወዘተ የሚሉ የሃይማኖት አባቶች በማይቀበሏቸው አባባሎች ላይ የተመሠተ ነው፡፡ በእንዲህ ዓይነቱ መሠረት ላይ የተገነባ መቻቻል አንደኛው ወገን ትክክለኛውን ሃይማኖቱን ልወቅና ልከተል ብሎ የተነሣ ዕለት ብትንትኑ ይወጣል፡፡ስለዚህ አንድነታችን ፣አብሮነታችንና መቻቻላችን ለሌላው ዓለም ተምሳሌት ሆኖ ይቀጥል ዘንድ መቻቻላችንን በጥሩ መሠረት ላይ መገንባት ግድ ይለናል፡፡ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ የሁሉም ሃይማኖት ተከታዮች የራሳቸውንና የተቃራኒ ዎቻቸውን ሃይማኖት በአግባቡ ሲያውቁና ሲረዱ ብቻ ነው እንጂ ‹‹አንተም የራስህን ደብቅ! እኔም የኔን በልቤ ልያዝ! በዚህ ጉዳይ እኔም አንተም ምንም ነገር ባናነሣ ይሻላል!›› ተከድኖ ይብሰል! ዓይነት ከሆነ ከዕለታት አንድ ቀን ይገነፍልና ወደ አላስፈላጊ አቅጣጫ ያመራል፡፡ ይህ ደግሞ ለማንም አይበጅም፡፡ስለዚህ ተቀራርቦ መወያየትና መነጋገር የበለጠ ያቀራርባል እንጂ አያራርቅም፡፡አጉል በአትንኩኝ ባይነት ተኮፍሶ መቀመጥ ለማንም አያዋጣም፡፡

በዚህ ረገድ በአሁኑ ሰዓት በአንዳንድ የሃይማኖት ተከታዮች መካከል የምናየው ሠላማዊ የሆነ ሃይማኖታዊ ውይይት (ክርክር) ለኛ ጥሩ ተምሣሌት ሊሆነን ይችላል ብለን እገምታለን፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ሠላማዊ የሆነ ውይይት እንደድፍረትና የሰውን ሃይማኖት እንደመንካት አድርገው የሚቆጥሩ አንዳንድ ወገኖችም አይጠፉም፡፡እነዚህ ወገኖች የያዙት አቋም አንድም የሃይማ ኖታቸውን መመሪያ በጥልቀት ካለማወቅ አሊያም የሚቀርቡላቸውን ጥቂዎች ‹በአግባቡ መመለስ አንችልምና ሰው ፊት እንዋረዳለን!› ከሚል ከንቱ ሥጋት የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡ለነዚህ ወገኖቻችን የምንላቸው ነገር ቢኖር የሃይማኖታችሁ መመሪያ(መጽሐፍ) በዚህ ጉዳይ ላይ ምን እንደሚል

በአግባቡ እንድታዩት እንድትፈትሹትና ራሳችሁን ጥሩ ተወያይ አድርጋችሁ ለማቅረብ እንድትሞክሩ ነው።አንዳንዶች ደግሞ የራሳቸውን ድክመት ለመሸፋፈን ሲሉ ለተራው ሰው ሃይማኖቱ እንደተነካና እምነቱ እንደተዘለፈ አድርገው በማቅረብ ሆን ብለው ህዝቡን ለዱላና ለአላስፈላጊ ግጭት እንዲጋለዝ የማድረግ ሥራ ሲሰሩ ይታያል:: ይህ ዓይነቱ ድርጊት በፈጣሪም በፍጡርም ዘንድ ያስወቅሳልና ሁላችንም እናስብበት።

ይህ 'ክርስቶስ ማነው?' የሚለው የወንድም አህመዲን ጀበል መጽሐፍ ብዙዎችን ሰውይይት የሚጋብዝና እጅግ በርካታ መልስ የሚሹ ጥያቄዎችን የያዘ ድንቅ መጽሐፍ በመሆኑ ማንኛውም በክርስቶስ በትክክል ማመን እፈልጋለሁ፤ በክርስቶስ ዙሪያ ያለኝ አቋም እውነታን ያዘለ፤ መጽሐፍ ቅዱስን ያገናዘበ ነው ወይስ ልማዳዊና በውርስ የተገኘ ነው? ብሎ ራሱን ከስሜታዊነትና ከወገንተኝነት በራቀ መልኩ መፈተሽ የሚፈልግ ሰው ሁሉ ሊያነበውና ራሱን ሊጠይቅበት የሚገባ መጽሐፍ ነው።አዘጋጁ ከዚህ ቀደም ሌሎች በርካታ ሥራዎችን በመሥራት የብዙዎችን ሕይወት ለውጧል።ከሰራቸው ሥራዎች ውስጥ ለአብነት ያህል ‹‹የሴቶች መብትና እኩልነት በኢስላምና በክርስትና እምነት›› በሚል ርዕስ ያቀረበው ብርቅዬ መጽሐፍ ይጠቀሣል።

ይህን ‹‹ክርስቶስ ማን ነው? 303 ወሳኝ ጥያቄዎች›› የሚለውን መጽሐፍ ከግልበኝነትና ከጭፍን ወገንተኝነት ርቆ የቀድሞ መነጽሩን አውልቆ በባዶ ዓይኑ የሚያነብ ማንኛውም ክርስቲያን (ከተራው ክርስቲያን እስከ ሊቃውንት ድረስ ማለት እችላለሁ) በእርግጠኝነት መጀመሪያ የሚያውቀው ክርስቶስና ከንባቡ በኋላ የሚያገኘው ክርስቶስ ፍፁም የተለያዩ ሆነው እንደሚያገኛቸው ቅንጣት ያህል አልጠራጠርም።ይህ ዓይነቱ መጠይቃዊ

አቀራረብ ለማንኛውም ተራ አንባቢ እንኳ ሳይቀር ጉዳዩን በቀላሉ እንዲረዳውና እንዲያውቀው ስለሚያደርግ በዘርፉ ከተሠሩ ሥራዎች ውስጥ እጅግ የተሻለው እንደሚሆን እገምታለሁ። በመጨረሻም አላህ(ሱ.ወ) የመራውን የሚያሳስተው፤እርሱ ያጠመመውን ደግሞ የሚያቃናው የለምና እርሱ በቸርነቱ ሁላችንንም ትክክለኛውን መንገድ ይምራን እያልኩ ለሁላችንም መልካም ንባብን እመኛለሁ።

ባህሩ ዑመር

## መግቢያ

የክርስቶስ ጉዳይ የሙስሊሞች እና የክርስቲያኖች እንዲሁም በተለያዩ የክርስትና ቡድኖች መካካል የመለያየታቸው አንዱ አብይ ምክንያት ነው፡፡ ሙስሊሞች ኢየሱስ ነቢይ መሆኑንና በተዓምር ከማርያም ያለ አባት መወለዱን ያምናሉ፡፡ቁርአንም ሃያ አምስት(25) ጊዜ ስለ ኢየሱስ(ኢሳ) ማንነት ጠቅሷል፡፡ከታላላቅ ነቢያት አንዱ መሆኑን አስተምሯል፡፡(ለምሳሌ፡- ሱረቱ ኒሳእ 4፡171-173)፤በሥላሴ ማመን ክህደት መሆኑን(ቁርአን ሱረቱል 5፡73-75)

እንዲሁም ‹አዛኙ አምላክ(አል-ራህማን) ልጅ ወለደ፤ኢየሱስ የአምላክ ልጅ ነው› መባሉን በጽኑ ሲቃወም ‹‹አል-ራሕማንም ልጅን ያዘ (ወለደ) አሉ፤ ከባድ መጥፎን ነገር በእርግጥ አመጣችሁ፤ከርሱ (ከንግግራቸው) ሰማያት ሊቀደዱ፤ ምድርም ልትሰነጠቅ፤ጋራዎችም ተንደው ሊወድቁ ይቃረባሉ፡፡ ለአል-ራሕማን ልጅ አለው ስላሉ፡፡ለአል-ራሕማን ልጅን መያዝ አይገባውም፡፡ በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ (በትንሣኤ ቀን) ለአል-ራሕማን ባሪያ ኾነው የሚመጡ እንጂ ሌላ አይደሉም፡፡››(ሱረቱል መርየም 19፡88-93)

ቁርአን ከኢስላም ውጭ ሌላ ሃይማኖትን የሚከሉትን ይተቻል፡፡ አቋማቸውን እንዲፈትሹ ጥሪ ያደርጋል፡፡ጥያቄዎችን ያቀርብላቸዋል፡፡ ያላቸውን ‹ማስረጃ› እንዲያቀርቡ በመጠየቅ ለውይይት ይጋብዛቸዋል፡፡ ያብራራል፡፡ለአብነት በአንድ ሥፍራ ካብራራ በኋላ እኛም ከዚህ ትምህርት እንድንቀስም ስለማብራራቱ እንዲህም ሲል ይገልጻል፡-‹‹እንዴት እንደም ናብራራ ተመልከት፤ከዚያም (ከእውነት) እንዴት እንደ ሚመለሱ ተመልከት ፡፡››(ቁርአን ሱረቱል 5፡73-75)

ክርስቲያኖች የመርየምን(ማርያምን) ልጅ አል-መሲህን(ክርስቶስን) አምላክ አድርገው መያዛቸውን ሲተች ‹‹የመርየምን ልጅ አል-መሲሕንም ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ፡፡ከሚያጋሩት ሁሉ የጠራ ነው፡፡የአላህን ብርሃን

በአፎቻቸው ለማጥፋት ይፈልጋሉ፤አላህም ከሓዲዎች ቢጠሉም እንኳን ብርሃኑን መሙላትን እንጂ ሌላን አይሻም።እርሱ ያ አጋሪዎቹ ቢጠሉም መልክተኛውን (ሙሐመድን) በቅን መንገድና በእውነተኛ ሃይማኖት ላይ ከሃይማኖት ሁሉ በላይ ይፋ ያደርገው ዘንድ የላከው ነው።››(ቁርአን ሱረቱ አት-ተውባ 9:30-32)

ኢስላም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለው አቋም ይህ ነው።አንዳንዶች ክርስቶስን የራሳቸው ብቻ አድርገው በመቁጠር ‹እናንተ ሙስሊሞች ስለ ክርስቶስ ምን አገባችሁ?››፤‹‹ክርስቶስን ‹ሰው ነው› ከማለት የበለጠ ምን ስድብ አለ?›› ይላሉ።ይህ አባባል ‹‹ክርስቲያን ሆኑ›› እንደ ማለት ነው። ይህን እምነታችንን ቀየርን ማለት ክርስቲያን ሆንን ማለት ነው። ሌሎቹ ደግሞ በየጎዳናውና ቤት ለቤት በመሄድ ‹ጌታን ተቀበል› በማለት ጠለቅ ያለ እውቀት የሌለውን ሙስሊሙን ያዋክቡታል። ሌሎች ደግሞ ‹ኢየሱስ ጌታ ነው!› በማለት በየመደብሮቻቸው ሲለጥፉና ሌሎቹ በየታክሲውና የሕዝብ መጓጓዣዎች በመለጠፍና መዝሙር በመክፈት ‹ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ያላመነ ያልተጠመቀ አይድንም።ይፈረድበታል› እና መሰል አቋሞቻቸውን ‹ልንነግራችሁ ይገባል› ይሉናል።አንዳንዶች መጽሐፍ በመጻፍ የነርሱን እምነት ያልተቀበለ ዋጋ እንደሌለው ይነግሩናል።ለምሳሌ አንድ የክርስቲያን ጸሐፊ ለሙስሊሞች እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡- «የማርያም ልጅ የመሢሕ ክርስቶስ መውረድ መወለዱንና አዳኝነቱን ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ እኩልነቱን አምናችሁ እስካልተቀበላችሁ ድረስ ዋጋ የላችሁም፤«እነሆ የእግዚአብሔር በግ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ»፤«ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ ከርሱ ጋራ የለም፤በወልድ የሚያምን አብም ደግሞ ከርሱ ጋራ ነው»»[1]

---

[1] መምህር ኪዳነ ማርያም ጌታሁን(ለሸህ አህመድ ዲዳት የተሰጠ መልስ)፤ክርስቶስ በኢስላም (በቁርዓን)፤ ክርስቶስን ከቁርዓን ጋር ምን አገናኘው?፤ በ1999 ዓ.ም. ለሁለተኛ ጊዜ ብርሃንና ሠላም ማተሚያ፤ገጽ 22

ኢስላም ‹ኢየሱስን ሰው ነው፤ፍጡር ነው።› በማለቱ እንዲህም ሲሉ ይወቅሳሉ፦«ፍጡርና ፈጣሪን ለይታችሁ ባለማወቃችሁ››[2] እንዲሁም ‹‹ክርስቶስ ትንቢት ተነገሮለት ሱባኤ ተቆጥሮለት የመጣ፣ አዳምና ልጆቹ ሲጠብቁት የኖረ መድኃኒት መሆኑን አምኖ ያልተቀበለ ሁሉ አሁንም አልዳነም››[3]

እንዲሁም ሙስሊሞችን ወደ ክርስትና ማስገባትን ዓላማው አድርጎ ‹ዓላማዬ ትውልዱን ለክርስቶስ ማዘጋጀትና ሙስሊሞችን በወንጌል መድረስ ነው› በሚል መፈክር የሚንቀሳቀሰው ኤልሻዳይ መጽሔት ‹‹መስጊዶች የወንጌል መሰብሰቢያ፣ኢማሞችና ሼኮች ሁሉ በድፍረት ወንጌል ሰባኪዎች አገልጋዮች ይሆናሉ።መኪናዎች፣ጎዳናዎች፣ካፍቴሪያዎችና ሻይ ቤቶች የወንጌልና የእግዚአብሔርን ስም ይጠራሉ፤››[4] ሲል ጽፏል።መሰመር ሰለሞን የተባሉ ጸሐፊ ደግሞ «እውነትን በመሸፋፈን መግለጥ አይቻልም።ምንም ነገር ሳይደበቅ ግልጽ ዉይይት መካሄድ ይኖርበታል።ትክክለኛ ግንዛቤ ሊኖር የሚችለው ይህ ሲሆን ብቻ ነው። ሐቅን ሁሉ በተከፈተ አእምሮ ማስተዋል እጅግ አስፈላጊ ነው።››[5] ይሉናል።ሌላኛው ጸሐፊ ደግሞ «ሃይማኖት በማስረጃ እንጂ በኃይልና በጉልበት የሚስፋፋበት ግዛት አይደለም፤በማስረጃ ያልተደገፈ እምቢታ ከባዶ ቤት አይሻልም፤»[6] ይላሉ።

አምላካችን አላህ(ሱ.ወ) የርሱን ብቸኛ አምላክነት ያልተቀበሉ ወገኖችን «ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን? እውነተኞች እንደኾናችሁ ማስረጃችሁን አምጡ፤ በላቸው።» (ቁርአን ሱረቱ አል-ነምል:64) ሲል ጥሪ ያደርጋል።«አለን»

---

[2]ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ፣ገጽ 17
[3] መምህር ኪዳነ ማርያም ጌታሁን፤ገጽ 21
[4] ገዛኢ ዮሐንስ፣ኤልሻዳይ/ያህዌህንሲ/ መጽሔት፣ግንቦት 1999፣ገጽ 20
[5] መስመር ሰለሞን፣ይድረስ ለሙስሊም ወገኖቼ፣ ገጽ V|||
[6] መምህር ኪዳነ ማርያም ጌታሁን፤

የሚሉትን ማስረጃ ሲያቀርቡ ዉይይትና ክርክር ይደረጋል።በመወያየትና በመከራከር መተማመን ያለ ነው።እንዲያውም ክርክር የነቢያት ፈለግ ነው። በቁርአን የነቢዩ ኑሕን(ኖሕ)(ዐ.ሰ) መከራከርን አስመልክቶ ሲነግረን «ኑሕ ሆይ! በእርግጥ ተከራከርከን እኛን መከራከርህንም አበዛኸው...አሉ።» (ሱረቱል ሁድ፡32) ክርክሩ በመልካም ጠባይ ይሆን ዘንድ ቁርአን «የመጽሐፉን ባለ ቤቶችንም በዚያች እርሷ መልካም በኾነችው ክርክር እንጂ አትከራከሩ፤»(አል-አንከቡት፡ 46)

ስለሆነም በቁርአን መርህ መሠረት ለሙስሊሙ ከሚያቀርቡት ‹ጌታን ተቀበል› እና መሰል ግብዣዎች እንዲሁም ‹እመኑበት› የሚሉንን መጽሐፎቻቸውን በማንበብና በማስተንተን ‹‹ቤተክርስቲያኒቱም ሆነች መጽሐፉ ምን ያህል ተአማኒነት አላቸው?›› ብሎ መጠየቅ ያለና የሚጠበቅ ነው።ያቀረቡት ማስረጃ ለምን ሊያሳምነን እንዳልቻለ በመልካም ቋንቋ ማስረዳት ደግሞ የኛ ፈንታ ይሆናል።እኛም በተራችን በክርስትና እምነት ላይ ያሉንን ጥያቄዎችን የማንሳትና እምነቱን እንድንቀበል የጋበዙን ወገኖች በእምነታቸው ላይ እንዲያስቡበት የበኩሌን ለማለት ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ችያለሁ።በየገጠሩ ሙስሊሙን ‹ጌታን ተቀበል› በማለት የሚያስቸግሩትን ሚሽነሪዎችም በማውቀውና ባነበብኩት ያክል አንድ ልላቸው ይኸው እንካችሁ ብያለሁ።የጥያቄዎቹ አቀራረብ መንደርደሪያ በማብዛት ከማሰልቸት በቀጥታ ሳይንዛዙ ወደ ነጥቦቹ መሄድ ያስፈልጋል ብዬ በማመኔ አሁን ባለበት አኳኋን እንዲሆን አድርጌያለሁ።

ሁሉም ወገን የራሱን እምነት ትክክለኛነት ያጸድቃል። የሌላውን ክህደትም እንዲሁ።ምሳሌ የሚሆነን አላህ በቁርአን ውስጥ የገለጸልን የአይሁዶች፣ የክርስቲያኖችና የዐረብ ጣኦታውያን ሁኔታ ነው።ሁለቱም ወገኖች

(አይሁዳዎችና ክርስቲያኖች) አንዱ ሌላኛው የሚከተለው ፍኖት ስህተት እንደሆነ፣እርሱ የሚከተለው መንገድ ብቻ ‹ትክክል› እንደሆነ፣ እናም ጀነት (ገነት) የምትገባው ለርሱ ብቻ እንደሆነ ይናገራል፡፡የዐረብ ጣኦታውያንም (አጋሪዎችም) የሁለቱን እምነቶች ከንቱነትና የራሳቸውን እምነት ትክክለኛነት ያጸድቃሉ፡፡አላህ ግን የሁሉም፡- ‹‹እኔ ነኝ ትክክል›› ባይነት ከንቱ ምኞት መሆኑን በግልጽ አውጇል፡፡እንዲህም ይላል፡-

‹‹አይሁዶች፡-‹ክርስቲያኖች በምንም ነገር ላይ(ትክክለኛ እምነት ውስጥ) አይደሉም›› አሉ፡፡ክርስቲያኖች ደግሞ፡- ‹አይሁዶች በምንም ነገር ላይ (ትክክለኛ እምነት ውስጥ) አይደሉም› አሉ፡፡ሁሉም ወገኖች መጽሐፍ ያነባሉ፡፡እነዚያ የማያውቁት (የዐረብ አጋሪዎችም) ያሉት እንደነርሱው ነው፣(ከነርሱ በቀር ሁሉም ወገኖች ትክክለኛ እምነት ውስጥ እንዳልሆነ ይናገራሉ)፡፡ አላህ በሚወዛገቡበት ነገር ብይኑን ይሰጣል፡፡››(ቁርአን፣አል-በቀራህ 2፡113)

ለምሳሌ አይሁዶች ‹‹አይሁድ ያልሆነ ገነት አይገባም፤አይሁድ ሁኑ›› ይላሉ፡፡ክርስቲያኖችም ‹‹ክርስቲያን ያልሆነ ገነት አይገባም፤ክርስቲያኖች ሁኑ›› ይላሉ፡፡ቁርአን የአይሁዶችንና የክርስቲያኖችን ሁኔታ እንዲህ ይነግረናል፡-*‹‹(ቅኑን መንገድ) ትመሩ ዘንድ አይሁድ ወይም ክርስቲያኖች ሁኑ›› አሉ፡፡››(አል-በቀራህ 2፡135)*

እንዲህም ብሏል፡-*‹‹አይሁድ ወይም ክርስቲያን ካልሆነ በቀር ማንም ጀነት አይገባም፡፡›› አሉም፤ይህ የነርሱ (ከንቱ) ምኞት ነው፡፡(ሙሐመድ ሆይ!) (ለምትሉት ነገር) እውነተኛ ከሆናችሁ ማስረጃችሁን አምጡ›› በላቸው፡፡›› (አል-በቀራህ 2፡111)*

የትኛውም ወገን ‹ትክክል ነኝ፤ከኔ ውጭ ያለው መንገድ ስቷል›› ስላለ ሳይሆን ትክክለኝነቱ የሚረጋገጠው ተቀባይነት ያለው አሳማኝ ማስረጃ ማቅረብ ሲችል ነው፡፡ ለዚህም ነው ቁርአን ‹እውነተኛ ከሆናችሁ

ማስረጃችሁን አምጡ›› ያለው።ይህ ስለሌላው ብቻ አይደለም፣ኢስላምም ቢሆን መመርመር አለበት። አላህ(ሱ.ወ) ራሱ ቁርአንን‹መርምሩ›፣ ‹አስተንትኑ› ሲል ይጋብዛል።እንዲህ ሲልም ይጣራል:-‹‹*ቁርአንን አያስተነትኑምን? ከአላህ (አምላክ) ሌላ አካል (የመነጨ ቢኖን ኖሮ ከውስጡ በርካታ ተቃርኖዎችን ባገኙ ነበር።›› (ቁርአን፣አን-ኒሳእ 4:82)*

ቁርአን ‹ሃይማኖት› ያላቸውን ግለሰቦች ብቻ ሳይሆን ‹አምላክ የለም› የሚሉትንም ጭምር እንዲያስቡ፣እንዲመራመሩና እንዲያስተነትኑ ይጋብዛቸዋል።ለምሳሌ ቁርአን እንደሚከተለው በአምላክ መኖር የማያምኑትን ይጠይቃል:- ‹‹ከምንም ነው የተፈጠሩት? ወይስ እነርሱ ራሳቸው ፈጣሪዎች ናቸው? ወይንስ ሰማያትንና ምድርን ፈጥረዋል? አይደለም፣በእውነቱ እነርሱ ጽኑ እምነት የላቸውም።››(ቁርአን አጥ-ጡር 52:35-36)

‹አስተንትኑ›፣‹አዕምሯችሁን ተጠቀሙ›፣‹ጭፍን ተከታይ አትሁኑ!› የሚሉት ምክሮች በቁርአን ዉስጥ በስፋት ተጠቅሰዋል።አንዳንዶች ‹የወላጆቼን እምነት ነው የምከተለው› ይላሉ።ቆም ብለን ካሰብነው ግን ‹የአባት የእናቴ እምነት ስለ ሆነ› የሚለው ምክንያት እጅግ ኋላ ቀር ነው። የወላጁን እምነት ሳይመረምር፣እውነት መሆኑንም ሳይገነዘብና ሳይገባው የሚከተል ሰው እጅግ ኢ-ምክንያታዊ ነው።እንዲህ ያለው ግለሰብ ወላጆቹ የሆኑት ይሆናል። ሙስሊም ቢሆኑ ሙስሊም ይሆን ነበር።የሂንዱ፣ የቡድሃ ፣የክርስትና እምነት ተከታዮች አልያም ጣኦት አምላኪዎች ቢሆኑም ወላጆቹ የሆኑትን ይሆናል።ገደል ቢገቡም አብሯቸው ይገባል።ቁርአን ስለነዚህ አይነት ሰዎች እንዲህ ይላል:-‹‹‹(ካላችሁበት የክህደት ጽልመት ወጥታችሁ) አላህ (በነቢዩ ሙሐመድ ላይ) ያወረደውን (መልዕክት) ተከተሉ።› በተባሉ

ጊዜ ‹በፍጹም! የምንከተለው የአባቶቻችንን ፈለግ ነው።› ይላሉ።(ይህ አቋማቸው እጅግ የሚደንቅ ነው!) አባቶቻቸው ምንም ነገር የማያውቁና ቅኑን ጎዳናም ያልጨበጡ ቢሆኑም (እንኳ ይከተሏቸዋልን?)›› (ቁርአን አል-በቀራህ፣ 2፡170)

እንደ አማኝነታቸው እምነታቸውን ለኛ ለሙስሊሞች መመኘታቸው አያስወቅስም።ብስለት በተሞላበት አኳኋን መወያየት፣ አሳማኝ ማስረጃ ማቅረብና በተሳሳተ ማስረጃ እንዳንሳሳት መጠንቀቅ ግን አስፈላጊ ነው። ስለዚህ ብስለት ሊጎድለን አይገባም።አስተዋይ ሆነን በእውቀትና በምክንያታዊነት መንቀሳቀስ ይገባናል።መጽሐፈ ምሳሌ እንዲህ ይመክራል፡- *‹‹እናንተ ብስለት የጎደላችሁ ጠንቃቃነትን ገንዘብ አድርጉ፣እናንተ ተላሎች ፣ማስተዋልን አትርፉ።›› (ምሳሌ 8፡5)* እንዲሁም፡-*‹‹አስተዋይ ሰው ሥራውን በዕውቀት ያከናውናል፣ተላላ ግን ሞኝነቱን ይገልጣል።›› (ምሳሌ 13፡16)*

የማናውቀውን መከተል አደጋው የከፋ ነው።ምክንያቱም ‹ትክክል ናቸው› ያልናቸውና የተከተልናቸው መሪዎች የተሳሳተ ጎዳና ላይ ሆነው ቢገኙስ? አብረን መሳሳታችን አይደለምን? መጽሐፍ ቅዱስ መሪዎቻቸው ስላሳቷቸው ህዝቦች እንዲህ ይላል፡-*‹‹ህዝቤ ሆይ! መሪዎችህ አሳስተውሃል ከመንገድህም መልሰውሃል።›› (ኢሳይያስ 3፡12)*

እውቀት ከማጣት የተነሳ ስንቶች ጠፉ? *እኛም* እውቀት ከማጣት የተነሳ ጠፍተን ከሆነስ? ሳናዉቅ በጭፍን መከተል ያጠፋናል። ያለ እውቀት መከተል፣ማመን፣እና ደጋፊ መሆን ሊያጠፋን እንደሚችል ልብ ልንል ይገባል።መጽሐፍ ቅዱስ በትንቢተ ሆሴዕ 4፡6 እንዲህ ይላል፡-*‹‹ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሳ ጠፍቷል።››*

ከልጅነት ጀምሮ ዉስጣችን ስላለ ያደግንበት ጎዳና ሁል ጊዜ ‹ቅን› መስሎ ይሰማናል።በጭፍኑ ተከታይ መሆንን አቁመን ማሰብ ግድ ይለናል። ምክንያቱም ቀና መስሎ የሚታየው መንገድ ወደ ውድቀት ሊመራን ይችላልና።ምሳሌ 16:25 እንዲህ ይላል:-«ለሰው ቀና መስሎ የሚታይ መንገድ አለ፣በመጨረሻ ግን ወደ ሞት ይመራል››

ወደተነሳንበት ‹‹ክርስቶስ ማነው?›› ወደሚለው ርዕስ ስንመለስ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለ ክርስቶስም ሆነ በአጠቃላይ በክርስትና እምነት ላይ 303 ወሳኝ ጥያቄዎችን አቅርቤያለሁ።እንደሙስሊምነቴ የክርስትና እምነትን ለምን እንደማልቀበል ለማስረዳት፣‹ካላመናችሁና ካልተጠመቃችሁ አትድኑም› በማለት ሙስሊሙን ሊያዋክቡ ለሚሹ የክርስትና ሚሺነሪዎች፣እስከዛሬ በዚህ መልኩ ስለእምነታቸው (ክርስትና) እንዲያስቡ የሚያደርግ አጋጣሚ ላላገኙ የክርስትና እምነት ተከታዮች እና ስለኢየሱስ ክርስቶስ ማወቅ ለሚሻ ሁሉ ይህንን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ችያለሁ።

ማንኛውንም ነገር ሳያውቁ መንቀፍ አግባብ አይደለም።ማመናችንንም ሆነ አለማመናችን በምክንያትና በማስረጃ ላይ የተደገፈ መሆን አለበት። የኦርቶዶክሱ መጽሐፍ ቅዱስ በመጽሐፈ ሲራክ 11:7 ላይ:- «ሳትመረምረው አትንቀፈው፤አስቀድመህ ነገሩን ጠይቀው» ይላል። ክርስቲያኖች ሙስሊሞችን ‹የኢየሱስን አምላክነት አልተቀበላችሁም› ሲሉ ይወቅሳሉ።

ስለዚህ የቀረቡ ማስረጃዎችን በመመልከት ቶሎ የሚበጀንን እንምረጥ። ትክክለኛውንም እምነት እንወቅ።ይህን መጽሐፍ በጥንቃቄ፤ያለፍርሀት ፣ንዴት፣ነጻ በሆነ አዕምሮና እውነትን ለማወቅ በሚል እሳቤ እንዲያነቡ

እጋብዛለሁ።በመጨረሻም ከመጽሐፉ በምናገኘው ግንዛቤ የሚበጀንን እንምረጥ እላለሁ።መጽሐፉንም እያነበቡ አብረን እንወቅ በማለት በትህትና እጠይቃለሁ።ኢዮብ 34:4 እንዳለው *«የሚበጀንን እንምረጥ፤ መልካሙንም አብረን እንወቅ።»*

አህመዲን ጀበል

## የኢየሱስ ማንነት ጉዳይ

1. በሐዋርያት ሥራ 2:36 ላይ «እንግዲህ፤እግዚአብሔር ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን፤ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ ይረዳ።»[7] ይላል።ታዲያ እግዚአብሔር ኢየሱስን «ጌታ» ካደረገው መጀመሪያ ምን ነበር? «ጌታ» የሚለው የክብር መጠሪያ ከሆነ ያስኬዳል። ነገር ግን «አምላክ» በሚለው ትርጉም ከሆነ የማይመስል ነው። ለምን ቢሉ ከጊዜ በኋላ «ጌታ (አምላክ)» መሆን ይችላልን? ጥቅሱ የሚለው «ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ ይረዳ» ነው። ይህ ማለት ደግሞ በትክክል ጌትነትን ከጊዜ በኋላ ነው ያገኘው የሚል ነው። አምላክ ደግሞ ዘላለማዊ ነው። ታዲያ ኢየሱስ እንዴት አምላክ (ጌታ) ሊባል ይቻለዋል?

2. መጽሐፍ ቅዱስ በሉቃስ ወንጌል 22:3-5 «ሰይጣንም ከዐሥራ ሁለቱ ጋር ከተቆጠረው አንዱ በነበረው የአስቆሮቱ በተባለው በይሁዳ ገባበት።ሄዶም እንዴት አሳልፎ እንደሚሰጣቸው ከካህናት አለቆችና ከመቅደስ አዛዦች ጋር ተነጋገረ።እነርሱም ደስ አላቸው፤ገንዘብም ሊሰጡት ተዋዋሉ።እርሱም በነገሩ ተስማማ።» ይላል።ሰይጣን በይሁዳ ገብቶ ኢየሱስን አሳልፎ እንዲሰጥ ካደረገውና ክርስቲያኖች እንደሚሉት ኢየሱስም ተይዞ ከተሰቀለ ሰይጣን የክርስቲያኖች ባለውለታ ሆኗል ማለት ነው።ለምን ቢሉ ክርስትያኖች እንደሚሉት በኢየሱስ መሰቀል ነውና «ድነው ከኃጢአት ነጻ የወጡት፤ ገነትንም ወራሽ የሆኑት።» ይህ ነው የክርስትና መዳኛ መንገድ።ስለዚህ ሰይጣን በይሁዳ ገብቶ ኢየሱስን አሳልፎ እንዲሰጥ አደረገው።ከዚያም ክርስትና እንደሚለው ኢየሱስ ተይዞ ተሰቀለ። በጥሞና ካስተዋልነው ክርስቲያኖች «ድነናል» ያሉበት «ስቅለት» እንዲሳካ ሰይጣን ግንባር ቀደም አስተዋጽኦ አበርክቷል። የመዳኛውን መንገድ ዘርግቷል።

---

[7] በዚህ መጽሐፍ ዉስጥ ትኩረት እንዲቸራቸው በርካታ ቦታዎች ላይ አስምሬባቸዋለሁ፤(በቦልድ) አጥቁሬያለሁ።

ታዲያ የክርስትና አብዩ አስተምህሮትና መዳኛው የሰይጣን ሊሆን አይደል? ሰይጣን በይሁዳ ገብቶ ኢየሱስን አሳልፎ እንዲሰጥ ባያደርግ ኖሮ ስቅለቱ ይሳካ ነበርን? ክርስትና እንደሚለው ክርስቶስ ባይሰቀል ክርስቲያኖች ከኃጢአት ይነጹ ነበርን? ክርስትና የሚባል እምነትስ ይኖር ነበርን? በፍፁም!!! ታዲያ እንደ ሰይጣን ማን መልካም ሠሪ አለ? ኢየሱስን አሰቅሎ ክርስቲያኖችን አድኖ የለም እንዴ!?

3. ኢየሱስ ሰው መሆኑ በማቴዎስ 8:20፣ማቴዎስ 9:6፣ማቴዎስ 17:9፣ማቴዎስ 17:22፣ማቴዎስ 19:28፣ማቴዎስ 20:18፣ማቴዎስ 20:28፣ማቴዎስ 24:27፣ ማቴዎስ 24:30፣ማቴዎስ 25:31፣ማቴዎስ 26:2፣ማቴዎስ 26:24፣ማቴዎስ 26:45፣ማቴዎስ 26:64፣ማርቆስ 9:31፣ማርቆስ 10:33፣ማርቆስ 10:45፣ ማርቆስ 13:29፣ማርቆስ 14:21፣ማርቆስ 14:41 ፣ማርቆስ 14:6-2፣ሉቃስ 7:34፣ሉቃስ 9:21-22፣ሉቃስ 9:44፣ሉቃስ 9:58፣ሉቃስ 12:8፣ሉቃስ 12:40፣ ሉቃስ 18:31 ፣ሉቃስ 19:10፣ሉቃስ 21:27፣ሉቃስ 22:69፣ሉቃስ 24:7፣ ዮሐንስ 1:51፣ዮሐንስ 3:13-14፣ዮሐንስ 5:27 ፣ዮሐንስ 6:27 ፣ዮሐንስ 6:53፣ ዮሐንስ 6:62፣ዮሐንስ 8:28 እና የሐዋርያት ሥራ 7:55-56 ላይ ተገልጿል:: አምላክ ከሆነ ለምን በርካታ ስፍራ ላይ «የሰው ልጅ»፣«ሰው» ተባለ? አምላክ ሰው ነውን? የሚከተሉት ጥቅሶች አምላክ ሰው እንዳልሆነ ይገልጻሉ :-

ሀ) «ይዋሽ ዘንድ <u>እግዚአብሔር ሰው አይደለም</u>፤ይፀፀትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም::» (ዘኍልቁ 23:19)

ለ) «የእስራኤል ክብር የሆነው እግዚአብሔር አይዋሽም፤አይፀፀትምም፤ <u>እርሱ ይፀፀት ዘንድ ሰው አይደለምና::</u>»(1ኛ ሳሙኤል 15:29)

ሐ) «እኔ በመካከላችሁ ያለሁ ቅዱስ <u>አምላክ ነኝ እንጂ ሰው አይደለሁምና</u> ፤በቁጣ አልመጣም::» (ትንቢተ ሆሴዕ 11:9)

«ኢየሱስ ፍጹም ሰው፤ ፍጹም አምላክ ነው» ስንል አምላክን «ሰው ነው» እያልነው ነው:: ይህ ታዲያ አምላክ ሰው እንዳልሆነ የተገለጸውን መፃረር አይደለምን?

- ሌላው አጠያያቂ ነጥብ ሐዋርያት ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወይም ከመላእክት የላቀ አካል መሆኑን ከተቀበሉ ክርስቶስን «ሰው» ብለው መጥራታቸው ለምን ይሆን? ሐዋርያት የኢየሱስን አምላክነት ከተቀበሉ በኋላ «ሰው» ነበር ብለው ማስተማራቸው ክብሩን መንካትና ደረጃውን መቀመቅ መከተት አይሆንምን?
- ይህን ጉዳይ በአዝነ ልቦና ማየት ተገቢ ነው። በስክነትና በጥሞና መፈተሽም ያስፈልጋል።ሐዋርያት ኢየሱስን አይተውታል።አናግረውታል።አብረው ተመግበዋል።ይህን ሁሉ ሲፈፅሙ ግን ኢየሱስ ልክ እንደነሱ ሰብዓዊ ፍጡር መሆኑን ቅንጣት ታህል ተጠራጥረው አያውቁም። ታዲያ በዚህ ሁኔታ እያለ ኢየሱስ ሰው ሳይሆን «የዓለማት ፈጣሪ አምላክ ነው» ቢባል የሚሰማቸው ድንጋጤና ግርምት እኛ አንድ የምናውቀው ሰው አምላክ ወይም የዓለም ፈጣሪ ነው ብንባል የሚሰማንን ያህል ነው። ለምን? ቢሉ ኢየሱስ በርካታ ሰዋዊ ተግባራት ሲፈፅም፣ ስኬትና ውድቀት ሲፈራረቅበት፣ ሀሴትና ሀዘን ሲመላለስበት ተመልክተዋል። የሰው ልጅን ሊገጥሙ የሚችሉ ሰዋዊ መታከቶች ሲደቁሱት አስተውለዋል።ታዲያ ይህ መሰሉ ሁኔታ የአምላክነት ክብርና ደረጃውን እንዲያስቡ አድርጓቸው ነበር ብሎ ማሰብ ያስኬዳልን? አይመስለኝም!

4. ቆላሳይስ 1:15 ላይ ስለኢየሱስ «እርሱ የማይታየው አምላክ አምሳል ነው፣ ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው፣» ይላል። እንዲሁም በሮሜ 8:29 ላይ «እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰናቸው። ይኸውም ከብዙ ወንድሞች መካከል እርሱ በኩር እንዲሆን ነው።» ይላል። ኢየሱስ «የፍጥረት በኩር» ወይም መጀመሪያ የተፈጠረ ከሆነ እንዴት ከፍጡርነት አልፎ ፈጣሪ ይሆናል? ይህ ሁኔታ የክርስቶስን ማንነት እንድንፈትሽ አይጋብዝምን?

5.እውነተኛ አምላክ ኢየሱስ ነው ወይንስ እግዚአብሔር? የሚከተሉት ጥቅሶች እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ እንደሆነ ይገልጻሉ :-

- «እርሱ ብቻ ጥበበኛ ለሆነ አምላክ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለዘላለም ክብር ይሁን አሜን።» (ሮሜ 16:27) ይህ ጥቅስ «እርሱ ብቻ ጥበበኛ ለሆነ አምላክ» ይላል። ጥበበኛው የኢየሱስ አምላክ ብቻ ከሆነ ኢየሱስ ምን ሊባል ነው?
- ‹‹እግዚአብሔር ግን እውነተኛ አምላክ ነው፤እርሱ ህያው አምላክ፤ ዘላለማዊም ንጉስ ነው፤ በሚቆጣበት ጊዜ ምድር ትንቀጠቀጣለች ፤ መንግስታትም ቁጣውን ሊቋቋሙ አይችሉም።›› (ኤርሚያስ 10:10)
- ኢየሱስ እንዲህ አለ «እውነተኛ አምላክ የሆንኸውን አንተንና የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።» (ዮሐንስ 17:3) ታዲያ ኢየሱስ አምላክ ከሆነ ለአምላኩ ሲጸልይ «እውነተኛ አምላክ የሆንኸውን አንተንና የላክኸውንም ኢየሱስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።» ለምን አለ? ኢየሱስ እውነተኛው አምላክ ራሱ ሳይሆን የላከው አምላክ መሆኑን እንዴት ገለፀ?

6.ከላይ በጠቀስናቸው የክርስትና ሃይማኖት አስተምህሮዎች ውስጥ ቀጥተኛና ግልፅ በሆነ መልኩ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑን አላስተማረም። ለዚያም ነው በክርስቶስ አምላክነት ዙሪያ የማይነጥፉ ጥያቄዎች የሚነሱት።እስቲ አሁን ደግሞ የሚከተሉትን ማገናዘቢያዎች ከስሜታዊነት በፀዳ መልኩ ለማስተዋል እንሞክር። ኢየሱስ አምላክ እንዳለው በሚከተሉት ጥቅሶች ላይ ተገልጿል:-

- «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፤» (1ኛ ጴጥሮስ 1:3)
- «ስለ እናንተ እያመሰገንኩ ስጸልይ ስለ እናንተ ማሳሰብን አልተውም፤የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣቸው እለምናለሁ።» (ወደ ኤፌሶን 1:16-17)

- «ለወደደንና ከኃጢአታችንም በደሙ ነፃ ላወጣን፤አምላኩንና አባቱን እንድናገለግልም መንግስትና ካህናት ላደረገን፤ ለእርሱ ክብርና ኃይል ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን! አሜን።» (የዮሐንስ ራዕይ 1:6)
- «ለዘላለም የተመሰገነው የጌታ ኢየሱስ አምላክና አባት እንደማልዋሽ ያውቃል።» (2ኛ ቆሮንቶስ 11:31)
- «ብርታትንና መጽናናትን የሚሰጥ አምላክ ክርስቶስ ኢየሱስን ስትከተሉ፤ በመካከላችሁ የአንድነትን መንፈስ ይስጣችሁ ፤ይኸውም በአንድ ልብና በአንድ አፍ ሆናችሁ፣ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክና አባት ታከብሩ ዘንድ ነው።» (ሮሜ 15:5-6)
- «በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ ይባረክ።» (ኤፌሶን 1:3)
- «ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላት፤ ከሁሉ የሚበልጠው ይህ ነው፤ «እስራኤል ሆይ! ስማ፣ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፤...»(ማርቆስ 12:29)
- «ኢየሱስም፤«ገና ወደ አብ ስላላረግሁ አትንኪኝ፤ ይልቁንስ ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ፤ «ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፤ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ አርጋለሁ» ብሎአል ብለሽ ንገሪያቸው አላት።» (ዮሐንስ 20:17)
- «በዘጠኝም ሰዓት ኢየሱስ፤ «ኤሎሄ፤ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ ትርጓሜውም «አምላኬ፤ አምላኬ፤ ስለምን ተውኸኝ?» ማለት ነው።» (የማርቆስ ወንጌል 15:34 እና ማቴዎስ 27:46)
- «የርህራሄ አባት፤ የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።» (2ኛ ቆሮንቶስ 1:3)

ኢየሱስ አምላክ እያለው እንዴት ራሱ አምላክ ይሆናል? አምላክ ሌላ አምላክ አለውን? ክርስቲያኖች የሚያመልኩት አምላክ ራሱ አምላክ አለው ማለት ነውን?

7. በሚከተሉት ጥቅሶች ላይ አምላክ አንድ ብቻ መሆኑ ተገልጿል፡- ሮሜ 3:30፣1ኛ ጢሞቴዎስ 2:5 ፣ማርቆስ 12:32 ፣ያዕቆብ 2:19 ፣ሚልኪያስ 2:10 ፣1ኛ ቆሮንጦስ 8:6 ፣ኤፌሶን 4:5-7 እና ዘዳግም 6:4-5:: አምላክ አንድ ብቻ መሆኑን ከተስማማን በኋላም ግን ክርስትያኖች ‹ኢየሱስ አምላክ ነው› ይላሉ:: ለምንድነው ታዲያ በ1ኛ ቆሮንቶስ 8:6 ላይ «አንድ አምላክ» የተባለው ኢየሱስ ሳይሆን አብ የሆነው? ታዲያ ብቸኛው አምላክ አብ ከሆነ የኢየሱስ አምላክነት ምኑ ላይ ነው?

8. አምላክ የማይሞት መሆኑ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 1:17፣ ሮሜ 1:21-23፣ ሮሜ 1:25 እና 1ኛ ጢሞቴዎስ 6:16 ላይ ተገልጿል:: ኢየሱስ ሟች ነው፤አምላክ የማይሞት ከሆነ ኢየሱስ ሟች መሆኑ አምላክ አለመሆኑን አያሳይምን? ኢየሱስ ሲሞት «ሰውነቱ» ነው ወይንስ «አምላክነቱ» ነው የሞተው? በሰውነቱ ከሞተስ እንዴት ሰው የዓለምን ኃጢአት ሊሸከም ይችላል? የአምላክ ወደምድር መምጣት ያስፈለገው ሰው ሊሸከመው ስለማይችል ነው ብለው ክርስትያኖች ያምኑ የለምን? አቋሞን በማስረጃ ቢያስደግፉስ?

9. የሐዋርያት ሥራ 10:38 <u>«እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ</u>ና በኃይል ቀባው፤ እርሱም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበረ በደረሰበት ሁሉ መልካም እያደረገ በዲያብሎስ ሥልጣን ሥር የነበሩትን ሁሉ ፈወሰ::» ይላል:: በመጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ በአንድም ሥፍራ ላይ «እግዚአብሔር» ባይባልም ክርስቲያኖች «ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው» ይላሉ:: «እርሱም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበረ» በሚለው ጥቅስ «እርሱም» እና «እርሱ» የሚሉት ቃላት ኢየሱስን ለመግለጽ በጥቅሱ ውስጥ ስለተገለጹ እንዲሁም ክርስቲያኖች ኢየሱስን «እግዚያብሔር ወልድ» ስለሚሉት ቃላቶቹን በ«እግዚአብሔርም» ብንተካው «እግዚአብሔርም (እርሱም) እግዚአብሔር ከእግዚአብሔር (ከእርሱ) ጋር ስለነበረ» ይሆናል:: ስንት እግዚአብሔሮች ሆኑ?

ክርስትያኖች ሦስት የሆኑትን «አንድ» ቢሉ እዉን ሦስትነታቸውን ትተው አንድ ይሆናሉን? በዚህ ጥቅስ «እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስና በኃይል ቀባው» የሚለውን ብናጤን፣ እግዚአብሔር (አብ) ፣ኢየሱስ (እርሱንም ክርስቲያኖች «እግዚአብሔር ነው» ይላሉ::) እና መንፈስ ቅዱስ (እንደሚሉት እርሱም ከሥላሴዎቹ አንዱና ራሱም እግዚአብሔር ነው::) ይህ ማለት ከሦስቱ ሥላሴዎች እና ራሳቸውም እግዚአብሔር ከሆኑት፣ አንደኛው እግዚአብሔር ሁለተኛውን እግዚአብሔርን በሦስተኛው እግዚአብሔር ቀባው ማለት ነው:: ይህ ትክክለኛ እሳቤ ነው ብለው አእምሮዎን ማሳመን ይችላሉን?

10. ማርቆስ 13:32 ላይ «ነገር ግን ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰዓት ከአብ በቀር፣የሰማይ መላእክትም፣ወልድም ቢሆን፣ማንም አያውቅም::» እንደተባለው ስለ ትንሳኤ ኢየሱስንም ጨምሮ ማንም ከአብ በቀር የሚያውቅ እንደሌለ ተገልጿል ::ክርስቲያኖች እንደሚሉት ኢየሱስ ከአብ እኩል ከሆነ እንዴት የትንሳኤን ጊዜ ማወቅ ተሳነው? አንዱ አምላክ አውቆ ሌላኛው «አምላክ» ሳያውቅ እንዴት ቀረ? ኢየሱስ ሁሉንም የማያውቅ ከሆነ እንዴት አምላክ ነው ልንል እንደፍራለን? አንዳንድ ክርስቲያኖች «ወልድ ሰው ስለሆነ ነው የማያውቀው» ይላሉ::ግና ሰው ብቻ ነውን? ኢየሱስ ወደ ምድር ሳይመጣ በፊትና ወደ ሰማይ ካረገ በኃላ «ወልድ» አይባልምን? ታዲያ ጥቅሱ «ወልድም ቢሆን» እንጂ «ምድር ሳለ፣ ሥጋ በለበሰ ጊዜ» አይል?

11. በዮሐንስ 17:3 (የ1980 እትም) ላይ እንደተገለጸው «የዘላለም ሕይወትም፣ብቻህን እውነተኛ አምላክ የሆንከውን አንተንና የላክኸውን ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ ነው::» በማለት ኢየሱስ ይፀልይ ነበር:: ኢየሱስ ፀሎቱን ያቀረበው «ብቻህን እውነተኛ አምላክ» ብሎ ለጠራው አካል እንደሆነ ልብ ልንል ይገባል:: ቀጥሎም «እንግዲህ አባት ሆይ! ዓለም ሳይፈጠር ከአንተ ጋር በነበረኝ ክብር በአንተ ዘንድ አክብረኝ» ይላል:: (ዮሐንስ 17:5)

እዚህ ላይ ኢየሱስ በእምላክ ዘንድ ለመከበር በፀሎት እየጠየቀ እርሱ ራሱ እንዴት «ብቸኛው እውነተኛ አምላክ» ሊሆን ይችላል? ቆም ብሎ ማገናዘብ አያሻምን?

12. ክርስቲያኖች «ኢየሱስ ኃጢአትን ይቅር ማለት ስለሚችል አምላክ ነው» ይላሉ::[8] በዮሐንስ 20:23 ላይ «ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ «ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው::» ይላል::ታዲያ በዚህኛው ጥቅስ ላይ ደቀመዛሙርቱ ኃጢአትን ይቅር ማለት እንደሚችሉ ተገልጿል::ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱንም አምላክ ልንላቸው ይሆን? «አይደለም! ለደቀመዛሙርቱ ይህን ስልጣን የሰጠው ኢየሱስ ነው!» ሊሉ ይችላሉ:: ግን ይህንን ጥቅስ አላነበቡምን ? «ኢየሱስም ደቀመዛሙርቱ ወዳሉበት ቀርቦ እንዲህ አላቸው፤ «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል፤» ይላል::(ማቴዎስ 28:18) ስልጣን የራሱ ቢሆን ኖሮ ግን «ስልጣን ተሰጠኝ» ሳይሆን «ስልጣን አለኝ» ነበር የሚለው:: ስለዚህ ለኢየሱስ ስልጣን የሰጠው አምላክ መሆኑን እንረዳለን::

13. 1ኛ ቆሮንቶስ 8:6 «ለእኛ ግን ሁሉም ነገር ከእርሱ የሆነ፤ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፤ ደግሞም ሁሉም ነገር በእርሱ አማካይነት የሆነ፤ እኛም በእርሱ አማካኝነት የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን::» ይላል:: በዚህ ጥቅስ ላይ «አንድ አምላክ አብ አለን፤» ሲል አንዱ አምላክ አብ መሆኑን ገልጾ «አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን::» ይላል:: ለምን «አምላክ» እና «ጌታ» በሚል በተለያየ መጠሪያ ተገለፁ? ኢየሱስ «ጌታ» ሲባል አምላክ መሆኑን ለማሳየት ነውን? አምላክ መሆኑን ለማሳየት ቢሆንማ ለምን አብን «አንድ አምላክ» ብሎ ኢየሱስን «አምላክ» ሳይል «አንድ ጌታ» ብሎ ገለፀው?

---

[8] በዐሁ ደሳለኝ፣እኔን ማን ትሉኛላችሁ? የክርስቶስ ማንነትና ሥራዎች፣ሕይወት ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት፣አዲስ አበባ፣1996 ዓ/ም፣ገጽ 36

ኢየሱስ «ጌታ» ስለተባለ አምላክ ሊባል ይቻላልን? እንዲህማ ከተባለ በመጽሐፍ ቅዱስ እነ ሙሴ (ዘኍልቁ 12:11፣ዘኍልቁ 11:28)፣መላዕክት (ዘካርያስ 6:4፣ኢያሱ 5:13-14)፣ዮሴፍ (ዘፍጥረት 42:33 ፣ዘፍጥረት 45:8-9)፣ዳዊት(1ኛመጽሐፈ ነገሥት 1:11-13)፣ኢዮብ (2ኛ ሳሙኤል 11:11)፣ኤልያስ (1ኛ ነገሥት 18:7) እና ሳኦል (1ኛ ሳሙኤል 24:8) «ጌታ» ተብለው የተጠሩትን ሁሉ «ጌታ» ስለ ተባሉ ለምን አምላክ አንላቸውም?

14. ኢየሱስ ተዓምር ሲያሳይ ተአምራቱን ያዩ ሰዎች ተደንቀዋል።በማቴዎስ 9:8 ላይ «ህዝቡም አይተው ተደነቁ፤ «ለሰውም እንዲህ ያለ ሥልጣን የሰጠ እግዚአብሔርን አከበሩ» ይላል። ታዲያ ይህን ተአምር ያየው ህዝቡ ሁሉ ከሃዲ ነውን? ለምን ቢሉ «ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ በራሱ ስልጣን ተአምራቱን አደረገ» ብለው እንደ ዛሬዎቹ ክርስትያኖች አላመኑም። «ለሰውም እንዲህ ያለ ስልጣን የሰጠ እግዚአብሔርን አከበሩ» ይላል። ታዲያ ኢየሱስ አምላክ ቢሆንና በራሱ ስልጣን ቢኖረው ለምን እግዚአብሔር ይህን ተአምር እንደሰጠው ገለፀ? እግዚአብሔር የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ የጋራ ጥምረት ከሆነና «እግዚአብሔር» የሚለው ኢየሱስን የሚጨምር ከሆነ ህዝቦቹ እግዚአብሔርን ሲያከብሩ ኢየሱንንም ይጨምሩት ነበር። ነገር ግን እርሱን «ሰው ነው» ብለው አመኑበት። ታዲያ ያንን ሁሉ ታላላቅ ተአምራት ያየውንና ኢየሱስን የተከተለውን ህዝብ እምነት ትተን በተቃራኒ ማመን አግባብ ነውን?

15. ከኢየሱስ በፊት የነበሩት ነብያት አምላክ አንድ መሆኑን፣ ብቸኛና ኃያል መሆኑን ሰብከዋል፤ ሕዝቡም ተቀብሎ አምኗል። ምእመናን ደግሞ አምላክ በትንሳኤ እለት ለፍርድ እንደሚመጣ ተምረው ተቀብለዋል። መጽሐፍ ቅዱስም አምላክ እግዚአብሔር እንደሚፈርድ በመዝሙር 75፥2 ላይ «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ «ፍርዱ የሚሰጥበትን ጊዜ ወስኛለሁ፤ በዚያን ጊዜ በቅንነት እፈርዳለሁ» እንዲሁም በመዝሙር 75፥7 ላይ ፦ «በአንዱ ላይ የሚፈርድ ሌላውን ነጻ የሚያወጣ ቅን ፈራጅ እግዚአብሔር

ነው።» ሲል ይገልጻል። ስለዚህ እርሱ እንደሚፈርድ አምነው ተቀብለውታል። በአዲስ ኪዳን ግን ኢየሱስ የተባለ «የአምላክ ልጅ» መኖሩንና እርሱም እንደሚፈርድ ወዘተ ጳውሎስ አስተምሯል። ታዲያ ነገ በትንሳኤ ከኢየሱስ በፊት የነበሩት አማኞች የአምላክን ፍርድ ለማየት ሲጠባበቁ ዳኛው ሌላና ኢየሱስ የተባለ ሰው ሆኖ ሲያገኙት ምን ይሰማቸዋል? ያስተማሯቸውን ነብያት «ሐሰተኛ» ሊሉ ነውን? ኢየሱስስ በማን አስተምሮት ነው የሚፈርድባቸው?

16. የሉቃስ ወንጌል 2:52 ላይ «ኢየሱስም በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት አደገ።» ይላል።ኢየሱስ አምላክ ከሆነ እንዴት አምላክ በጥበብ ያድጋል? ከማደጉ በፊትስ? ፍፁም የሆነው አምላክ ሁሉን አዋቂ ነው ። የቀድሞውንም፣ የአሁኑንም ሆነ የወደፊቱንም ያውቃል። ኢየሱስ ግን ከጊዜ በኋላ ነው በጥበብ ያደገው። ታዲያ እንዴት አምላክ ይሆናል?

17. መጽሐፍ ቅዱስ (የ1980 እትም) በዕብራውያን 5:7-8 ላይ ስለ ኢየሱስ እንዲህ ተገልጿል:- «እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፤ እግዚአብሔርንም ስለመፍራቱ ተሰማለት፤ ምንም ልጅ ቢሆን ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ» ይላል። ክርስቲያኖች እንደሚሉት ኢየሱስ «አምላክ» ከሆነ አምላክ እንዴት ከልምድ ይማራል? ጥቅሱ ይቀጥልና «እግዚአብሔርንም ስለመፍራቱ ተሰማለት» ሲል ይገልጻል።

ኢየሱስ እግዚአብሔር ከሆነ እግዚአብሔር ራሱን ይፈራልን? ኢየሱስ አምላክን እንደሚፈራ በዚህ ጥቅስ ተገልጿል። ታዲያ «ኢየሱስ አምላክ ነው» ከተባለ እንዲሁም «አምላክ አንድ ነው» ካልን ኢየሱስ የፈራው እራሱን ነው ማለት አይሆንምን? እንዴትስ አምላክ ራሱን ይፈራል? ወይስ ከሦስቱ አማልክት ውስጥ አንዱ ሌላኛውን ይፈራል?

18. እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ በሚከተሉት ጥቅሶች ላይ «ኢየሱስን ከሞት ያስነሳው» አምላክ መሆኑ ተገልጿል። እነርሱም :- ሮሜ 10:9፣ ገላትያ 1:1 ፣ ኤፌሶን 1:20-21፣ ቆላስይስ 2:11-12፣ 1ኛ ጴጥሮስ 1:21፣ የሐዋርያት ሥራ 2:23-24፣ የሐዋርያት ሥራ 3:15 ፣የሐዋርያት ሥራ 10:40 ፣የሐዋርያት ሥራ 13:33-34 ፣የሐዋርያት ሥራ 3:26 ፣የሐዋርያት ሥራ 4:10 ፣የሐዋርያት ሥራ 13:37 እና የሐዋርያት ሥራ 6:14 ናቸው። በቀረበው ማስረጃ «ኢየሱስን ከሞት ያስነሣው» አምላክ ከሆነ ታዲያ እንዴት «ኢየሱስ ሞትን ድል አደረገ» ይባላል? እንዴትስ «በሞት ላይ ስልጣን ስላለው ተነሣ» ልንል እንችላለን?

19. በዮሐንስ 14:12 ላይ ኢየሱስ «እውነት እላችኋለሁ፤በኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ ይሠራል፤ እንዲያውም እኔ ወደ አብ ስለምሄድ፤ ከእነዚህም የሚበልጥ ያደርጋል።» ብሏል። እንግዲህ ክርስቲያኖች «ኢየሱስን አምላክ ነው» እንደሚሉት ካሰብን በኢየሱስ የሚያምን ሰው ከአምላክ በላይ ሥራን መስራት ሊችል ነው ማለት ነው። ታዲያ ከአምላክ መብለጥ ተቻለ ማለት አይደል? ከአምላክ እንኳን ሊበልጥ ይቅርና ሊነፃፀር የሚችል ሥራ ማንስ መስራት ይችላል?

20. ዮሐንስ 10:36 ላይ «ታዲያ፤«የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ» ስላልሁ፤ አብ ለራሱ ለይቶ የቀደሰውንና ወደ ዓለም የላከውን፤ ተሳድበሃል ብላችሁ ለምን ትወነጅሉኛላችሁ?» ይላል። ኢየሱስም «አምላክ ነው» ከተባለ፣ እንዴት አምላክ ይቀደሳል? ኢየሱስ ተለይቶ ከመቀደሱ በፊት ምን ነበር? እንዴትስ አምላክ ይባላል?

21. ሮሜ 8:17 ላይ «ልጆች ብንሆን ወራሾች ደግሞ ነን፣ የክብሩ ተካፋዮች እንሆን ዘንድ በእርግጥ የመከራው ተካፋዮች ብንሆን፣ የእግዚአብሔር ወራሾች፣ ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን።» ይላል። ክርስቶስ እውን

አምላክ ከሆነ፣ እንዲሁም የሥላሴ አንዱ አካል ከሆነ ወራሽ ነው ወይንስ አስወራሽ? ነገ የእግዚአብሔርን ገነት ሊወርስ ነው ማለት ነውን? እንዲህም ሆኖ አምላክ ትሉታላችሁ?

22. እንደ ሉቃስ ወንጌል 23:43 አገላለጽ ኢየሱስ መስቀል ላይ ሆኖ አብሮት ከተሰቀለው ለአንዱ «በእውነት እልሃለሁ፣ ዛሬዉኑ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ!» አለው።» ይላል። ክርስቲያኖች እንደሚሉት ኢየሱስ አምላክ ከሆነ እንዴት አምላክ ገነት ይገባል? አምላክ ገነት ይገባል ወይንስ አማኞችን ያስገባል?

23. ዕብራውያን 1:13 ላይ «እግዚአብሔር፤ «ጠላቶችህን የእግርህ መርገጫ እስከማደርግልህ ድረስ፤ በቀኜ ተቀመጥ» ያለው ከመላእክት ከቶ ለማን ነው?» ይላል። ይህ ጥቅስ እንደሚነግረን «በቀኜ ተቀመጥ» የተባለው ኢየሱስ ብቻ ከሆነ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መመለስ ያሻል:-
ሀ. ኢየሱስም አምላክ ነው እየተባለ እንዴት በጊዜ ተወስኖ ከእግዚአብሔር ቀኝ እንዲቀመጥ ይፈቀድለታል? ከአምላክ ማን በልጦ ይህን ያዘዋል?
ለ. ጠላቶቹን የእግሩ መርገጫ ካደረገ በኋላ ኢየሱስን እግዚአብሔር ከቀኙ ያነሳዋል ማለት ነው። ለምን? ቢሉ «የእግርህ መርገጫ እስከማደርግልህ» ነው ያለውና። ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ቀኝ ከተነሣ በኋላ ምን ይሆናል?
ሐ. ኢየሱስ ከመላዕክት ቢለይም ያው ከእግዚአብሔር እገዛን የሚሻ አይደለምን?
መ. አምላክ እግዚአብሔር ነው ወይንስ በጊዜ ገደብ ከ«እግዚአብሔር ቀኝ» እንዲቀመጥ የተፈቀደለት ኢየሱስ?

24. ኢየሱስ አምላክ ነው ወይንስ የአምላክ አምሳል? ቆላስይስ 1:15 እና 2ኛ ቆሮንጦስ 4:4 ኢየሱስ የእግዚአብሔር አምሳል መሆኑን ይናገራሉ። እንደዚሁም በዘፍጥረት 1:26 ላይ ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩ ተገልጿል። ታዲያ ኢየሱስ እንደማንኛውም ሰው የእግዚአብሔር አምሳል ከሆነ ልዩነቱ ምኑ ላይ ነው? ያው መቼም አምላክ አምላክ ነው።

ክርስትና እንደሚለው ደግሞ ኢየሱስ አምሳሉ ነው፤ ኢየሱስ «አምላክ»ም፣ «የአምላክ አምሳልም» ሊሆን ይችላልን? እንዴት ራሱና አምሳሉ አንድ ይሆናሉ?

25. ኢየሱስ አንድ ጊዜ «ፍፁም አምላክ»፤ በሌላ ጊዜ «ፍጹም ሰው» ይሆናል ካልን በክርስቶስ ማንነት ላይ ብዥታው ይጎላል።ምክንያቱም አምላክ «እኔ እግዚአብሔር አልለዋወጥም።» ሲል በሚልክያስ 3:6 ላይ ገልጿል። ታዲያ አምላክ ይህንን ቃሉን አጠፈ ማለት ነውን?

26. በማርቆስ 9፥21-23 ላይ «ኢየሱስም የልጁን አባት «ይህ በሽታ ከጀመረው ምን ያህል ጊዜ ነው?» ሲል ጠየቀው።አባትየውም እንዲህ አለ «ከሕጻንነቱ ጀምሮ ነው። ሊገድለውም እየፈለገ ብዙ ጊዜ በእሳትና በውሃ ውስጥ ይጥለው ነበር፤ ግን ቢቻልህ እባክህ እዘንልን፣ እርዳንም።» ኢየሱስም «ቢቻልህ ትላለህን? ለሚያምን ሁሉ ነገር ይቻላል» አለው።» ይላል። ኢየሱስ ክርስቲያኖች እንደሚያስቡት «አምላክ» ከሆነ ታዲያ በማን አምኖ ነው ተዓምር ማድረግ የቻለው? ለምን ቢሉ «ለሚያምን ሁሉ ነገር ይቻላል» በማለት «ቢቻልህ» ተብሎ የተጠየቀውን ጥያቄ መልሷል። አምላክ ስለሆንኩ ምን ይሳነኛል አለማለቱም አስተውሎት ሊቸረው ይገባል።

27. በራዕይ 2:27 ላይ:-«ይህም ልክ እኔ ከአባቴ ሥልጣንን እንደተቀበልኩ ነው።» ይላል። ስለዚህ ኢየሱስ ሥልጣንን ተቀብሏል። እንዲያውም «ሥልጣንን እንደተቀበልኩ» ሲል ከጊዜ ጋር አቆራኝቶ ገልጿል። ታዲያ ሥልጣንን ሳይቀበል በፊት ኢየሱስ ምን ነበር ?

28. ኢየሱስን «ጌታ» ይሉታልን? ይህ ከሆነ መንግስተ ሰማያት መግባት አይፈልጉም ማለት ነው። ለምን ቢሉ በማቴዎስ ወንጌል 7:20-23 ላይ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፦ «በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! የሚለኝ ሁሉ መንግስተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።በዚያ ቀን ብዙዎች ፡- ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! በስምህ ትንቢት

<u>አልተናገርንምን? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን? ይሉኛል:: በዚያን ጊዜም ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ::»</u> ይላል:: ኢየሱስን «ጌታ» የሚለው ማነው? ሙስሊሞች ወይንስ ክርስቲያኖች? «አላውቅኋችሁም፤አመሰክርባቸኋለሁ» ያለውስ ማንን ነው? ክርስቲያኖችን! የትኞቹን ክርስቲያኖች? የሚል ጥያቄ ከተነሳ ደግሞ «ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ: የሚለኝ ሁሉ» ብሎ ኢየሱስ ገልጾታል! እና መንግስተ ሰማያት መግባት አይፈልጉም? ለምን ሌላ ትርጉም በመስጠት ራስዎን ያታልላሉ? ኢየሱስን ጌታ ከማለት ውጭ የአምላክን ተእዛዛት መጠበቅና የአምላክን ፈቃድ መተግበር ትተዋል:: ታዲያ እንዴት ተዘናጉ?

**29.** እንደ ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 7 ከቁጥር 16-17 ከሆነ:- «ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤«የማስተምረው ትምህርት ከራሴ ሳይሆን፤ከላከኝ የመጣ ነው:: ማንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ቢፈልግ፤<u>የእኔ ትምህርት ከእግዚአብሔር ወይም ከራሴ የመጣ መሆኑን ለይቶ ያውቃል::</u>» ሲል ተናግሯል:: በዚህ ጥቅስ ላይ ኢየሱስ «ከእግዚአብሔር ወይም ከራሴ» ሲል እግዚአብሔርና እርሱ የተለያዩ መሆናቸውን አስረድቷል:: ታዲያ ኢየሱስና እግዚአብሔር የተለያዩ ከሆኑ ክርስቲያኖች ስንት አማልክትን ነው እየተገዙ ያሉት? ኢየሱስን ወይስ እግዚአብሔርን?

**30.** ዕብራውያን 1:4-5 እንዲህ ይላል:- «ስለዚህ የወረሰው ስም ከመላእክት ስም እንደሚበልጥ ሁሉ እርሱም ከመላዕክት እጅግ የላቀ ሆኖአል:: እግዚአብሔር «አንተ ልጄ ነህ፤ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ ወይስ ደግሞ <u>«እኔ አባት እሆነዋለሁ፤ እርሱም ልጅ ይሆነኛል» ያለው</u> ከመላእክት ከቶ ለማን ነው?» በዚህ ጥቅስ ላይ «ዛሬ ወልጄሀለሁ» ሲለው፤«ዛሬ» የሚለው ቃል የሚያሳየን ይህ አገላለጽ «ዓለም» እና «ጊዜ» ከተፈጠረ በኃላ መሆኑን ነው:: ምክንያቱም ጊዜ ፍጡር ስለ ሆነ ጊዜ ከመፈጠሩ በፊት «ትናንት

፤ዛሬ፣ነገ» ወዘተ የሚሉና ጊዜን አመላካች የሆኑ ቃላት አልነበሩምና:: «ዛሬ» ተብሎ የተገለፀው ቀን ከመወለዱ በፊት ነበርን? እንዲሁም «የወረሰው ስም በመላእክት ስም እንደሚበልጥ ሁሉ» ይላል:: ኢየሱስ «የእግዚአብሔር ልጅ» የመባልን ስም ከመውረሱ በፊት ምን ነበር? እንዲሁም «<u>እኔ አባት እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል</u>» ይላል:: «እኔ አባት እሆነዋለሁ» ሲል «አባቱ ነኝ» ማለት እንዳልሆነ ልብ ብለዋልን? «እሆነዋለሁ» ማለት የወደፊት ጊዜን አመላካች አይደለምን? እንዲሁም ጥቅሱ «እኔ አባት እሆነዋለሁ፤እርሱም ልጅ ይሆነኛል፤» ያለው ከመላዕክት ከቶ ለማን ነው?» ይላል::በጥቅሱ ላይ «ያለው ከመላዕክት ከቶ ለማን ነው?» ሲል «ያለው» በማለት መግለፁ ምንን ያስመከታል? «ያለው» ሲል በተምሳሌታዊ አገላለጽ(symbolical exprerssions) «ልጅ ነህ» ማለት እንጂ በተግባር መወለዱን አያመለክትም:: ይህ ባይሆንማ ኖሮ በጭራሽ ከመላዕክት ጋርም ባልተነፃፀረ ነበር::

31. መጽሐፍ ቅዱስ ላይ «ሰዎች ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ፤እንደዚሁም ሰዎች ሁሉ በክርስቶስ ሕያዋን ይሆናሉ፤ ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል፤ መጀመሪያ በኩራት የሆነው ክርስቶስ፤ ከዚያም በኋላ እርሱ ሲመጣ የክርስቶስ የሆኑት:: ከዚያም ግዛትን፤ ሥልጣንና ኃይልን ሁሉ ከዳሰሰ በኋላ <u>መንግስትን ለእግዚአብሔር አብ ሲያስረክብ፤ ያን ጊዜ ፍፃሜ ይሆናል:: ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ ሥር እስከያደርግ ድረስ ሲነግሥ ይገባዋልና</u>::» (1ኛ ቆሮንቶስ 15:22-24) እንዲሁም «<u>ሁሉ ከተገዛለት በኋላ እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ እንዲሆን ወልድ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ለእርሱ ይገዛል::»</u> ይላል:: (1ኛ ቆሮንቶስ 15:28) (የ1980 እትም) ኢየሱስ ስልጣን እንደተሰጠው ተናግሯል:: ግን ይህ ጥቅስ በሚገርም መልኩ ስልጣኑን እንደሚያስረክብ ይገልፃል:: ታዲያ ኢየሱስ ከጊዜ በኋላ ከስልጣን የሚወርድ ከሆነ ምኑ ላይ ነው የእርሱ አምላክነት? ኢየሱስ ከስልጣኑ ወርዶ ለአምላኩ የሚገዛ ከሆነ ምኑን አምላክ ሆነ? ክርስቲያኖች አሻፈረን አሉ እንጂ ኢየሱስ በምድር ላይ ሳለም አምላኩን ሲገዛ አልነበረምን? ኢየሱስ

የሚነግሠው በጥቅሱ «ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ ሥር እስኪያደርግ ድረስ ሊነግሥ ይገባዋልና፡፡» በማለት እንደተገለፀው ከሆነ የእርሱ «ንግስና» በጊዜ የተገደበ ነው፡፡ አምላክ ግን ከዘላለም እስከ ዘላለም ንጉስ ነው፡፡ ስልጣንን ለማንም አያስረክብም፡፡ ኢየሱስ ግን «መንግስትን ለእግዚአብሔር አብ ሲያስረክብ፤ ያን ጊዜ ፍፃሜ ይሆናል» ተብሎ እንደተገለፀው ስልጣኑን ያስረክባል፡፡ ታዲያ ኢየሱስን አምላክ ልንለው እንዴት ይቻለናል? ጥቅሱ እግዚአብሔርን ነው እንጂ «<u>እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ እንዲሆን</u>» ያለው ኢየሱስን አይደለም፡፡ አልያም «አንድ እግዚአብሔር» የሚሆኑት «አብ፣ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን» አላለም፡፡ ታዲያ እንዴት ኢየሱስ አምላክ ሊባል ይችላል?

32. በማርቆስ 11:12-14 ላይ «በማግስቱ ከቢታንያ ሲወጡ ተራበ፤ ቅጠል ያለበት በለስ በሩቁ አይቶ ምናልባት አንዳች አገኝባት እንደሆነ ብሎ ወደርሷ መጣ፤ ነገር ግን የበለስ ወራት አልነበረምና ከቅጠል በቀር ምንም አላገኘ ባትም፡፡ ከዚያም ዛፏን፦ ከአሁን ጀምሮ ለዘላለም ማንም ፍሬ ከአንቺ አይብላ» አላት፡፡ ደቀመዛሙርቱም ይህን ሲናገር ሰሙት፡፡» ይላል፡፡ «አምላክ ነው» የሚባለው ኢየሱስ እርሱ እንኳን ባለበት ሆና ፍሬ ይኑራት አልያም አይኑራት የሚለውን ማወቅ ተስኖት ለማረጋገጥ ቀርቦ ቢያጣባት ለምን ይረግማታል? እርሷ ምን ታድርግ? የበለስ ወቅት አልነበረም፡፡ ኢየሱስ አምላክ ቢሆን ኖሮ እንዴት ከፊቱ ራቅ ብላ ያለች በለስ ፍሬ ይኑራት አይኑራት ማወቅ ይሳነዋል? በለሷንስ አምላክ አይደል ፍሬ እንድታፈራ የሚያደርጋት? አምላክስ ከበለስ ምን ጉዳይ ኖሮት ሲያጣባት ይረግማታል?

33. እንደ ክርስትና እምነት «ኢየሱስ ሰውም አምላክም ነው»፡፡ ኢየሱስ ፍጡር ነውን? «አይደለም» ከሆነ ምላሽም ኢየሱስ ሰው አይደለም ማለት ነው፡፡«አዎን» ካሉ ደግሞ «አምላክ» አይደለም፡፡ ምክንያቱም አምላክ ፍጡር አይደለምና፡፡ ታዲያ ምን ሊሆን ነው?

34. በማቴዎስ 19፥16-17 እንደተዘገበው ኢየሱስ የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት ምን ማድረግ እንደሚገባ ሲጠየቅ «ትዕዛዝን ጠብቅ» ሲል መልሷል:: የመጀመሪያው ትዕዛዝ በአምላክ አንድነት ማመን ነው:: (ዘፀአት 20፥3) ታዲያ ኢየሱስ በሥላሴ ካመነና የሥላሴ አባልም ከሆነ ለምን እንዲህ ሲል መለሰ? ቤተክርስቲያን የሚዳነው በሥላሴ በማመን እና ኢየሱስ ለሰው ልጆች ኀጢአት ቤዛ መሆኑን በማመን እንደሆነ ታስተምራለች:: ታዲያ እውነተኛው አስተምህሮት የትኛው ነው? የኢየሱስ ወይንስ የቤተክርስቲያን?

35. በዮሐንስ ወንጌል 8:40 ላይ «ኢየሱስ እንዲህ ሲል ለአይሁዶች ተናገረ:- «ከእግዚአብሔር የሰማሁትን እውነት የነገርኳችሁን ሰው ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ፤» ይላል::ታዲያ እርሱ «ከእግዚአብሔር የሰማሁትን» ሲል እርሱ እንደማን ሆኖ ነው ከእግዚአብሔር የሚሰማው? እንደ ክርስትና አስምህሮት «እግዚአብሔር» ማለት ሥላሴ የሆነና ኢየሱስን የሚጨምር አይደለምን? ስለ ኢየሱስስ ከርሱ የበለጠ ክርስቲያኖች ያውቃሉ ማለት ነው? እርሱ ስለ ራሱ «እውነቱን የነገርኳችሁን ሰው» ሲል «ሰው» መሆኑን ገልጿል:: ክርስቲያኖች ግን «አምላክ» ይሉታል:: ማንኛው ነው የዋሸው?

36. ማቴዎስ 12:28 ላይ ኢየሱስ:- «እኔ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆንኩ፤ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግስት ወደ እናንተ ደርሳለች::» ብሏል:: ታዲያ ኢየሱስ አጋንንትን በእግዚአብሔር መንፈስ የሚያወጣ ከሆነ ምኑ ነው የሚገርመው? ኢየሱስ «በራሴ» አላለ፤ «በእግዚአብሔር መንፈስ» ነው ያለው:: ተዓምሩስ የማነው? ታዲያ አምላክ ሁሉን ቻይ አይደለምን? ነቢያት በእግዚአብሔር መንፈስ ተዓምራት አሳይተው የለምን? ኢየሱስ በፈጣሪ እገዛ ተአምር ቢሰራ ምን ይለየዋል?

37. ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ አብሮት ስለሆነ አምላክ የምናደርገው ከሆነ ከኢየሱስ ሌላ በርካታ መንፈስ ቅዱስ አብሯቸው የነበሩትን ሁሉንም አምላክ ልናደርጋቸው ነውን?

38. ኢየሱስ በርካታ ነገሮችን ማድረግ ሲያቅተው ተስተውሏል:: ምንም ከራሱ ማድረግ እንደማይችልም በዮሐንስ 5:30 (የ1879 እትም) «እኔ ብቻዬን ከራሴ ምንም ማድረግ አልችልም!» ሲል በግልጽ ተናግሯል:: አምላክ ከራሱ ብቻውን ምንም ማድረግ አይችልምን? አምላክ ከሌላ አካል እገዛ ይሻልን? እንዲሁም ሆኖ ምንም ማድረግ የማይችል አምላክ ነበርን?

39. በዮሐንስ 14:1 ላይ «ልባችሁ አይጨነቅ!በእግዚአብሔር እመኑ! በእኔም ደግሞ እመኑ!» ሲል ኢየሱስ እግዚአብሔርና ኢየሱስ የተለያዩ መሆናቸውን አልገለፀምን? «በኔም ደግሞ እመኑ!» ሲል ራሱን ከእግዚአብሔር ለይቶ ለምን ጠየቀ?

40. ማቴዎስ 26፥29 ላይ «በአባቴ መንግስት አዲሱን የወይን ፍሬ ጭማቂ ከእናንተ ጋር እስከምጠጣበት ቀን ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ የወይን ፍሬ ጭማቂ ዳግመኛ አልጠጣም እላችኋለሁ» ይላል:: ኢየሱስ አምላክ ነው ካልን ነገ አምላክ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ገነት ገብቶ የወይን ጭማቂ ሊጠጣ ነውን? አምላክ ገነት ይገባል ወይንስ ያስገባል?

41. ኢየሱስ ምድር ሳለ ምንም ማድረግ እንደማይችል በርካታ ስፍራ ላይ ተጠቅሷል:: ወደ ምድር ሲመጣ አምላክነቱን ትቶ ሰው ሆኖ መጣ ማለት ነውን? ሰው ከሆነ ታዲያ የተሰቀለው ኢየሱስ የተባለው ሰው እንጂ አምላክ እንዳልሆነ አያሳይም?

42. ኢየሱስ በተደጋጋሚ ለአምላኩ ሲፀልይ ነበር::ይህም በማቴዎስ 26:39 ፣ማቴዎስ 26:42፣ማቴዎስ 26:44፣ ማርቆስ 1:35፣ማርቆስ 14:35፣ማርቆስ

14:39 ፣ሉቃስ 5:16፣ዮሐንስ 17:1-3፣ዕብራዊያን 5:7 እና ሉቃስ 6:12 ላይ ተገልጿል:: ኢየሱስና አምላክ እኩል ቢሆኑ ኖሮ ለምን ኢየሱስ ለአምላኩ ፀለየ? አምላክ የሚጸልይለት ሌላ አምላክ አለውን? ይፀልያልን? ኢየሱስ አምላክ ከሆነ ለማን ነው ልመናን ያቀረበው? «አምላክ» ከሆነ ለራሱ ነው ልመናን ያቀረበው ማለት ነውን?

43. በመጽሐፍ ቅዱስ አብ ኃያል፣አዳኝ፣ሳኪ፣ፈጣሪ፣ልዑል መሆኑ ሲገለፅ ኢየሱስ ደግሞ ከራሱ ምንም ማድረግ የማይችል፣ ኃይል የለሽ፣ሟች እና መልዕክተኛ መሆኑን እናነባለን:: እንደሚባለው ክርስቶስ በአምላክ የሚላክ፣ ሟች፣ ምንም ማድረግ የማይችል፣ክብሩና ሁሉም ነገር ፀአብ የተሰጠው ከሆነ እንዴት ዘላለማዊ አምላክ ይሆናል?

44. ማቴዎስ 28:18 «ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱ ወዳሉበት ቀርቦ እንዲህ አላቸው:- «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶኛል፤» ይላል::

ሀ) ክርስቲያኖች እንደሚሉት ኢየሱስ አምላክ ከሆነ ዘላለማዊ የሆነው አምላክ እንዴት «ተሰጠኝ» ይላል? ማንስ ሰጠው? ሳይሰጠው በፊትስ ምን ነበር? ወይንስ አምላክነቱ ከጊዜ በኋላ ነው የተሰጠው?

ለ)ከዚህና ከመሰል ጥቅሶች የምንረዳው የኢየሱስ ሕልውና ያልታየበት ወቅት እንደ ነበረ ነው:: የአምላክ ሕልውና ግን አንድም ወቅት አልተቋረጠም:: ኢየሱስ የተፈጠረው በአምላክ በመሆኑም ሕልውናው (አካሉ) ውስን ነው:: ስለሆነም ኢየሱስ የፈጣሪ ብቸኛ ባሕሪ የሆነውን ዘላለማዊነትን ሊላበስ አልቻለም:: አምላክ ብቻ ነው ዘላለማዊ::ኢየሱስ ፍጡር በመሆኑ ለለውጥ ሕግ ተገዥ ነው:: አምላክ ብቻ ነው ሊለወጥ የማይችለው ወይም «ለውጥ» የማይደርስበት:: ታዲያ ምነው ይህን መረዳት ተሳነን?

ሐ) ስለሆነም ኢየሱስ አምላክ አይደለም። ታዲያ በዚህ አባባሉ ምን ሊያመላክት ፈልጎ ይሆን? በአምላክ የተላከ ወይንስ ራሱ አምላክ መሆኑን? ማንስ ሰጠው? ሳይሰጠው በፊትስ ምን ነበር?

45. ኢየሱስ በአምላክ እንደተላከ በተደጋጋሚ ተገልጿል። ለአብነት በማቴዎስ 10:40፣ማርቆስ 9:37፣ ሉቃስ 9:48፣ሉቃስ 10:16፣ዮሐንስ ወንጌል 4:34፣ ዮሐንስ 5:24፣ዮሐንስ 5:30፣ ዮሐንስ 5:36፣ዮሐንስ 6:44፣ዮሐንስ 6:57፣ ዮሐንስ 7:16-18፣ዮሐንስ 7:28-29፣ዮሐንስ 7:33፣ዮሐንስ 8:14-16፣ዮሐንስ 8:18፣ዮሐንስ 8:26፣ዮሐንስ 8:28-29፣ዮሐንስ 8:42፣ዮሐንስ 9:4-5፣ዮሐንስ 1:41-42፣ ዮሐንስ 12:44፣ዮሐንስ 12:49፣ ዮሐንስ 13:20፣ዮሐንስ 14:24፣ ዮሐንስ 15:21፣ዮሐንስ 16:5፣ዮሐንስ 17:6-9፣ ዮሐንስ 17:18፣ዮሐንስ 18:23 ፣ዮሐንስ 18:25፣ዮሐንስ 20:21 እና ዮሐንስ 13:3 ላይ ተገልጿል። ክርስቲያኖች ኢየሱስን «አምላክ ነው» እንደሚሉት ቢሆን ኖሮ አምላክን ማን ይልከዋል? አምላክ ሌላ የሚልከው አምላክ አለውን?

46. በሐዋርያት ሥራ 7:55 ላይ «እስጢፋኖስ ግን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት ፣የእግዚአብሔርን ክብር፣እንዲሁም ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየና፣«እነሆ፣ሰማያት ተከፍተው ፣<u>የሰው ልጅም</u> በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ» አለ።» ይላል። እንዲሁም በማርቆስ ወንጌል 16:19 ላይ «ጌታ ኢየሱስ ይህን ከተናገራቸው በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ፤በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ።» ይላል።አምላክ እግዚአብሔር ነው ወይንስ ከእግዚአብሔር ቀኝ የቆመው ኢየሱስ ነው? ወይንስ ሁለቱም? ታዲያ ምኑ ላይ ነው «እግዚአብሔር አንድ ነው» የሚባለው? «አምላክ (እግዚአብሔር)» ስንል ኢየሱስን ይጨምራል ወይስ አይጨምርም? እግዚአብሔር በዙፋን ላይ ያለው ነው ወይስ ከቀኙ የቆመው ኢየሱስ? እንዲሁም በክርስትና «መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው»።ታዲያ እስጢፋኖስ የተሞላው በአምላክ ነውን? እስጢፋኖስ ኢየሱስ ካረገ በኃላ ከእግዚአብሔር

ጎን ሲቆም ‹የሰው ልጅ› ሲል ጠራው፡፡ታዲያ ካረገም በኋላ ‹ሰው› መሆኑን ሊነግረን ፈልጎ አይደል?

47. ኢየሱስ በሰይጣን ተፈትኗል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ አምላክ በሰይጣን እንደማይፈተን ይናገራል፡፡ «ማንም ሲፈተን ፤«እግዚአብሔር ፈተነኝ» አይበል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንም፤ እርሱም ማንንም አይፈትንም፤» (የያዕቆብ መልእክት 7:13) በተቃራኒው «ከዚህ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን በዲያቢሎስ ይፈተን ዘንድ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው፡፡» (ማቴዎስ 4:1) አምላክ የማይፈተን መሆኑ ተነግሮ ሳለ ኢየሱስ አምላክ ቢሆን ኖሮ እንዴት በሰይጣን ይፈተን ነበር? ታዲያ ኢየሱስ በሰይጣን እየተፈተነ አምላክ ነው ይባላልን? አንድም ቦታ ላይ የኢየሱስ «ሰዋዊ ባህሪው ተፈተነ» አይልም፡፡ ታዲያ ኢየሱስ አምላክ አለመሆኑን አያሳይምን?

48. የዘብዴዎስ ልጆች እናት ሁለቱ ልጆቿን በመንግስት ሰማያት በቀኙና በግራው ያስቀምጥላት ዘንድ ኢየሱስን ጠይቃ እንዲህ ሲል መልሶላታል፡- «ኢየሱስ «በእርግጥ እኔ የምጠጣውን የመከራ ፅዋ ትጠጣላችሁ፤ <u>ነገር ግን በቀኜና በግራዬ እንድትቀመጡ የማደርገው እኔ አይደለሁም፤</u> ይህ ቦታ የሚሰጠው አባቴ ላዘጋጀላቸው ሰዎች ነው፡፡» (ማቴዎስ 20:23) ታዲያ ኢየሱስ ክርስቲያኖች እንደሚሉት አምላክ ከሆነ እንዴት መንግስተ ሰማያት የማስገባው «እኔ አይደለሁም» ሲል ይመልሳል? ክርስቲያኖች እንደሚሉት ከሆነ ለበርካታ ጊዜያት የተለያዩ ነገሮችን ማድረግ የተሳነው «ሥጋ ለብሶ ሰው ሆኖ ወደ ምድር ስለመጣ» ነው፡፡ ነገር ግን በዚህኛው ጥቅስ ኢየሱስ «እኔ አይደለሁም» ሲል እንደማይችል የተናገረው ሥጋ በለበሰበት ጊዜ ሳይሆን በመጪው ዓለም በመንግስተ ሰማያት ነው፡፡ ታዲያ «አምላክ» ከሆነ እርሱስ ለምን እንደ አብ ገነት ማስገባት ይሳነዋል?

49. ኢየሱስ እንዲህ ሲል አምላኩን ለምኗል:- «የምለምንህ ከክፉው እንድትጠብቃቸው እንጂ፣ ከዓለም እንድታወጣቸው አይደለም:: እኔ ከዓለም እንዳልሆንኩ ሁሉ፣ እነርሱም ከዓለም አይደሉም:: ቃልህ እውነት ነው፤ በእውነትህ ቀድሳቸው::» (ዮሐንስ 17:15-16) ኢየሱስ ሁሉን ማድረግ የሚችል ፈጣሪ ቢሆን ኖሮ አምላክን መለመን ለምን አስፈለገው?

50. ሉቃስ 22:43-44 ላይ «መልአክም ከሰማይ ተገልጦለት አበረታው:: እጅግ ተጨንቆም በብርቱ ይፀልይ ነበር፤ ላቡም እንደ ደም ነጠብጣብ ወደ ምድር ይፈስ ነበር::» ይላል::ኢየሱስ ክርስቲያኖች እንደሚሉት ፍፁም ሰው፤ ፍፁም አምላክ ከሆነ ላለመሞት ፈርቶ ይህን ያህል ሲጨነቅ የአምላክ ፍጡር የሆነው መልአክ ከሰማይ ተገልጦለት ከሚያበረታታው የራሱ አምላካዊው ባህሪው በቅርቡ አለለት አይደለምን? ለምን ራሱን አያበረታውም ነበር? «አምላክ» እጅግ ሲጨነቅ መልአክ ያበረታታዋል ማለት ነውን? ምንስ አስጨነቀው? ክርስቲያኖች እንደሚነግሩን ሞትን የፈጠረው ራሱ አይደለምን?

51. የማርቆስ ወንጌል 16:19 «ጌታ ኢየሱስ ይህን ከተነገራቸው በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ፤ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ::» ይላል:: ክርስቲያኖች «በአንዱ አምላክ እናምናለን» ይላሉ:: «አንዱ አምላክ» ብለው ሲለምኑ እግዚአብሔርን ነው ወይንስ ከእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠውን ኢየሱስን ነው? ወይስ ሁለቱንም? ታዲያ ስንት ፈጣሪ ነው ያለው?

52. ሉቃስ 2:40 ላይ «ሕፃኑም እያደገና እየጠነከረ ሄደ፤ በጥበብ ተሞላ፤የእግዚአብሔርም ፀጋ በእርሱ ላይ ነበረ::» ይላል:: እንደ ክርስትና አስተምህሮት ሕፃኑ ኢየሱስ አምላክ አይደለምን? በክርስትና እግዚአብሔር ሥላሴ የሆነ አይደለምን? ኢየሱስን ይጨምር የለምን? ኢየሱስ አምላክ ቢሆን መጀመሪያውኑ ጥበበኛ ይሆን አልነበረምን? እንዴት በጥበብ ይሞላል?

በተጨማሪ «<u>የእግዚአብሔርም ፀጋ በእርሱ ላይ ነበረ</u>» የሚለውን ካስተዋልን «በእርሱ» እና «ሕፃኑም» የሚሉት ቃላት ለኢየሱስ ነው የገቡት:: እንደክርስትና አስተምህሮት «በእርሱ» የተባለው ኢየሱስ «አምላክ /እግዚአብሔር» ነው::

የክርስትና እምነት ይህ ስለሆነ «በእርሱ» እና «ሕፃኑም» በሚለው ምትክ «በእግዚአብሔር/በአምላክ» የሚለውን ብንተካ (ምክንያቱም አንድ ስለሆኑ) «አምላክ (ሕፃኑም) እያደገና እየጠነከረ ሄደ፤<u>በጥበብ ተሞላ</u>፤<u>የእግዚአብሔርም ፀጋ በእግዚአብሔር (በእርሱ) ላይ ነበረ::»</u> ይሆናል:: ይህ ትክክለኛ እሳቤ ነውን? ስንትስ ሆኑ?

53. በዕብራውያን 1:2 ላይ «በዚህ መጨረሻ ዘመን ግን <u>ሁሉን ወራሽ ባደረገውና</u> ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ ለእኛ ተናገረን::» ይላል:: ኢየሱስ በክርስትና እምነት መሠረት «አምላክ ነው»:: አምላክ ወራሽ ነው ወይንስ አስወራሽ?

54. ዕብራውያን 1:4 «ስለዚህ የወረሰው ስም ከመላእክት ስም እንደሚበልጥ ሁሉ፤እርሱም ከመላእክት እጅግ የላቀ ሆኖአል::» ይላል:: «ኢየሱስ ከመላእክት እጅግ የላቀ ሆኖአል» ሲል «የላቀ ነው» ከሚለው ጋር እጅጉን ይለያል:: «ሆኖአል» ሲል መጀመሪያ አልሆነም፤ በኋላ ላይ ሆነ የሚል ትርጉም ያስይዘናል:: ታዲያ አምላክ ነው የሚባለው ኢየሱስ ከመላእክት ያንስ ነበርን?

55. መጽሐፍ ቅዱስ በ2ኛ ጴጥሮስ 1:2 ላይ «እግዚአብሔርንና ጌታችን ኢየሱስን በማወቅ ፀጋና ሰላም ይብዛላችሁ::» ይላል:: ክርስቲያኖች «በአንዱ እግዚአብሔር እናምናለን» ሲሉ ይህ አባባል ኢየሱስን ይጨምራልን? ታዲያ ለምን በዚህኛው ጥቅስ እግዚአብሔርንና ኢየሱስን ሁለት የተለያዩ አድርጎ አቀረበ?

56. የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት «ራእይ»ን እንዲህ በማለት ይተረጉማል:- «ራእይ:- ሰው ሳያንቀላፋ በተመስጦ የሚያየውና የእግዚአብሔር ቃል የሚገለጥበት:: ራእይ ከህልም ይለያል:: ራእይ እግዚአብሔርን ለሚያውቁ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ላደረባቸው ይሰጣል»[9] ይላል::

የዮሐንስ ራእይ 1:1 ላይ:- «ቶሎ መሆን የሚገባውን ነገር ለአገልጋዮቹ እንዲያሳይ፤ እግዚአብሔር ለእርሱ የሰጠው የኢየሱስ ክርስቶስ ራእይ ይህ ነው::» ይላል:: ክርስቲያኖች እንደሚያምኑት ኢየሱስ አምላክ ከሆነ ሁሉንም ያውቃል ማለት:: ነገር ግን ይህ ጥቅስ «እግዚአብሔር ለእርሱ የሰጠው የኢየሱስ ክርስቶስ ራእይ» ይላል:: ታዲያ አምላክ ቢሆን ሁሉን አዋቂ መሆን አልነበረበትምን? ራእይ ሊሰጠው ይገባ ነበርን? እርሱስ ቢሆን የሦስቱ ሥላሴዎች አባል አይደለምን?

57. በማቴዎስ 19፥28 ላይ «ኢየሱስም እንዲህ አላቸው «በእውነት እላችኋለሁ የሰው ልጅ በክብር ዙፋን ላይ በሚቀጥመበት በአዲሱ ዘመን የእኔ ተከታዮች የሆናችሁ እናንተም በአስራ ሁለት ዙፋን ላይ ትቀመጣላችሁ፤ በአስራ ሁለቱም የእስራኤል ነገዶች ላይ ተሾማችሁ ትፈርዳላችሁ::» ይላል:: ከነዚህ አስራ ሁለት ሐዋርያቶች መካከል አንዱ ይሁዳ ኢየሱስን ከድቷል:: ነገር ግን ኢየሱስ አጠገቡ የነበሩትን 12ቱን ሐዋርያት «እናንተ ትፈርዳላችሁ» ሲል ይሁዳን ጨምሮ ነው የገለፀው:: ታዲያ ከሀዲው ይሁዳም ይፈርዳልን? ሌላ ሰው በከሀዲው ምትክ ይተካል እንዳንል «እናንተም»፣ «ትፈርዳላችሁ»፣ «የሆናችሁ»፣«አላቸው» እና «ትቀመጣላችሁ» የሚሉት ቃላት በወቅቱ እዚያ ለነበሩት ለ12ቱ ብቻ መሆናቸው ግልፅ ነው:: ታዲያ ኢየሱስ ይህን

---

[9] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፣የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ፣ገጽ 54

አያውቅምን? ደግሞ ኢየሱስ ስለሚፈርድ «አምላክ» ከተባለ አስራ ሁለቱም ሐዋርያትም አምላክ ሆኑ ማለት አይደለምን?

58. ፊልጵስዮስ 2:9 ስለ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ገልፇል:- «ስለዚህ እግዚአብሔር እጅግ ከፍ አደረገው፤ ከስም ሁሉ በላይ የሆነውን ስም ሰጠው።» ስሙ ሳይሰጠውና ከፍ ከመደረጉ በፊትስ ምን ነበር? ክርስቲያኖች እንደሚሉት ኢየሱስ «አምላክ» ከሆነ አምላክ ከፍ ያደርጋል ወይንስ ከፍ ይደረጋል? ከስም ሁሉ በላይ የሆነው ስምስ ምንድነው? «የአምላክ ልጅ» መባል? ይህ ከስም ሁሉ በላይ የሆነው ስም ሳይሰጠው በፊት ኢየሱስ ምን ነበር? ይህ ስሙን ከማግኘቱ በፊት ጊዜ እንደነበረ አያሳይምን?

59. ዕብራውያን 5:5-6 «እንዲሁም ክርስቶስ ሊቀ ካህናት የመሆንን ክብር ለራሱ አልወሰደም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር፣ «አንተ ልጁ ነህ፣ እኔ አባት ሆንኩህ» አለው» ሲል በሌላ ስፍራ ደግሞ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ» ይላል። ይህ ጥቅስ «ክርስቶስ ሊቀ ካህናት የመሆንን ክብር ለራሱ አልወሰደም» ይላል። የእርሱ ስልጣን ዘላለማዊ ከሆነና ከነበረ እንዴት ከጊዜ በኋላ የመውሰድና ያልመውሰዱ ጥያቄ ይነሳል? በራሱ ባይወስድም ከመውሰዱ በፊት ምን ነበር?

60. የሐዋርያት ሥራ 5:31 ላይ «እርሱም ለእስራኤል ንስሐንና የኀጢአትን ስርየት ይሰጥ ዘንድ፣ እግዚአብሔር የሁሉ ራስና አዳኝ አድርጎ በቀኙ ከፍከፍ አደረገው።» ይላል። እግዚአብሔር በቀኙ ከፍ ሳያደርገውስ በፊት ኢየሱስ ምን ነበር? የኀጢአት ስርየትስ ለማን ነው ይሰጥ ዘንድ የተላከው? ለእስራኤል! ታዲያ ምን ነካቸው?

61. ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ በ2006 እትሙ ላይ እንደገለጸው የክርስቲያኖች ክፍፍል (የክርስትና ዓይነት) 33000 (ሠላሣ ሦስት ሺህ)

ደርሷል።[10] ሁሉም «በመንፈስ ቅዱስ ተነድተናል፣ተሞልተናል፣ስርጾብናል» ወዘተ ይላሉ።እውን መንፈስ ቅዱስ የሚነዳቸው ከሆነ እንዴት ክርስቲያኖችን በመለያየት 33000 ቦታ ከፋፈላቸው? የትኛውስ ነው ትክክለኛው ክርስትና?

62. እንደ ክርስቲያኖች አስተምህሮት «የዮሐንስ ራዕይ» የተባለው መጽሐፍ ሲጻፍ ኢየሱስ ወደ ሰማይ አርጎ ነበር። ታዲያ ለምንድነው በዮሐንስ ራዕይ 1:6 እና 3:12 ላይ በሰማይ ያለው አብ አምላኩ እንደሆነ የተገለፀው?

63. በመዝሙር 89፥27 ዳዊት «የአምላክ ልጅ» ተብሏል። እንዲሁም ሰለሞን (1ኛ ዜና መዋዕል 22፥10) እስራኤል በ (ዘፀአት 4:22፤ በመዝሙር 82፥6) ፣ኤፍሬም (ኤርምያስ 31:9)፣ በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ በ(ሮሜ 8:14) ፣ ሰላም አስፋኞች በ (በማቴዎስ 5፥9)፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ያመኑ በ (ገላትያ 3:13) ፣ አዳም በ (ሉቃስ 3:38) እና ኢየሱስን የተቀበሉት ሁሉ በ (ዮሐንስ 1:10) «የአምላክ ልጅ» ተብለዋል።የኢየሱስ «የአምላክ ልጅ» መባል ከሌሎች የተለየና የሥጋ (እውነተኛ) ከሆነ ለምን ኢየሱስም ሆነ አምላክ ለይተው ይህን አልገለጹም? ያለ ማስረጃ በራሳችን ለምን እንለያለን?

64. በሐዋርያት ሥራ 3:26፣ 4:27 እና 4:30 ላይ የእንግሊዝኛዎቹን መጽሐፍ ቅዱሳት ብንመለከት ኢየሱስን «የአምላክ ባሪያ» በማለት ይገልፃሉ። ነገር ግን የአማርኛዎቹ ይህን ትርጉም እንዳይዙ ሆነው «ባሪያ፣ አገልጋይ» በሚለው ምትክ «ብላቴና፣ ልጅ» በሚለው ተተክቷል።

[10] Encyclopedia Britannica 2006\Ultimate Reference Suite DVD\ Electronic versions

በማስከተል ከእንግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚከተሉት ሰባቱ ኢየሱስን «የአምላክ ባሪያ» ብለው መግለጻቸውንና «ባሪያ» በሚለው ቃል ላይ በማሥመር እንመለከታን :-

ሀ) «እግዚአብሔር ***ብላቴናውን*** ባስነሳ ጊዜ፣ እያንዳንዳችሁን ከክፋ መልሶ ይባርካችሁ ዘንድ አስቀድሞ ወደ እናንተ ላከው።»(የሐዋርያት ሥራ 3:26)

- "When ***God raised up his servant***, he sent him first to you to bless you by turning each of you from your wicked ways." *(Acts 3:26 ,New International version, NIV)*
- "To you first, ***God, having raised up His Servant Jesus***, sent Him to bless you, in turning away every one of you from your iniquities." *(Acts 3:26 ,New King James Version, NKJV)*
- "For you first, ***God raised up His Servant*** and sent Him to bless you by turning every one of you from your wicked ways." *(Acts 3:26 ,New American standard bible Updated edition, NASU)*
- "Unto you first ***God, having raised up his Servant***, sent him to bless you, in turning away every one of you from your iniquities." *(Acts 3:26 ,American Standard Version, ASV)*
- "For you first, ***God raised up His Servant***, and sent Him to bless you by turning every one of you from your wicked ways." *(Acts 3:26 ,New American Standard, NAS)*
- "***God, having raised up his servant***, sent him to you first, to bless you in turning every one of you from your wickedness." *(Acts 3:26 ,Revised standard Version, RSV)*
- "And as soon ***as God had brought his servant*** to life again, he sent him first of all to you men of Israel, to bless you by turning you back from your sins." *(Acts 3:26 ,The Living Bible, TLB)*

ሰባቱም «ባሪያውን ኢየሱስን» ይላሉ።

ለ) «ለመፈወስ እጅህን ዘርጋ፤*በቅዱሱ* <u>*ብላቴናህም*</u> *በኢየሱስ* ስም ድንቅና ታምራትን አድርግ » (የሐዋርያት ሥራ 4:30)

- "Stretch out your hand to heal and perform miraculous signs and wonders through the name of <u>***your holy servant Jesus***</u>." ***(Acts 4:30 ,New International version, NIV)***
- "by stretching out Your hand to heal, and that signs and wonders may be done through the name of <u>***Your holy Servant Jesus***</u>." ***(Acts 4:30 ,New King James Version, NKJV)***
- "and send your healing power, and may miracles and wonders be done by the name of <u>***your holy servant Jesus***</u>." ***(Acts 4:30 ,The Living Bible, TLB)***
- "while thy stretchest forth thy hand to heal; and that signs and wonders may be done through the name of thy <u>***holy Servant Jesus***</u>. " ***(Acts 4:30 ,American Standard Version, ASV)***
- "while You extend Your hand to heal, and signs and wonders take place through the name of <u>***Your holy servant Jesus***</u>." ***(Acts 4:30 ,New American standard bible Updated edition, NASU)***
- "while thou stretchest out thy hand to heal, and signs and wonders are performed through the name of thy <u>***holy servant Jesus***</u>." ***(Acts 4:30 ,Revised standard Version, RSV)***
- "while Thou dost extend Thy hand to heal, and signs and wonders take place through the name of <u>***Thy holy servant Jesus***</u>. "***(Acts 4:30 ,New American Standard, NAS)***

ሰባቱም «አገልጋይህ ኢየሱስ» ይላሉ።

ሐ) «በእርግጥም ሄሮድስና ጳንጥንዮስ ጲላጦስ ከአሕዛብና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በዚች ከተማ አንተ በቀባኸው በቅዱስ ብላቴናህ ላይ ክንድና ፈቃድ ጥንት የወሰኑት እንዲፈጸም ነው።» (የሐዋርያት ሥራ 4:27)

- "Indeed Herod and Pontius Pilate met together with the Gentiles and the people of Israel in this city to conspire against **your holy servant Jesus**, whom you anointed." ***(Acts 4:27 ,New International version, NIV)***
- "For truly against ***Your holy Servant Jesus***, whom You anointed, both Herod and Pontius Pilate, with the Gentiles and the people of Israel, were gathered together ***"(Acts 4:27,New King James Version, NKJV)***
- "For truly in this city there were gathered together against ***Your holy servant Jesus***, whom You anointed, both Herod and Pontius Pilate, along with the Gentiles and the peoples of Israel, " ***(Acts 4:27 ,New American standard bible Updated edition, NASU)***
- "for of a truth in this city against ***thy holy Servant Jesus***, whom thou didst anoint, both Herod and Pontius Pilate, with the Gentiles and the peoples of Israel, were gathered together, " ***(Acts 4:27 ,American Standard Version, ASV)***
- "For truly in this city there were gathered together against ***Thy holy servant Jesus***, whom Thou didst anoint, both Herod and Pontius Pilate, along with the Gentiles and the peoples of Israel, "***(Acts 4:27 ,New American Standard, NAS)***
- "for truly in this city there were gathered together against ***thy holy servant Jesus***, whom thou didst anoint, both Herod and Pontius Pilate, with the Gentiles and the peoples of Israel," ***(Acts 4:27 ,Revised standard Version, RSV)***
- "That is what is happening here in this city today! For Herod the king, and Pontius Pilate the governor, and all the Romans-as well as the people of Israel-are united against ***Jesus, your anointed Son, your holy servant***. " ***(Acts 4:27 ,The Living Bible, TLB)*** ሰባቱም«አገልጋይህ ኢየሱስ» ይላሉ::

ከላይ የጠቀስናቸው የተለያዩ የመፅሀፍ ቅዱስ ቅጂ ጥቅሶች በሙሉ ስለ ኢየሱስ የአምላክ አገልጋይነት እንጂ ስለ አምላክነቱ አይደለም የሚገልፁት!!! ይህ እንግሊዝኛው ሲሆን የ1980 ቀላል ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከበፊቱ በተለየ መልኩ ልክ እንደ እንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስን አገልጋይ ይለዋል፡- «በእርግጥም ሄሮድስና ጴንጤናዊ ጲላጦስ ከአረማውያንና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በዚህች ከተማ ተሰብስበው መሲህ ባደረግኸው በቅዱስ *አገልጋይህ በኢየሱስ* ላይ ተነሱ!» (የሐዋርያት ሥራ 4:27) እንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ «Your servant Jesus» «አገልጋይህ ኢየሱስ» ይላል። ለምን አማርኛው ይህንን «አገልጋይህ» የሚለውን በ«ብላቴናህ» ቀየረው? ኢየሱስ የአምላክ ባሪያና አገልጋይ ከሆነ እንዴት አምላክ ሊሆን ይችላል? የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎችስ ምነው «የአምላክ አገልጋይ» የሚለውን በ«ብላቴና» መለወጣቸው? ኢየሱስ አምላክ እንዲሆን ፈልገው ይሆን?

65. ኢየሱስ መሞቱን ክርስቲያኖች ያምናሉ። አምላክ ግን እንደማይሞት እንደሚከተለው ተገልጿል፡- «የተባረከውና ብቻውን ገዥ የሆነው የነገሥታት ንጉሥ፤ የጌቶች ጌታ እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ የሚያሳየው ነው፤ <u>እርሱ ብቻ የማይሞት ነው</u>፤ ሊቀረብ በማይችል ብርሃን ውስጥ ይኖራል፤ እርሱን ያየ ማንም የለም፤ ሊያየውም የሚችል የለም። ለእርሱ ክብርና ኃይል ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን፤ አሜን።» (1ኛ ጢሞቴዎስ 6:16) እንዲሁም «<u>ብቻውን አምላክ</u> ለሚሆን፤ <u>ለማይሞተው ለማይታየውም</u> ለዘመናት ንጉስ ምስጋናና ክብር እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን፤ አሜን።» (1ኛ ጢሞቴዎስ 1፤17)

ታዲያ ኢየሱስ ሟች ከሆነና አምላክ የማይሞት ከሆነ ኢየሱስ አምላክ እንዳልሆነ አያሳይምን? እንዲሁም «ብቻውን አምላክ ለሚሆን» ሲል ጥቅሱ አምላክ ብቸኛ፣እርሱም እግዚአብሔር መሆኑንና ኢየሱስ የሚባል ሌላ አምላክ እንደሌለ አያሳይምን?

66. በ2ኛ ቆሮንቶስ 5:18 ላይ «ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን፣ የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሄር ነው» ይላል። በክርስትና ጽንሰ ሐሳብ አምላክ «ከሰማየ ሰማያት ወርጄ፣ ከድንግል ማርያም ተወልጄ አድንሃለሁ» ስላለ ወርዶና ተወልዶ አዳነን ይባላል። ነገር ግን ጥቅሱ «በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን» ይላል። አምላክ የሚባለው ክርስቶስ ነው ወይንስ በክርስቶስ አማካኝነት ከራሱ ጋር ያስታረቀው ነው? ጥቅሱ ይቀጥልና «የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሔር ነው» ይላል። «አንዱ እግዚአብሔር» ሲባል ክርስቶስን ይጨምራል ወይንስ አይጨምርም? ከጨመረ አንዴት አንዴም ቢሆን ይህ አልተገለጸም? ካልጨመረስ ክርስቶስ ስንተኛ አምላክ ሊሆን ነው?

67. በዕብራውያን 3:3 ላይ ስለ ኢየሱስ ሲገልጽ «ቤትን የሚያዘጋጀው ከቤቱ ይልቅ የሚበልጥ ክብር እንዳለው መጠን እንዲሁ እርሱ ከሙሴ ይልቅ የሚበልጥ ክብር የተገባው ሆኖ ተቆጥሮአልና።» ይላል። ታዲያ ኢየሱስ አምላክ ነው ከተባለ እንዴት ከሙሴ ጋር ይነጻጸራል? አምላክ ከማን ጋር ሊነጻጸር ይችላል?

68. በኢሳይያስ 44:6-7 ላይ አምላክ እንዲህ ማለቱን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል:- «የእስራኤል ንጉሥ ቤዛ እግዚአብሔር፣ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ <u>የፊተኛውም እኔ ነኝ፣ የኋለኛውም እኔ ነኝ፣ ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም፣ እስቲ እንደ እኔ ማን አለ? ይናገር</u>።» ክርስቲያኖች እንደሚሉት ኢየሱስ አምላክ ከሆነ እና አምላክም ሥላሴ (ሦስትም አንድም) ከሆነ እንዴት አንዱ አምላክ «ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም» ይላል? እንዲሁም እንዴት «እስቲ እንደ እኔ ማን አለ? ይናገር፣» ይላል? ምናልባት ያኔ ኢየሱስ ገና ስላልተወለደ ይሆንን? በፍፁም! እንዲህማ ቢሆን ኖሮ ለምን «የፊተኛውም እኔ ነኝ፣ የኋለኛውም እኔ ነኝ፣ ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም» ሲል ይናገራል?

69. የማቴዎስ ወንጌል 12:18 ላይ ስለ ኢየሱስ:- «እነሆ የመረጥሁት የምወደውና በእርሱ ደስ የሚለኝ አገልጋዬ መንፈሴን በእርሱ ላይ አኖራለሁ፤ እርሱም ለአህዛብ ፍትህን ያውጃል!» ሲል ይገልጻል:: በዚህ ጥቅስ ኢየሱስ የአምላክ አገልጋይ መሆኑ ተጠቅሷል:: ክርስቲያኖች እንደሚሉት ኢየሱስ «አምላክ» ነው ወይንስ ይህ ጥቅስ እንደሚለው የአምላክ አገልጋይ? አምላክ «አገልጋዬ» እያለው ክርስቲያኖች እንዴት አምላክ ነው ይሉታል?

70. በማቴዎስ 15:12 ላይ «በዚያን ጊዜ ደቀመዛሙርቱ ቀርበው ፈሪሳውያን ይህን ቃል ሰምተው እንደተሰናከሉ አወቅህን? አሉት::» ይላል:: ደቀመዛሙርቱ «ኢየሱስ ኃያሉ አምላክ ነው» ብለው ቢያምኑ ኖሮ እንዴት «አወቅህን?» ብለው ይጠይቁታል? አምላክ መሆኑ ከታመነ ሁሉን አዋቂ ነውና «አወቅህን?» ተብሎ ይጠየቃልን?

71. በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለፀው ኢየሱስ የትንሳኤን ጊዜ የማያውቅ፣ ከራሱ ምንም ማድረግ የማይችል፣ ሲቸገር ወደ አምላኩ የሚጣራ፣ሲሞት በፈጣሪ የተቀሰቀሰ፣ ከፍጥረታት በኩር፣ ነገሮች ሁሉ ከጊዜ በኋላ የተሰጠው ከሆነ እንዴት እርሱ ዘላለማዊው አምላክ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል?

72. መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ኢየሱስ በስቅለት ጊዜ የጭንቅ ፀሎት ወደ አምላኩ አሰምቷል:: በክርስቲያኖች የዓለማት ፈጣሪ የሚባለው ክርስቶስ ወደ አምላክ ካለቀሰ የርሱ «አምላክ» መባል ምኑ ላይ ነው ታዲያ?

73. አንድ የክርስትና ጸሐፊ «ክርስቶስ የጸለየው የጭንቅ ጸሎት ነበር:: ክርስቶስ ሰው ከመሆኑ የተነሣ ከመሞቱ በፊት ጸልዩል::»[11] ይላሉ::ነገር ግን ኢየሱስ እንደ ክርስትና እሳቤ «ሰው» ብቻ ነውን? «ሰውም፤ አምላክም» አይደል እንዴ? «አምላኬ! አምላኬ! ስለምን ተውኸኝ» ሲል ምን ነበር? ሰው ወይስ

---

[11] ምሕረቱ ጲ.ጉታ፣መልስ ደናረው ይሆን? ፣ገጽ 55

አምላክ? ምላሽዎ «ሰው» ከሆነ የሞተው ኢየሱስ የተባለው ሰው ነው ማለት ነው:: ምላሽዎ «አምላክ» ከሆነ ደግሞ አምላክ «አምላክ» ሲል ሌላኛውን አምላክ ይማፀናልን?

74. የአምላክ ሕልውና በማንም ላይ ጥገኛ አይደለም:: አይሆንምም:: በዮሐንስ 5:26 ላይ መጽሐፍ ቅዱስ «አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታል::» ይላል:: ነገር ግን እንደዚህኛው ጥቅስ ገለጻ የኢየሱስ ህልውና በአብ (አምላክ) ላይ ጥገኛ ነው:: «ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታል::» ይላል:: ወልድ ህልውና (ሕይወት) ያገኘው አብ ስለሰጠው ነው:: የኢየሱስ ሕልውና በአብ ላይ ጥገኛ ነው፤ ኢየሱስ ያለ አብ በራሱ ህልውና ሊኖረው ካልቻለ እንዴት አምላክ ሊሰኝ ይችላል?

75. ፊሊጵስዮስ 2:8-9 ላይ «ሰው ሆኖ ተገልጦም፣ ራሱን ዝቅ አደረገ፣ እስከ ሞት ያውም በመስቀል ላይ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ:: <u>ስለዚህ እግዚአብሔር እጅግ ከፍ አደረገው፤ ከስምም ሁሉ በላይ የሆነውን ስም ሰጠው</u>» ይላል:: ኢየሱስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት በከፍተኛ ደረጃ ስልጣን ከነበረው ለአምላክ ታዛዥ በመሆኑ ወደ ነበረበት ደረጃ ይመለሳል ወይስ እንደ አዲስ «ከፍ» ይደረጋል? ይሰጠዋል? ጥቅሱ እንደ አዲስ ስለ ማግኘቱ እንጂ «ወደ ነበረበት ይመለሳል» አይልም:: አንዱ የሥላሴ ክፍል ሌላኛውን ያዘዋልን? ከፍ ያደርገዋልን? ስጦታ ይሰጠዋልን?

76. ኢየሱስ እኔ «አምላክ ነኝ! ተገዙኝ» ብሏልን? ካለስ የቱ ጋር? ካላለስ ለምን ይገዙታል? ነገ ኢየሱስ «እኔ አምልኩኝ ብዬ መች አስተማርኳችሁ?» ቢልዎ ምን ይመልሱለታል?

77. 1ኛ ጢሞቴዎስ 2:5 ላይ <u>«አንድ እግዚአብሔር አለና፤ ደግሞም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል አንድ አስታራቂ አለ፤ እርሱም ሰው</u>

የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።» ይላል። አምላክ ስንት ነው? አንድ! እርሱም እግዚአብሔር ነው። ኢየሱስስ? ጥቅሱ «ደግሞም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል አንድ አስታራቂ አለ፤» ይላል። እርሱ ማን ነው? ከተባለ «ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።» ይላል። ታዲያ እግዚአብሔር አንድ ከሆነ ኢየሱስ ሰው፤ በአምላክና በሰው መካከል አስታራቂ እንዲሁም አምላክ ይሆናልን? በምን ስሌት ነው ኢየሱስ የተባለውን ሰው አምላክ ልንለው የምንሞክረው?

78. በ1ኛ ቆሮንጦስ 8:5-7 ላይ «መቼም ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች አሉ፤ ነገር ግን በሰማይ ሆነ በምድርም ሆነ አማልክት የተባሉ ምንም ቢኖሩ ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፤ ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን» ይላል። ይህን ጥቅስ ልብ ብለው ካስተዋሉ ክርስቲያኖች እንደሚሉት ከአንድ አምላክ ክፍል የሆኑ «አንድ ጌታ» እና «አንድ እግዚአብሔር» አይልም። ነገር ግን «አንድ አምላክ አብ» ነው የሚለው። ኢየሱስንም በዚህ አንዱ በተባለው አምላክ ውስጥ አልጨመረም። ለብቻው ነው «አንድ ጌታ» የሚለው። ይህ ጌትነት አምላክ ውስጥ ካልተጠራ እንዴት ጌታ ከተባሉ ሌሎች ግለሰቦች ለይተን ኢየሱስን «አምላክ» ልንለው ይቻለናል? «ጌታ» እና «እግዚአብሔር» ማለት አንድ ቢሆኑ ለምንድነው በመጽሐፍ ቅዱስ በበርካታ ስፍራ ሰዎች ኢየሱስን «ጌታ» ሲሉት አንድም ጊዜ «እግዚአብሔር» አልያም «እግዚአብሔር አብ» እንደሚባለው «እግዚአብሔር ወልድ/ኢየሱስ» ያልተባለው? ካልሆነ ለምንድነው አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ በአንድነት በአንዱ አምላክ «እግዚአብሔር» ውስጥ ተካተው ወልድን ያልገለጹት?

## የኢየሱስ መወለድና ጥያቄዎች

79. ዕብራውያን 1:5 «እግዚአብሔር፣ «አንተ ልጄ ነህ፤እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ ፤ ወይስ ደግሞ፤እኔ አባት እሆነዋለሁ፤እርሱም ልጅ ይሆነኛል» ያለው ከመላዕክት ከቶ ለማን ነው?» ይላል። እግዚአብሔር ኢየሱስን «እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ» ሲለው ያኔ ከመወለዱ በፊት እንዳልነበር ግልጽ ነው። «ዛሬ» ፣ «ትናንት» እንዲሁም በአጠቃላይ «ጊዜ» ከተፈጠረ በኋላ ነው «ዛሬ» ሊባል የሚችለው። በኢስላምም ሆነ በክርስትና ሃይማኖት «ጊዜ» ፍጡር እንደሆነ ነው የሚታመነው። ታዲያ እንዴት «ኢየሱስ ዘላለማዊ ነው» ሊባል ይችላል? ከመወለዱ በፊት ነበርን?

80. ኢየሱስ ጅማሬ፣ ፍጥረት እና ውልደት ከሌለው እንደ ክርስትና እሳቤ አንዱ «አምላክ» (ኢየሱስ) «ልጅ/ወልድ» ሲባል ሌላኛው አምላክ (አብ) «አብ/አባት» ተብሏል።ታዲያ ለምንድነው ቅደም ተከተልን በሚገልጽ ቃላት የተጠሩት? «አባት» እና «ልጅ» ቅደም ተከተል ከሌላቸው ለምን እንዲህ ያለ መጠሪያ ኖራቸው? ካልሆነ ስያሜያቸውን መቀያየር እንችላለንን?

81. ማርያም ከማርገዟ በፊት ኢየሱስ ነበርን? ከነበረ የትና እንዴት? እርሷ ከመንፈስ ቅዱስ ስታረግዝ እርሱ የት ነበር? ስታረግዝ ያ የነበረው ጠፋ ሊባል ነው? ወይስ ኢየሱስ እንደሚወለድ የሚገልጽ የአምላክ ቃል ብቻ ነበር? እስቲ በደንብ ያውጠንጥኑት!

82. ከሥላሴዎች አንዱ አብ ለሌላኛው (ለኢየሱስ) አባት ነው ይባላል። ሌላኛው የሥላሴ አባል የሆነው መንፈስ ቅዱስ ደግሞ እናቱ ማርያምን አስፀንሷል (ማቴዎስ 1:1-20፤ሉቃስ 1:35) ታዲያ ኢየሱስ ስንት አባት ነው ያለው?

83. የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 2 ቁጥር 21 ላይ «ሊገርዘት ስምንት ቀን በሞላ ጊዜ በማህጸን ሳይረገዝ በመልአኩ እንደተባለ ስሙም ኢየሱስ ተብሎ

ተጠራ» ይላል። ኢየሱስን የገረዙት ሰዎች ሲገርዙት «የዓለምን ፈጣሪ ኃያሉን አምላክ ገረዝን» ብለው ነበር ያሰቡት? እንደ ክርስቲያኖች እምነት አምላክ የኢየሱስን ስጋ ተዋህዶታል። ያቺ በግርዛት የተቆረጠችው የኢየሱስ ቁራጭ ሥጋስ? የአምላክ ቁራጭ ልትሆን?

84. ማርያም አርግዛ ሳለ «ኢየሱስ» የሚለውን ስያሜ እንደምታወጣለት ተገልጿል። በእርሷ ይህንን ስያሜ ከመሰጠቱ በፊት እውን ኢየሱስ ከነበረ ማን ነበር ስሙ?

85. በሉቃስ ወንጌል 2፥41-48 ላይ «ዮሴፍና ማርያም በየዓመቱ ለፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዱ ነበር። ኢየሱስም አስራ ሁለት ዓመት በሆነውም ጊዜ እንደተለመደው በዓሉን ለማክበር ሄዱ። በዓሉ ከተፈጸመ በኋላ እነርሱ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ቀረ፤ ዮሴፍና ማርያም ግን እዚያ መቅረቱን አላወቁም ነበር። ከመንገደኞች ጋር አብሮ የሚሄድ መስሎአቸው የአንድ ቀን መንገድ ሲጓዙ ዋሉ፤ ከዚያም በኋላ ከዘመዶቻቸውና ከጓደኞቻቸው ዘንድ ይፈልጉት ጀመር። ነገር ግን ሊያገኙት ስላልቻሉ እየፈለጉት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። ከሦስት ቀንም በኋላ በቤተመቅደስ አገኙት። በዚያም በሊቃውንት መካከል ተቀምጦ ሲያዳምጣቸውና ጥያቄ ሲያቀርብላቸው ነበር። የሰሙትም ሁሉ በማስተዋሉና በመልሱ ይገረሙ ነበር፤ ዮሴፍና ማርያም በቤተ መቅደሱ ባዩት ጊዜ ተደነቁ ፤በዚያን ጊዜ እናቱ «ልጄ ምነው እንዲህ አደረግኸን? አባትህና እኔ ተጨንቀን ስንፈልግህ ነበር እኮ!» አለችው» ይላል። ማርያም ልጇ ኢየሱስ የዓለም ፈጣሪ ኀያሉ አምላክ ነው ብላ ታምን ነበርን? አምላክ መሆኑን ብታውቅ «አባትህና እኔ ተጨንቀን ስንፈልግህ ነበር እኮ!» ትል ነበርን? አምላክነቱን ካወቀች ምን ያስጨንቃታል? ታዲያ ወላጅ እናቱ ማርያም ልጇ አምላክ ነው ብላ ካላመነች ክርስቲያኖች እንዴት አምላክ ሊሉት ቻሉ?

86. ክርስቲያኖች እንደሚሉት ኢየሱስ ‹ሰዋዊ› ባህሪውን ከማርያም (ከእናቱ) ‹መለኮታዊ› ባህሪውን ደግሞ ከአባቱ (ከአብ) ነስቶ ተወለደ። ታዲያ አንዱን ባህሪውን ከአባቱ ሌላኛውን ደግሞ ከእናቱ ከነሳ አባቱ እና እናቱ ምን እና ምን ናቸው?

87. ኢየሱስ ያለ አባት በመወለዱ «አምላክ» ከሆነ ያለአባትና እናት የተፈጠረውን አዳም ትልቅ «አምላክ» ልንለው ለምን አልደፈርንም?

88. ማቴዎስ 1፡23 ላይ «እነሆ፣ድንግል ትፀንሳለች፣ወንድ ልጅም ትወልዳለች ፤ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል፣ትርጉሙም፣«እግዚአብሔር ከእኛ ጋር» ማለት ነው።» ይላል።ድንግል ምን ትወልዳለች ተባለ? ወንድ ልጅ! ታዲያ «ድንግል አምላኳን ወለደች» የሚለው ከየት መጣ?

89. ሉቃስ 1፡6-7 ላይ «በዚያም እንዳሉ የምትወልድበት ጊዜ ደረሰ፤ የበኩር ልጅ የሆነውን ወንድ ልጅ ወለደች፤በጨርቅም ጠቀለለችው፤በእንግዶችም ማረፊያ ቦታ ስላላገኙ በግርግርም አስተኛችው።» ይላል። ክርስቲያኖች እንደሚሉት ድንግል አምላኳን ነው የወለደችው? ጥቅሱ «ወንድ ልጅ» ነው የሚለው? ኢየሱስን ስትወልድ ማርያም «አምላኬን ወለድኩ» ብላ ነበር ያሰበችው ወይስ «ወንድ ልጅ»? ታዲያ «ድንግል አምላኳን ወለደች» የሚለው ከየት መጣ? ከገባኤ?

በሐዋርያት ዘመንስ ይህ «ድንግል ፈጣሪዋን ወለደች» የሚለው እምነት ነበርን? ታዲያ ከየት መጣ? ከጉባኤ! የሚከተለው ይህንን ያረጋግጣል፡- <u>ቤተክርስቲያን</u>

<u>በ431 ዓ.ል በኤፌሶን በተካሄደው ጉባኤ ድንግል ማርያም ቴዎቶኮስ (የአምላክ እናት)</u> መሆንዋን እንደ ሃይማኖት ሕግ አወጀች::[12]

## <u>አምላክ ሥጋ ለብሶ ሰው ሆኗልን?</u>

90. በመጽሐፍ ቅዱስ ፈጣሪ ታይቶ እንደማይታወቅ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 6:1፣ 1ኛ ዮሐንስ መልእክት 4:12 ፣ዮሐንስ 1:18፣እና ዮሐንስ 5:57 ላይ ተገልጿል:: ለአብነት ያህል በ1ኛ ጢሞቴዎስ 6:16 ላይ «የተባረከውና ብቻውን ገዥ የሆነው የነገሥታት ንጉሥ፣የጌቶች ጌታ እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ የሚያሳየው ነው፣እርሰ ብቻ የማይሞት ነው፣ሊቀረብ በማይችል ብርሃን ውስጥ ይኖራል፣እርሱን ያየ ማንም የለም፤ ሊያየውም የሚችል የለም:: ለእርሱ ክብርና ኃይል ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን፤ አሜን::» ይላል:: እንዲሁም በዮሐንስ 1:18 ላይ «ከቶውንም እግዚአብሔርን ያየ ማንም የለም::» ይላል:: ኢየሱስ ግን ታይቷል:: ታዲያ አምላክ የማይታይ ከሆነ ኢየሱስ አምላክ እንዳልሆነ አያሳይምን?

91. ክርስቲያኖች «ኢየሱስ አምላክ ነው፣ወደ ምድር የሰው ሥጋ ለብሶ መጥቷል» ይላሉ:: ወደ ሰማይ ከተመለሰ በኋላስ በሥጋ እንዳለ ይቆያል ወይስ አስቀድሞ ነበረ በተባለበት ሁኔታ ይመለሳል? ኢየሱስ የሰው ሥጋን በመተው አስቀድሞ ነበረ ወደ ተባለበት አምላካዊ ሁኔታ ይመለሳልን? መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተገለጸው ግን ኢየሱስ የሰው ሥጋ ለብሶ እስከ መጨረሻው መቀጠሉን እንጂ ሰውነቱን (ሥጋ መልበሱን) እንደሚተው አይናገርም! ታዲያ አንዱ የሥላሴ አባል ኢየሱስ እስከ መጨረሻ ሰው ነውን?

---

[12] ኢየሱስ ክርስቶስ የሕያው አብ ቃል እና የዓለም መድኃኒት፣በኢት/ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የጽ/ጠ/ጽ/ቤት ሐዋርያዊ ሥራ መምሪያ የተዘጋጀ ፣አዲስ አበባ፣ማስተር ማተሚያ ቤት፣ገጽ 159

92. ዕብራውያን 2:17 ላይ «ስለዚህ በሁሉም ነገር ወንድሞቹን መምሰል ተገባው፤» ይላል፡፡ታዲያ ክርስቲያኖች እንደሚሉት ኢየሱስ በሁሉም ነገር እንደኛ ከሆነ፣ እንዴት ፍፁም (100%) ሰው እንደዚሁም ፍፁም (100%) አምላክ ይሆናል? እንደኛ ሲሆን እኛስ ፍፁም አምላክ ልንሆን ነው ማለት ነውን?

93. ኢየሱስ ተርቧል፤ ደክሞታል፤ ተጨንቋል፤አርዳታ ጠይቋል ፤ሸሽቷል። በአጠቃላይ በርካታ የሰው ባሕሪያት ታይተውበታል። ታዲያ ይህን ሁሉ ሲያደርግ ሰው ነበር ወይስ አምላክ? አምላክ ከነዚህ ሁሉ የጠራና ፍፁም መሆኑ ግልፅ ነው። ታዲያ ይህን ሲያደርግ ኢየሱስ ሰው ነበር? ሌላ ጊዜ ደግሞ አምላክ ነበርን? አንዴ ሰው ሌላ ጊዜ አምላክ እየሆነ ተለዋወጠ? በሚልክያስ 3:6 ላይ «እኔ እግዚአብሔር አልለዋወጥም» ይላል። ታዲያ የሚለዋወጥ እንዴት አምላክ ይሆናል? አምላክ የማይቀያየር ከሆነ እንዴት ኢየሱስ አንዴ ሰው ሌላ ጊዜ አምላክ ይሆናል?

94. አንድ የክርስትና እምነት ጸሐፊ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡- «ምንም እንኳ የእስልምና ሃይማኖት ባይቀበልም፣ ለክርስቶስ ፍጹም አምላክ መሆንና ፍጹም ሰው መሆን ከተልዕኮው አኳያ እጅጉን አስፈላጊ ነው። የክርስቶስ ዋና ተልዕኮ ደግሞ የሰው ልጅን ከኃጢአታቸው ማዳን በመሆኑ ምንም እንኳን ክርስቶስ ሁለት ባህርያት አሉት ማለት ለሰው አእምሮ ከበድ ያለ ነገር መስሎ ቢታይም እግዚአብሔር በሁሉን ቻይነቱ ያደረገው የክርስቶስ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው መሆን እውነት ነው፡፡» [13]

[13] ምህረቱ ሲ. ጉታ፣ መልስ ደናረው ይሆን? ሌስ ላይ ሌም ማተሚያ ቤት ታተመ፣ 4ኛ ዕትም ፣ 1998፣ ገጽ 63

ሀ) እንዴት ኢየሱስ «ፍፁም ሰው ፍፁም አምላክ» ይሆናል? እንዴት ሁለት ነገር ፍፁም ይኮናል? አንድን ሰው «ከሰዎች ሁሉ ረጅሙ እርሱ ነው። አጭሩም እርሱ ነው።» ማለት ይቻላልን?

ለ) «ኢየሱስ ፍፁም ሰውም ፍፁም አምላክም ነው» ከተባለ ይህ አስተሳሰብ ከሎጂክ አንፃር ብቻ ሳይሆን ከመጽሐፍ ቅዱስም ጭምር የሚጋጭና የማያስኬድ ነው። አምላክ ፍፁም ኃያል፣ ሁሉን አዋቂ፣ ፍፁም ጥበበኛ ነው። ሰው ደግም በተቃራኒው ኃያል ያልሆነ፣ ሁሉን የማያውቅ፣ፍፁም ጥበበኛ ያልሆነ ነው። «አምላክ ፍፁም ሰው ፍፁም አምላክ ነው» ማለት፡- «አምላክ (ኢየሱስ) ሁሉን አዋቂ የሆነና ሁሉን አዋቂ ያልሆነ ነው። አምላክ ኃያል የሆነና ኃያል ያልሆነ ነው። አምላክ ፍፁም ጥበበኛ የሆነና ፍፁም ጥበበኛ ያልሆነ ነው» ማለት ነው።ይህ ትርጉም የሚሰጥ ነውን?

ሐ) የሆነ ነገርን «ፍፁምም ነው፤ ፍፁምም አይደለም» ማለት ልክ የሆነን ነገር «ይህ ነገር ክብም አራት ማዕዘንም ነው፤» እንደ ማለት ነው። «ክብ ነው» ስንል «አራት ማዕዘን አይደለም ማለት ነው»። «አራት ማዕዘን ነውም» ስንል «ክብ አይደለም» ማለታችን ነው። ስለዚህ ሁለት የማይገናኙትን ባህርያት ሁለቱንም በአንድ ጊዜ ፍፁም መሆን ይችላልን?

መ) ሁለት ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን በአንድነት ነው ማለት በፍፁም የማይሆን ነው።ለምሳሌ «አምላክ አለ» ብንል አንድ ዐረፍተ ነገር ነው።«አምላክ የለም» ብንል ደግሞ ሌላ ተቃራኒ ዐረፍተ ነገር ነው።ሁለቱም ትክክል ሊሆኑ በፍፁም አይችሉም።ክርስቲያኖች እንደሚሉት «ሁለት ተቃራኒ ነገሮች በአንድነት ሊኖሩ ይችላሉ» ብንልና «አምላክ አለ፤እንደዚሁም አምላክ የለም።» ብንል፣ሁለት ተቃራኒ ዐረፍተ ነገሮች ናቸው።«አምላክ ሁሉን ቻይ ስለሆነ ምን አለበት፣ሊኖርም ላይኖርም ይችላል። ምን ይሳነዋል?» ማለት ይቻለናልን?

95. ዮሐንስ 1:1 ኢየሱስን «አምላክነት» ይገልፃል ብለው ያምናሉን? «በመጀመሪያ ቃል ነበር። ቃልም እግዚአብሔር ዘንድ ነበር። ቃልም እግዚአብሔር ነበር።» ይላል። «እርሱም በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ነበር!» (ዮሐንስ 1:2)

ሀ) «በመጀመሪያ» ሲባል የምን መጀመሪያ? ለመሆኑ አምላክ መጀመሪያ አለውን? እንዴት «በመጀመሪያ» ይባላል? ዘላለማዊ አይደለምን?
ለ) «የአምላክ ቃል» የሚባለው ኢየሱስ ክርስቲያኖች እንደሚሉት «ዘላለማዊ ነው» ከተባለ እንዴት «መጀመሪያ» ይኖረዋል?
ሐ) በዮሐንስ 1:1 በሦስተኛው ዐረፍተ ነገር ቃልና እግዚአብሔር አንድ መሆናቸው ተነግሮናል! «ቃል» በሚለው ምትክ «እግዚአብሔር»ን ብንተካ «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ነበር! እግዚአብሔርም እግዚአብሔር ዘንድ ነበር!እግዚአብሔርም እግዚአብሔር ነበር!» ይሆናል።የትኛው እግዚአብሔር ነው እግዚያብሔር ዘንድ የነበረው? አእምሮን መጠቀም አይሻልምን? ኧረ እባካችሁ እናስብ !!

96. 1ኛ ቆሮንቶስ 15:29 ‹‹ትንሳኤ ከሌለማ ለሞቱ ሰዎች ብለው የሚጠመቁት ምን እያደረጉ ነው? ሙታን ከቶ የማይነሱ ከሆነ፣ ሰዎች ለእነርሱ ብለው ለምን ይጠመቃሉ?›› ይላል።እነማን ናቸው ‹ለሞቱ ሰዎች› ብለው የሚጠመቁት? ክርስቲያኖች ‹ለሞቱ ሰዎች› ብለው ነው እንዴ የሚጠመቁት? ወይስ ምን? እነማንስ ናቸው?

97. ሮሜ 11:26 ‹‹ስለዚህ እስራኤል ሁሉ ይድናሉ፣›› ይላል። እስራኤላውያን ግን ያኔ በኢየሱስ ዘመንም ሆነ ዛሬ በኢየሱስ ክርስቶስ አላመኑም። የአይሁድ እምነት(ጁዳይዝምን) ተከታይ ናቸው።ታዲያ በኢየሱስ ሳያምኑ ዳኑ? ወይስ ጥቅሱ ውሸት ነው?

98. ከአብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ከወጡ አብ ከሁለቱ መቀደሙ ግልጽ ነው፡፡ ታዲያ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሳይወጡ እርሱ (አብ) ብቻ አልነበረንም? ከነበረስ ታዲያ እንዴት ሦስቱም (አብ፣ ወልድና መንፈቅ ቅዱስ) ‹እኩል ለዘላለም ነበሩ› ይባላል?

99. ሔዋን የተከለከለችውን ዛፍ በመብላቷ አምላክ ቅጣት አዘዘባት፡፡ በወሊድ ጊዜ በስቃይ ትወልድ ዘንድ፡፡ዘፍጥረት 3:16 «ሴቲቱንም እንዲህ አላት፤ «በምጥ ጊዜ ጭንቅሽን አበዛለሁ፤በሥቃይም ትወልጃለሽ፤ ፍላጎትሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፤እርሱም የበላይሽ ይሆናል፡፡» ይላል፡፡በዚህ ጥቅስ ላይ የክርስቲያን ምሁራን እንዲህ ሲሉ ማብራሪያ ጽፈዋል፡- «ሔዋንና ሴቶች ተፈረደባቸው፡፡ከዚህ የተነሳ ልጅ መውለድ አስጨናቂ ሂደት ሆነ፡፡ሴቶች ከባሎቻቸው ጋር የነበራቸው የእኩልነት ግንኙነት ተለውጦ ለባሎቻቸው የሚገዙ ሆኑ፡፡»[14] እንደ ክርስትና እምነት አዳምና ሔዋን ባጠፉት ጥፋት ምክንያት የደረሰባቸውን ኃጢአት(«የዉርስ») ኢየሱስ መስዋዕት ሆኖ በደሙ ከዝርያቸው ላይ አንጽቷል፡፡ይህ አስተምህሮት እውነት ከሆነ ታዲያ በዚያው ጥፋት ምክንያት ሔዋን ላይ የተጣለው ቅጣት(ጭንቅና ስቃይ) አሁንም ለምን ቀጠለ? ወይንስ «ኢየሱስ ለኛ ሲል ቤዛ ሆነ» የሚባለው ሐሰት ነው?

100. እንደ ዘፍጥረት 3:13 ሔዋን ያሳሳታት እባብ መሆኑን «እባብ አሳሰተኝና በላሁ» ስትል ተናግራለች፡፡እግዚአብሔር አምላክ እባብን እንዲህ አለው፡- «ይህን ሥራ ሠራህ፤ «ከከብቶችና ከዱር እንሰሳት ሁሉ ተለይተህ የተረገምህ ሁን፤ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ፤ በደረትህ እየተሳብህ ትሄዳለህ፤ ዐፈርም ትበላለህ፡፡»(ዘፍጥረት 3:14) የክርስትናው ጸሐፊ ቲም ፊሉስ

[14] ቲም ፊሉስ፣የብሉይ ኪዳን የጥናት መምሪያና ማብራሪያ፣1ኛ መጽሐፍ፣ገጽ 126

በዚህ ጥቅስ ላይ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡- «እባብ ተፈጥሮው ተለዉጦ በሆዱ የሚሳብ ሆነ፡፡ በእባብ ተመስሎ የቀረበው ሰይጣን ተፈርዶበት የመጨረሻ ሽንፈቱ ተነገረ፡፡»[15]

ሀ) «በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ...፤ዐፈርም ትበላለህ፡፡» እንደተባለው እባብ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ አፈር ይበላልን?

ለ) እባብ እንዴት አድርጎ ሄዋንን አሳሳተ? ወይንስ ሰይጣን በእባብ ተመስሎ አሳታት?

ታዲያ ሰይጣን በእባብ ተመስሎ ካሳታት፣ ለምን እባብ «ይህን ሥራ ሠራህ፤ «ከከብቶችና ከዱር እንስሳት ሁሉ ተለይተህ የተረገምህ ሁን፤በሕይወት ዘመን ሁሉ፤በደረትህ እየተሳብህ ትሄዳለህ፤ ዐፈርም ትበላለህ፡፡» ተብሎ ተረገመ? ባልሰራው ኃጢአት?

## የኢየሱስ አስተምህሮት ምን ነበር?

1. ኢየሱስ አምላክ ከሆነ ለምንድነው በዮሐንስ 10:29 ላይ «እነርሱን የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፡፡» እንዲሁም በዮሐንስ 14:28 «ብትወዱኝስ አብ ከእኔ ስለሚበልጥ ወደ አብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር፤» ያለው? እንደዚሁም በዮሐንስ 13:16 እና 1ኛ ቆሮንቶስ 11:3 ላይ አምላክ ከኢየሱስ እንደሚበልጥ ተገልጿል፡፡ ከአምላክ የሚበልጥ ሌላ አምላክ አለን? ወይስ ኢየሱስ «ትንሹ አምላክ» ነው? አብ ከእርሱ እንዳሚበልጥ ኢየሱስ ሲናገር ክርስቲያኖች ግን «በፍፁም እኩል ናቸው» ይላሉ፡፡ ታዲያ ኢየሱስ ይህን ሲናገር እየዋሸ ነውን? ወይስ ክርስቲያኖች ናቸው የዋሹት? ኢየሱስ ክርስቶስ «አብ ከእኔ ይበልጣል» ሲል ሰብዓዊ ማንነቱን ብቻ የሚመለከት እንጂ «በመለኮታዊ ባህሪ ደረጃ ግን እኩል ናቸው» ብሎ ማሰብስ የቋንቋ አጠቃቀም ሥርዓትን ትርጉም ማሳጣት አይሆንምን?

---

[15] ቲም ፌሎስ፣ የብሉይ ኪዳን የጥናት መምሪያና ማብራሪያ፣1ኛ መጽሐፍ፣ገጽ 126

2. ኢየሱስ ለምንድነው በዮሐንስ 8:28 ላይ «ከራሴ ምንም ላደርግ አይቻለኝም» ያለው? ታዲያ እንደሚሉት ኢየሱስ አምላክ ሆኖ ከራሱ ምንም ማድረግ የማይችል ከሆነ ምንም ማድረግ የማይችል አምላክ አለ ልንል ነውን? ወይስ የሰው ሥጋ ስለለበሰ? ታዲያ በመጽሐፍ ቅዱስ አንድም ሥፍራ «ኢየሱስ ካረገም በኃላ ሥጋውን ይተዋል» አይልም።ታዲያ እስከ መጨረሻ ምንም ማድረግ ለማይችለው ኢየሱስ ፍፁማዊ አምላክነትን ልንሰጥ እንዴት ይቻለናል?

3. ኢየሱስ በማርቆስ 10:18 ላይ «ስለ ምን ቸር ትለኛለህ?» በማለት «ቸር» ለመባል ካልፈለገ እንዴት አምላክ ይባላል? ኢየሱስ ቸር መባል እንደሌለበትና «ቸር» አንዱ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ካስተማረ፣ ይህ ብቻ አምላክ አለመሆኑን አይገልፅምን? «ቸር» መባልን እንዲህ ከተቃወመ «ከአምላክ እኩል ነው» የሚለውን ቢሰማ እንዴት ይቆጣ ይሆን?

4. በመጽሐፍት አንድም ስፍራ ላይ አምላክ «አንድ» እንጅ «ሦስትም አንድም» ሳይባል መጠቀሱ፣ «አምላክ አንድም ሦስትም» የሚለው ንግግር መጽሐፍ ቅዱሳዊ አለመሆኑን አያሳይምን?

5. እውነተኛ አምላክ ማን ነው? ኢየሱስ ነውን? ኢየሱስ ምን አለ? <u>«እውነተኛ አምላክ የሆንኸውን አንተንና የላክኸውንም ኢየሱስን ያውቁ ዘንድ...»</u> (ዮሐንስ17:3)። እውነተኛው አምላክ ኢየሱስን የላከው መሆኑን ኢየሱስ ተናግሮ ሳለ እንዴት ኢየሱስ አምላክ ይባላል? ከርሱ አስተምህሮት በላይ የማን ንግግር ይታመናል? ወይስ ኢየሱስ «እውነተኛ አምላክ የሆነውን ሥላሴን» ብሎ አስተማረ? ታዲያ ኢየሱስ ሥላሴ እውነተኛ አምላክ ቢሆን ለምን አይገልጽም ነበር?

6. ሉቃስ 6:46-49 ላይ <u>«እኔ የምለውን አታደርጉም፣ታዲያ ለምን ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! ትሉኛላችሁ?</u> ወደ እኔ የሚመጣ፣ቃሌንም ሰምቶ የሚፈፅም ሁሉ

ማንን እንደሚመስል ላሳያችሁ። ቤት ለመሥሪያ አጥልቆ የቆፈረና በዓለት ላይ መሠረቱን የመሠረተን ሰው ይመስላል፣ጐርፍ በመጣ ጊዜ የውሃው ሙላት ያን ቤት ገፋው፣ በሚገባ ስለ ታነፀም ሊያነቃንቀው አልቻለም። <u>ቃሌን ሰምቶ የማይፈፅም ግን ቤቱን ያለመሠረት በዓፈር ላይ የሠራን ሰው ይመስላል</u>፣ የወንዙ ሙላትም ቤቱን በመታው ጊዜ ወዲያው ወደቀ፣ ክፉኛ ም ፈራረሰ።» ይላል።

ክርስቲያኖች ኢየሱስ ያስተማረውን ትተው ተቃራኒውን ያምናሉ፣ ይፈጽማሉ። እንዲህም ሆኖ «ጌታችን! ጌታችን!» ይሉታል። ኢየሱስ ግን እንዲህ ብሎ ነበር «እኔ የምለውን አታደርጉም፤ታዲያ ለምን ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! ትሉኛላችሁ?» (ሉቃስ 6:46) ክርስቲያኖች እውን የኢየሱስን ቃል እየተከተሉ ነውን? ወይስ «ሐዋርያ ነኝ» ያለውን የጳዉሎስን አስተምህሮትና ቃል ነው እየተከተሉ ያሉት?

7. የዮሐንስ ወንጌል 11:38-43 ላይ «ኢየሱስ ልቡ ዳግመኛ በሀዘን ተነክቶ ወደ መቃብሩ መጣ፤ መቃብሩም በድንጋይ የተገጠመ ዋሻ ነበር፤ እርሱም፤ «ድንጋዩን አንሱት» አለ። የሟቹም እኀት ማርታ፤ ጌታ ሆይ፤ አሁንማ አራት ቀን ስለቆየ ይሸታል» ኦላችው። ኢየሱስም <u>«ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ክብር ታያለሽ ብዬ አልነገርሁሽምን?»</u> አላት። ስለዚህ ድንጋዩን አነሡ። ኢየሱስም ወደላይ ተመልክቶ እንዲህ አለ «<u>አባት ሆይ፤ ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ። ሁልጊዜም እንደምትሰማኝ ዐውቃለሁ፤ ይህን መናገሬ ግን በዚህ የቆሙ ሰዎች አንተ እንደላከኸኝ ያምኑ ዘንድ ነው።</u>» ኢየሱስ ይህን ካለ በኋላ በታላቅ ድምፅ «አልዓዛር፤ና ውጣ!» ብሎ ተጣራ። የሞተውም ሰው እጅና እግሩን በቀጭን ስስ ጨርቅ እንደተጠቀለለ፤ ፊቱም በሻሽ እንደ ተጠመጠመ ወጣ። ኢየሱስም «መግነዙን ፍቱለትና ይሂድ» አላቸው።» ሲል ተገልጿል። ተዓምሩ የማን ነው? ኢየሱስ ጸልዮ «ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ» በማለት ፀሎቱ መሰማቱን ገለፀ። ተዓምራቱ የርሱ ነው በሚል እንዳይታሰስ ፀሎቱን ማሰማቱን ለምን እንደተናገረ ሲገልፅ «ይህን መንገሬ ግን በዚህ የቆሙ ሰዎች አንተ እንደ ላከኝ ያምኑ ዘንድ ነው»

ብሎ ነበር።ታዲያ ኢየሱስ አምላኩን ለምኖ ተዓምር ቢያደርግ ምን ያስገርማል? አምላክ ከዚህ የበለጠ ላሻው መስጠት አይችልምን? ይህንን ተዓምር ያየችው የሟቹ እህት ማርታ ተዓምሩ የራሱ ኢየሱስ መሆኑን አምና ነበርን? ኢየሱስስ ቢሆን «ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ክብር ታያለሽ ብዬ አልነገርሁሽምን?» አይደል ያላት። ታዲያ ምነው አምላክ ነው ማለታችን?

8. ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፦ «ሕግንና የነቢያትን ቃል ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ለመፈፀም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም።» (ማቴዎስ 5:17) እንዲሁም «እውነት እላችኋለሁ፤ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ሕግ ሁሉ ይፈፀማል እንጂ ከሕግ አንዲት ፊደል ወይም አንዲት ነጥብ እንኳን ቢተላለፍ፤ ሌሎችንም እንዲተላለፍ ቢያስተምር በመንግሥተ ሰማይ ታናሽ ተብሎ ይጠራል፤ ነገር ግን እነዚህን ትእዛዛት እየፈፀመ ሌሎችም እንዲፈፅሙ የሚያስተምር በመንግስተ ሰማይ ታላቅ ይባላል።»(ማቴዎስ 5: 18-19) ይላል።ትዕዛዛትን እየፈፀመ እንዲፈፀም የሚያስተምር ሰው ነው በመንግስተ ሰማያት ታላቅ የሚባለው። ግን ክርስቲያኖች «በኢየሱስ ለሰው ኃጢአት ቤዛ መሆኑን ያመነ ሰው ነው መንግስተ ሰማያትን የሚገባው» ይላሉ። ትዕዛዛትን መፈጸም አስፈላጊ እንዳልሆነ ሁሉ የሚያስተምሩ ክርስቲያኖችም አሉ። ታዲያ ኢየሱስ ያለው ውሸቱን ነበርን? ወይንስ እንዲህ የሚሉት ክርስቲያኖች ናቸው የዋሹት?

9. ዮሐንስ 17:26 ላይ መጽሐፍ ቅዱስ «ለእኔ ያለህ ፍቅር በእነርሱ እንዲሆን፤እኔም በእነርሱ እንድሆን፤ ስንተን እንዲያውቁ አድርጌአለሁ፤ እንዲያውቁህም አደርጋለሁ።» ይላል። ኢየሱስ «ስንተን እንዲያውቁ አድርጌአለሁ» ሲል ነቢይ እንደመሆኑ የርሱ ተግባር ስለ አምላክ ለሕዝቡ ማሳወቅ መሆኑን ገለጸ። ይህም ብቻ ሳይሆን ወደፊትም ስለ አምላክ የማሳወቁን ሥራውን እንደሚቀጥልበት «እንዲያውቁህም አደርጋለሁ።» ሲል የአምላክ ታማኝ አገልጋይ መሆኑን አረገግጧል። ታዲያ ኢየሱስ የአምላክ

አገልጋይና ሕዝቡ ስለ አምላክ እንዲያውቅ ማድረግ ተግባሩ ከሆነ እንዴት ራሱ አምላክ ሊሰኝ ይችላል?

10. በማቴዎስ 12፡49-50 ላይ «በእጁም ወደ ደቀ መዛሙርቱ እያመለከተ እንዲህ አለ፤ እናቴና ወንድሞቼ እነዚህ ናቸው። በሰማይ ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፤ወንድሜ፤እህቴና እናቴም ነው።» ይላል።ታዲያ የአምላክን ትዕዛዝ የሞላ ሰው የኢየሱስ እህትና ወንድም ከሆነ እርስዎም የአምላክ እህትና ወንድም ሊሆኑ ነዋ? ወይስ የእምነት ወንድምና እህት ለማለት ነው? እንዲያማ ከሆነ የኢየሱስ እምነት የሐዋርያት እምነት ነው ማለት ነው። ታዲያ ክርስቲያኖች «ኢየሱስ አምላክ ነው» ስለሚሉ አምላክ ሃይማኖትን ይከተላል፤ አማኝ ነው ማለት ነውን? ገነት የሚገባው የራሱን ፈቃድ የሚደርገው ሳይሆን «በሰማይ ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ» ነው በማለት የአባቱን ፈቃድ የፈጻሙትን መሆኑን ሲገልጽ ሐዋርያቶች እርሱ ማን መሆኑን ያውቁ ዘንድ ፈልጎ ይሆንን?

11. በማርቆስ 11፡20-23 ላይ «በማግስቱ ጠዋት በመንገድ ሲያልፉ፤ በለሲቱ ከነሥሯ ደርቃ አዩ። ጴጥሮስ ነገሩ ትዝ አለውና ኢየሱስን፤ «መምህር ሆይ! እነሆ፤የረገምሃት በለስ ደርቃለች» አለው። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤«በእግዚአብሔር እመኑ፤እውነት እላችኋለሁ፤ማንም ይህን ተራራ፤ ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር» ቢለውና ይህንንም በልቡ ሳይጠራጠር ቢያምን ይሆንለታል።» የሚል ጥቅስ ተገልጿል። ኢየሱስ ለምን እንዲህ አለ? ጴጥሮስ የኢየሱስ እርግማን መፈጸሙን በመገረም ሲነግረው፣ እንዳይገረምና እርሱም እንዴት ሊፈጸምለት እንደቻለ አይደል ሊገልጽ የፈለገው? ኢየሱስ «በእግዚአብሔር እመኑ፤እውነት እላችኋለሁ፤ ማንም ይህን ተራራ፤ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር» ቢለውና ይህንንም በልቡ ሳይጠራጠር ቢያምን ይሆንለታል።» ሲል ራሱ በማመኑ እርግማኑ መሳካቱን ገልጿል። ታዲያ በእግዚአብሔር የሚያምነው ኢየሱስ ራሱ አምላክ ነው ሊባል ይችላልን?

12. ማርቆስ 10:13-14 ላይ «ኢየሱስም እንዲዳስሳቸው፣ ሰዎች ሕፃናትን ወደርሱ አመጡ፤ ደቀ መዛሙርቱ ግን ገሠጿቸው፤ ኢየሱስም ይህን ሲያይ ተቆጥቶ እንዲህ አላቸው፡- «ሕፃናት ወደ እኔ ይምጡ፤አትከልክሏቸው፤ የእግዚአብሔር መንግስት እንደነዚህ ላሉት ናትና።›› ይላል። የውርስ ኃጢአት አሳቤ እንደሚለው ደግሞ ሰው ሁሉ ሲወለድ ከኃጢአት ጋር ነው። ይህ እውን ቢሆን ኖሮ ኢየሱስ ሕፃናት ከነውርስ ኃጢአታቸው ለምን ‹የእግዚአብሔር መንግስት እንደነዚህ ላሉት ናት› አለ? ሕፃናቱ ራሳቸውን አውቀው ገና ‹በማመን› የውርስ ኃጢአታቸውን አላስተሰረዩ? በዚህም ላይ ደግሞ ኢየሱስ ይህን የተናገረው ገና ተሰቀለ ከመባሉ በፊት ስለሆነ እንዴት የህፃናቱን ንፁህነት ገለፀ? ለመሆኑስ የውርስ ኃጢአት የሚባል ነገር ለአእምሮ አይጎረብጥምን?

13. ዮሐንስ 14:6 «ኢየሱስም እንዲህ አለው፡- ‹መንገዱ እኔ ነኝ፤ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ፤ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።›› ይላል።አንዳንድ ክርስትያኖች ይህን ጥቅስ ለኢየሱስ ‹አምላክነት› መከራከሪያ አድርገው ያቀርባሉ። ኢየሱስ ‹መንገዱ እኔ ነኝ› አለ እንጂ ‹መድረሻ ነኝ› መች አለ? መንገድ አድራሽ ነው እንጂ መድረሻ አይደለም። ነቢያት ሁሉ ያስተምራሉ፤ወደ አምላክ ጥሪ ያደርጋሉ።ማንም ገነት ለመግባት የግድ የነቢያቱን መንገድ መከተል አለበት። ወደ አምላክ የሚያደርሱ መንገድ ናቸው።ታዲያ ኢየሱስ ‹አምላክ ነኝ› መች አለ? ኢየሱስ በዘመኑ ብቸኛ የአምላክ መንገድ ነው።ያለርሱ መንገድነት በቀር (እርሱን ከመከተል ውጭ) ማንም ወደ አምላክ አይቀርብም። ኢየሱስ በግልጽ «በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።›› ብሏል። ታዲያ ክርስቲያኖች ምነው ይህን መመርመር አቃታቸው?

14. ማርቆስ 15:37 ‹‹ኢየሱስ በታላቅ ድምጽ ጮኸ፤ ነፍሱን ሰጠ።›› ይላል። ለመሆኑ ነፍሱን ለማነው የሚሰጠው? ራሱ ለራሱ ነው ወይስ ሰጪውና ተቀባዩ የተለያዩ ናቸው?

15. ማቴዎስ 3:17 ‹‹እነሆ፣‹በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው <u>ልጄ</u> ይህ ነው› የሚል ድምጽ ከሰማይ ተሰማ።›› ይላል። እዉን ይህ ከሰማይ የተሰማው ድምጽ የአምላክ ነውን? አምላክ ‹ልጅ አለኝ› ይላልን? ‹‹ይህ ከሰማይ የተሰማው ድምጽ›› የአምላክ ድምጽ አለመሆኑ እንዴት ይታወቃል? ኢየሱስን ‹የምወደው ልጄ› እያለው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ኢየሱስ ከዚህ ክስተት በኃላ በዮሐንስ 5:37 እንዲህ ብሏል፦ ‹‹የላከኝ አብ ራሱ ስለ እኔ መስክሮአል፤ <u>*እናንተ ከቶ ድምጹን አልሰማችሁም!*</u> መልኩንም አላያችሁም።›› ኢየሱስ እንዳለው የአብን (የአባቱን) ድምጽ ከቶ ካልሰሙ ፣ ያ ድምጽ እውን ተሰምቷልን? ከሆነስ የማን ድምጽ ነው? የአሳሳቹ ሰይጣን ቢሆንስ?

16. ዮሐንስ 5:20 ‹‹አብ ወልድን ስለሚወድ <u>የሚያደርገውን ሁሉ ያሳየዋል</u>፤ ትደነቁም ዘንድ ከእነዚህም የሚበልጥ ነገር ያሳየዋል።›› ይላል። ታዲያ አምላክ ኢየሱስን የሚያደርገውን ቢያሳየውምና ተዓምር ቢያደርግ ምን ይገርማል? አምላክ ከዚህ በላይ ማድረግ አይችልምን? በግልጽ ለኢየሱስ አምላክ ‹‹የሚያደርገውን ሁሉ ያሳየዋል›› ተብሎ የለምን?

17. ዮሐንስ 5:26-27 ‹‹አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው ሁሉ፣ወልድም በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና፤<u>ወልድ የሰው ልጅ ስለሆነም</u> እንዲፈርድ

ሥልጣን ሰጥቶታል::›› ይላል:: ወልድ ሕይወት እንዴት ሊኖረው ቻለ? ጥቅሱ ‹ወልድም በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና› ይላል!

አብ የወልድ ሕይወት ምንጭ አይደለምን? ክርስትያኖች እንደሚሉት ወልድ (ኢየሱስ) የመፍረድ ሥልጣን ያገኘው አምላክ ስለሆነ ነውን? ጥቅሱ ወልድ ‹አምላክ› ስለ ሆነ ነው ይላልን? በፍፁም! ‹‹<u>ወልድ የሰው ልጅ ስለሆነም</u> እንዲፈርድ ሥልጣን ሰጥቶታል::›› ነው የሚለው::ሳይሰጠው በፊትስ? ታዲያ ክርስቲያኖች ምነው ቆም ብለው ቢያስተነትኑ?

## <u>‹የሚስጢረ ሥላሴ› ሚስጢር</u>

1) የሥነ-መለኮት ምሁር የሆኑት ዶክተር ፓውል እንዝ «ታሪካዊ ሥነ-መለኮት አመጣጡና ትንተናው» በሚለው መጽሐፋቸው ላይ «የኒቅያው (Nicea) ጉባኤ በ325 ዓ.ም ታሪካዊውን አስተምህሮ-ሥላሴ አፀደቀ:: <u>በዚህም መሠረት ክርስቶስ ከአብ ጋር የባሕሪይ እኩልነት ያለው መሆኑ ግንዛቤ አገኘ::»</u>[16] ሲሉ ጽፈዋል:: በኒቅያው ጉባኤ መሠረት «ክርስቶስ ከአብ ጋር የባሕሪይ እኩልነት ያለው መሆኑ» ግንዛቤ ሳያገኝ በፊት ቤተክርስቲያን የሥላሴን እምነት ሳይሆን የአንድን አምላክ ኃያልነትና ብቸኝነት ሥታስተምር ተሳስታ ነበርን? ከኒቂያ ጉባኤ በፊት የነበሩት አማኞችና ሐዋርያትና የኢየሱስን በባህሪ ከአብ ጋር መስተካከል ሳይረዱትና ግንዛቤውን ሳያገኙ ቆይተው በኒቂያ ጉባኤ ተገኝተው በድምጽ ብልጫ የወሰኑት 300 ጳጳሳት ግንዛቤውን አገኙን? እምነት የሚጸድቀው እንደፖለቲካ ፓርቲ በጉባኤ ነው ወይስ በአምላክ ትእዛዝ?

2) ዶክተር ፓውል እንዝ ከላይ በጠቀስነው መጽሐፋቸው ላይ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል:- «በአርዮስ ትምህርት የተነሳ የተፈጠረውን ውዝግብ ለመፍታት

---

[16] ዶክተር ፓውል እንዝ፣ታሪካዊ ሥነ-መለኮት አመጣጡና ትንተናው፣በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት የታተመ፣1993፣አዲስ አበባ፣ገጽ 13

በ325 ዓ.ም ኒቅያ በተባለው ስፍራ አንድ ጉባኤ ተካሄደ። በጉባኤው ላይ 300 ጳጳሳት ተገኝተው ነበር። ጉባኤው አርዮስንም ሆነ አርዮሳዊነትን የሚቀበሉትን ሁሉ አውግዟል። በንጉሱ ካስፀደቀ በኋላም የሚከተለውን የሃይማኖት መግለጫ አወጣ፡-

<u>«ሁሉን በሚችል፣ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ፣ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን። የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በአንዱ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ፣ ከአብ ብቻውን በተገኘው ከአብ ጋር መገኛው («ኡሲያስ»/ousias) አንድ በሆነው፣ ከአምላክ በተገኘው አምላክ፣ ከብርሃን በተገኘ ብርሃን፣ ከእውነተኛ አምላክ በተገኘ እውነተኛ አምላክ ፣ በተፈጠረ ሳይሆን በተወለደ፣ ከአብ ጋር በማንነት (homoousion) አንድ በሆነ፣ሁሉ በእርሱ በሆነ ፣ በሰማይም ይሁን በምድር ባለው፣ ለእኛ ለሰው ልጆች ደህንነት ወርዶ ሥጋ በሆነ፣ ሰውም በሆነ፣ መከራን በተቀበለበት በሦስተኛ ውም ቀን በተነሳ፣ ወደ ሰማይ ባረገ ፣በሙታንና በሕያዋን ላይ ሲፈርድ በሚመጣው እናምናለን።»[17]</u>

ሀ) ይህ የኒቂያ ጉባኤ ራሱ «በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።» እንጂ አንድ እግዚአብሔር በሚሆኑት በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን።» እንደማይል አስተውለዋልን?

ለ) በዚህ መግለጫቸው ኢየሱስን «*<u>ከአምላክ በተገኘው አምላክ</u>*» ሲሉት መጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ የሌለውንና ኢየሱስ ራሱ ያላስተማረውን በመግለጫቸው ስላካተቱ እውነት ይሆናልን? «*<u>ከአምላክ በተገኘው አምላክ</u>*» ሲሉም የተገኘ መሆኑን አምነዋል።ነገር ግን መልሰው ያልተገኘውን ኢየሱስን (እንደነርሱ አባባል) «አምላክ» አሉት።አምላክ ሕልዉናው ዘላለማዊ ነው። ኢየሱስ ግን የተገኘ ነው።የተገኘና ዘላለማዊ ያልሆነው ኢየሱስ «አምላክ» ስለተባለ ብቻ አምላክ ሊሆን ይችላልን?

[17] ዶክተር ፓውሎ እንዝ፣ታሪካዊ ሥነ-መለኮት አመጣጡና ትንተናው፣ገጽ33-34

ሐ) «ኢየሱስ የተወለደ ነው» ግና አልተፈጠረም ሲሉ፡- «ብተፈጠረ ሳይሆን በተወለደ» ብለዋል:: «ተወለደ» ስንል ከመወለዱ በፊት ነበርን? «ብተፈጠረ ሳይሆን» የተባለበት ምክንያት «ተፈጠረ» ካልን «ፍጡር» እንዳይሰኝ ነውን? «ፍጡር» ስላላልን ፍጡር መሆኑ ይቀራልን?

መ) በመግለጫው እንደተባለው «ለእኛ ለሰው ልጆች ደህንነት ወርዶ ሥጋ በሆነ፣ሰውም በሆነ» ኢየሱስ ለሰው ልጅ ደህንነት ሲል ወርዶ ሥጋ ከሆነ ወደ ሰማይ አርጎ ለምን ሰውነቱን (ሥጋውን) ትቶ ከመውረዱ በፊት ለምንድነው «ነበረ» ወደተባለበት ሁናቴ ያልተመለሰው? መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኃላም ሆነ በእለተ ትንሳኤ ሰው ሆኖ (ሥጋ ሆኖ) እንጅ ቀድሞ በነበረበት ሁናቴ ይመጣል አይልም:: ታዲያ ኢየሱስ ለሰው ልጅ ሲል አምላክነቱን (ባህሪዉን) ሙሉ ለሙሉ ትቶ ሰው (ሥጋ ለባሽ) ሆኖ ቀረ ማለት ነውን?

ሠ) እዉን ኢየሱስ «ብሦስተኛውም ቀን በተነሳ» እንደተባለው በሦስተኛው ቀን ተነስቷልን?

ረ) ይህ የኒቂያ ጉባኤ ስለ እግዚያብሔርና ስለ ኢየሱስ ሲያወሳ «ከአንዱ አምላክ እግዚያብሔር ክፍል ነው፣ራሱም አምላክ ነው» የሚባለውን መንፈስ ቅዱስን ለምን ዘነጋ? እስከዚያ ጊዜ ድረስ የመንፈስ ቅዱስ «አምላክነት» በኒቅያ ጉባኤ ለተሳተፉት 300ዎቹ ጳጳሳት አልታያቸውም ነበርን?

ሰ) የሥላሴ ምስጢር ለምን እስከ አራተኛው ክ/ዘመን ሳይታወቅ ቀረ? ለምንስ በኒቂያ ጉባኤ በማስረጃ ብልጫ ሳይሆን በድምፅ ብልጫ ተወሰነ?

ሸ) የክርስትና ሃይማኖት ጸሐፊው «በነቂያው ጉባኤ የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ ከሥላሴ አካላት የአንዱ የመንፈስ ቅዱስ አስተምህሮ በግልጥ አልተቀመጠም::<u>መግለጫው ያረጋገጠው «በመንፈስ ቅዱስ እንምናለን»</u>

የሚለውን ብቻ ነበር።«የቆስጠንጢኒያው ጉባኤ በ381 ዓ.ም «ጌታ በሆነና ሕይወት በሚሰጥ፣ከአብ በሚወጣና ከአብና ከወልድ እኩል አምልኮን በሚቀበል፣በነቢያትም በተናገረ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን» የሚለውን መግለጫ አውጥቷል።መግለጫው መንፈስ ቅዱስ በህልውና ከወልድና ከአብ ያነሰ ሳይሆን እኩል መሆኑን በፅኑ አረጋግጧል።»[18] ይላሉ። ታዲያ መንፈስ ቅዱስም እንደወልድ ከአብ የሚወጣ ከሆነ መንፈስ ቅዱስም የፈጣሪ ልጅ ነውን? ካልሆነስ ለምን?

3) የክርስቲያን ምሁራን ስለ ሥላሴ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፦ «አስተምህሮተ ሥላሴን አስመልክቶ የነበረው ዋነኛ ችግር ብሉይ ኪዳናዊው የአሃዳዊነት እምነት ነበር። ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር አንድ ነው ከሚለው ትምህርቷ ጋር የክርስቶስን መለኮትነት እንዴት ነው የምትቀበለው? የሚለው ጥያቄ ዋና ነበር። ቤተ ክርስቲያን ገና ከጅማሬዋ የሥላሴን አስተምህሮት በሚመለከት ግልጽ የሆነ ግንዛቤ አልነበራትም።»[19] ክርስቲያኖች እንደሚሉት ቀደምት ነቢያትም ሆኑ ኢየሱስ ስለ ሥላሴ አስተምረው ከነበረ ቤተክርስቲያን እንዴት ግልጥ የሆነ ግንዛቤ አልነበራትም? ክርስቲያኖች ቤተክርስቲያን «በኢየሱስና በሐዋርያት ነው የተመሰረተችው» ይሉ የለ? እነርሱም ግልጽ ግንዛቤ አልነበራቸውም ማለት ነውን?

«አስተምህሮተ ሥላሴን አስመልክቶ የነበረው ዋነኛ ችግር ብሉይ ኪዳናዊው የአሃዳዊነት እምነት ነበር።» ይላል። ታዲያ ክርስቲያኖች ሊከራከሩ እንደሚሞክሩት በብሉይ ኪዳን ዘመን የሥላሴ አስተምህሮት ከነበረ እንዴት ብሉይ ኪዳናዊው አሃዳዊ እምነት ለሥላሴ እምነት ዋና ችግር ይሆናል?

---

[18] ዶክተር ፓውሎ እንዝ፣ታሪካዊ ምን-መለኮት አመጣጡና ትንተናው፣ገጽ 34
[19]ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ፣ገጽ 31

4) ኢሳይያስ 46:9 «እኔ አምላክ ነኝና ሌላም የለምና የቀድሞውን የጥንቱን ነገር አስቡ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ እንደ እኔም ያለ ማንም የለም።» ይላል። ከጥንት ጀምሮ የነበረውን አሀዳዊውን እምነት ወይስ ከኒቂያ ጉባኤ በኋላ የመጣውን የሥላሴን አስተምህሮ እንቀበል? ጥቅሱ ግን «የጥንቱን ነገር አስቡ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ እንደ እኔም ያለ ማንም የለም።» ይላል። ታዲያ ክርስቲያኖች ምን ነካቸው?

5) «አብ»፣«ወልድ» እና «መንፈስ ቅዱስ» የሚሉ ቃላቶችን ስናስብ ስለነርሱ ከተገለጸው ጋር ቃላቶቹ በምናባችን የሚፈጥሩት ምስል አለ። ክርስቲያኖች ሲፀልዩ ለአብነው? ወይስ ለወልድ? ወይስ ለመንፈስ ቅዱስ ነው? «አንዱ አምላክ» ብለው ሲለምኑ ማንን ማለታቸው ነው? የሦስቱ አምሳል ነው ወይስ አንድ አምሳል ነው በዓእምሯቸው የሚመጣው? ወይስ ሦስቱ ተያይዘው አንድ አምሳል ይፈጥራሉ?

6) የማቴዎስ ወንጌል 13:32 «ማንም ሰው በሰው ልጅ ላይ የሚናገረው ክፉ ቃል ይቅር ይባላል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚናገረው ክፉ ቃል ግን በዚህም ሆነ በወዲያኛው ዓለም ይቅር አይባልም።» ይላል። የሥላሴ አቀንቃኞች እንደሚሉት አብ፣ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ሦስቱም አምላክም እኩልም ከሆኑ እንዴት በሰው ልጅ (ወልድ) ላይ የሚነገረው ክፉ ይቅር ሲባል በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚባለው ንግግር ይቅርታ የሌለው ሆነ? ምኑ ላይ ነው ታዲያ እኩልነታቸው?

7) በማቴዎስ 26:39 ላይ ኢየሱስ «አባት ሆይ! ቢቻል ይህ ፅዋ ከእኔ ይለፍ፤ ነገር ግን እኔ እንደምፈልገው ሳይሆን አንተ እንደምትፈልገው ይሁን» ብሏል። ይህ አባባል የኢየሱስ ፍላጎት እና የአብ ፍላጎት ሁለት የተለያዩ መሆናቸው ያስረዳል። ታዲያ አብና ወልድ ሁለቱም የአንዱ እግዚአብሔር አካል ከሆኑ እንዴት ሁለት ፍላጎት ኖራቸው?

4) ዮሐንስ 8:29 «የላከኝ እርሱ ከእኔ ጋር ነው፤ምን ጊዜም የሚያስደስተውን ስለማደርግ ብቻዬን አልተወኝም።» ይላል።እውን ኢየሱስ አምላክ ቢሆን ኖሮ ሌላኛውን አምላክ ማስደሰት እንዴት ፈለገ? «ምን ጊዜም የሚያስደስተውን ስለማደርግ ብቻዬን አልተወኝም» ሲል የማያስደስተውን ቢያደርግ ብቻውን ይተወዋል ማለት አይደል? አምላክ ብቻውን እንዳይሆን የሌላኛውን አምላክ (አብ) ውዴታ ይፈልጋልን?

5) ክርስቲያኖች እንደሚሉት ዘፍጥረት 1:26 ላይ «ሰውን በመልካችን ፤ በአምሳላችን እንፍጠር» ሲል ሥላሴን ለማመልከት በሆነ ታዲያ «በአምሳላችን» ሲል ሰው በየትኛው አምሳል ነው የተፈጠረው ሊባል ነው? በአብ፣ በወልድ ወይስ በመንፈስ ቅዱስ? አልያም በሦስቱ አካላት ውህደት ተፈጠረ? ብሉይ ኪዳንን «ጠብቀው አቆዩ» የሚባሉት አይሁዶችስ ይህንንም ሆነ መሰል በሥላሴ በሚያምኑ ክርስቲያኖች ለማስረጃነት የሚቀርቡ ጥቅሶችን ሳይረዱና በሥላሴ ሳያምኑ መጽሐፉን «ጠብቀው አቆዩ» ማለት ያስኬዳልን?

6) እውን ሥላሴ የኢየሱስ አስተምህሮ ከሆነ ይህን ማንም ሊፈታው ያልቻለውን ሚስጢር ኢየሱስ ሳያስተምር (ሳይፈታ)፣ ቃሉን እንኳን አንስቶ ሳይናገር እንዴት አለፈ? በሥላሴ የተነሣ ለዘመናት ክርስቲያኖች ሲጋደሉ ነበር።የክርስትና እምነት ጸሐፊውም እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹ገና ከጅምሩ **ሥላሴ የሚለው ቃል የስነ-መለኮት እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንዳልሆነ ለመግለጽ እንፈልጋለን።››**[20] እንዴት «ሥላሴ» የሚለው ቃል እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልኖረም? የሌለ ነገር የሃይማኖት መሠረት ሆነ ልንል ነውን?

---

[20] ገርሃርድ ኔልስ፣ለሙስሊሞች ጥያቄዎች የክርስቲያኖች መልሶች፣ገጽ 137

7) በሥላሴ ማመን እና በርሱ ስም መጠመቅ ብቸኛ የመዳኛው መንገድ ከሆነ ኢየሱስ ለምን በግልፅ ትኩረት ሰጥቶ አላስተማረበትም? የኢየሱስ ደቀመዛሙርት «ሥላሴ» የምትለውን ቃል ስላልሰሙና በወቅቱ የማትታወቅ ስለነበረች እነርሱም አልዳኑም ማለት ነውን?

8) ስለ ሥላሴ አንድም ማስረጃ በሌለበት የኒቅያን መግለጫ ብቻ በመንተራስ ከራሳችን ምሳሌ እየሰጠን ለማሳመን እንዴት እንጥራለን? ስለ ሥላሴ የምናስረዳው በማስረጃ ነው ወይስ በምሳሌ?

9) 1ኛ ቆሮንቶስ 3:23 «እናንተም የክርስቶስ ናችሁ! ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው።» ይላል። ክርስቶስ የእግዚአብሔር መሆኑ በዚህ ጥቅስ ተገልጿል። ታዲያ «የእግዚአብሔር» እና «እግዚአብሔር» አንድ ናቸውን? እንዲያማ ከሆነ በጥቅሱ መሠረት «እናንተ የክርስቶስ ናችሁ።» ስለተባለ ክርስቲያኖችና ክርስቶስ አንድ ናቸው ማለት ነዋ?

3) «አብ አምላክ ነው! ወልድም አምላክ ነው! መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው። ግን አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት አይባሉም። አብ ጌታ ነው ወልድ ጌታ ነው መንፈስ ቅዱስ ጌታ ነው። ግን አንድ እግዚአብሔር እንጂ ሦስት ጌቶች አይባሉም።» ጉድ! እንደው የሥላሴን ሚስጢር ማን ይሆን የሚፈታው?

4) ሥላሴ የኢየሱስ እውነተኛ አስተምህሮት ከነበረ ለምንድነው አንድም ክርስቲያን ሊፈታው ያልቻለውን ሚስጢር ያን ታላቅ የማስተማር ችሎታውን ተጠቅሞ ኢየሱስ ያላብራራው? ሰዉንም ግራ ከመጋባት «ሁከት» ያልገላገለው?

5)የሥላሴ አስተምህሮ «ምስጢር» ነው ይባላል።ሥላሴ አስተምሮህቱም ሆነ ምስጢርነቱ የቱ ጋር ነው የተገለጸው? የሚገርመው ግን ምስጢር ነው እየተባለ ማስተማሩን ይቀጥሉበታል።ጥያቄ ሲነሳ ግን «ምስጢር ነው» ይባላል። እምነትና አምልኮ ምን ምስጢር ያስፈልገዋል?
6)ኢየሱስ ለዓለም ቤዛ ሆኖ ሰውን ነፃ ለማውጣት ከመጣ ስለ ኢየሱስ ጭራሽ ያልሰሙት ከርሱ መወለድ በፊት የነበሩ ህዝቦች በምን ሊድኑ ነው?

7)የሥላሴ ጽንሰ ሀሳብ ትክክለኛው ገለጻ የትኛው ነው? ከፊል ክርስቲያኖች «ሥላሴ» ከጣኦት አምላኪዎች ወደ ክርስትና የገባና ፈጠራ ነው ብለው ያምናሉ።[21] በሥላሴ ያመኑት አብያተ ክርስቲያናትም ቢሆኑ በትርጉሙ ሳይስማሙ «በሥላሴ ማመን ወሳኝ ነው» ይላሉ።ታዲያ የትኛው አብያተ ክርስቲያን ይሆን ትክክለኛው?

8) ክርስቲያኖች እንደሚሉት ኢየሱስ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ነበርን? ከመወለዱ በፊትስ ነበር ወይንስ አልነበረም? ምላሹ «ነበር» ከሆነ የነበረው ራሱ ከአብ የተወለደ ነው ትሉ የለምን? «አልነበረም» ከሆነ ታዲያ ከጊዜ በኋላ የተገኘ ነገር «ዘላለማዊ» ነው ይባላልን?

9)1ኛ ዮሐንስ 5:7 «መንፈስም እውነት ነውና የሚመሰክረው መንፈስ ነው። የሚመሰክሩት መንፈሱና ዉሃው፤ ደሙም ሦስት ናቸውና፤ ሦስቱም በአንድ ይስማማሉ።» ይላል። እነዚህ ሦስቱ ምስክሮች እኩል ናቸውን? ደም ውሃን ሊተካ ይችላልን? ውሃስ በማንኛውም መልኩ «እንደ መንፈስ ነው» ማለት ይቻለናልን። ልክ መንፈሱ፤ ደሙና ውሃው ሦስት የተለያዩ ነገሮች እንደሆኑት ሦስቱም የመጀመሪያ ምስክሮች እነርሱም አብ፤ ወልድ እና መንፈስ ቅድስ የተለያዩ ናቸውን?

---

[21] የይሆዋ ምስክሮች (ጆሆቫ ዊትነስ)

10) አምላክ «አንድም ሦስትም ነው» የሚል አንድ ጥቅስ እንኳ ማቅረብ ሳንችል እንዴት በሰው አመለካከት ላይ ተንተርሰን አምላክን «ሦስትም አንድም» ልንለው ይቻለናል?

11) ክርስቲያኖች «አምላክ ነው» የሚሉት «ዘላለማዊው ልጅ» (ወልድ) «ሰው» ከሆነና አብና መንፈስ ቅዱስ ካልተለዋወጡ ኢየሱስ ይህን የመሰለ ድንቅ ነገር ለምን ሳይናገር ቀረ?

12) የሥላሴ ፅንስ ሀሳብ ፈጠራ ሳይሆን ዘላለማዊ ከነበረ ኢየሱስን አብ «ዛሬ ወለድሁህ» ሳይለው በፊት ኢየሱስ ነበርን? መንፈስ ቅዱስስ ከአብ ሳይወጣ በፊት ነበርን? ሥላሴስ ነበርን?

13) ኢየሱስ ከማርያም ሳይወለድ በፊት ስለሥላሴ ማብራራት ይቻላልን? እስቲ የወልድን ሁኔታና የአካሉን ገጽታ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ብቻ አስደግፈው ያብራሩ:: ይችላሉን?

14) ብሉይ ኪዳንን ብንፈትሽ ኢየሱስ ከአብ ስለ መወለዱ አይገልፅም:: አምላክ እንደሚወልድም እንዲሁ:: በክርስትና ነው ይህ ያለው:: ታዲያ ይህ አስተምህሮቱ በአዲስ ኪዳን ዘመን የተፈጠረ መሆኑን አያሳይምን?

15) እውን አብ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት አንድ ልጅ (ወልድን) ወልዶ ከነበረ ይህን የሚመስል «ድንቅ» ነገር እንዴት አንዱም ነብይ እንኳን ሳያስተምር አልያም አንዴም ቢሆን ሳይናገር አለፈ? ለምንስ ነው በብሉይ ኪዳን ይህንን የሚመለከት አስተምህሮ ያልተገኘው?

16) ለንድ የክርስትያን ጸሐፊ ስለ ሥላሴ ሦስቱ አካላት እንዲህ ይላሉ፡- «ከሦስቱ አካላት እያንዳንዱ አካል በገጹ ፍጹም ነው። በሦስቱ አካላት ውስጥም መገዛዛት አንዱም ከአንዱ የሚያንስበት በማዕረግ መለኮት አንዱ ከሁለተኛው በልዩ የሚታይበት አንዱም ለሁለተኛው እንደ መልዕክተኛ አድርጎ በስልጣኑ የሚያዝበት ሁኔታ የለም። ነገር ግን በአንዱ መለኮት በአንዱ አገዛዝ በአንድ ክብር ሁሉን የሚችል የብርሃን ልዕልና አንድ ናቸው»[22] መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደሆነ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡- «ነገር ግን የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ፣ የሴትም ራስ ወንድ፣ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደሆነ ልታውቁ እወዳለሁ» (1ኛ ቆሮንቶስ 11:3)

ታዲያ እግዚአብሔር የክርስቶስ (ወልድ) ራስ እንደሆነ እየተገለጸ ለምን ይዋሻል? በተጨማሪ በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ የሚያገኟቸው በርካታ ጥቅሶች እግዚያብሔር የኢየሱስ (ወልድ) የበላይ እንደሆነ ያስረዳሉ። ታዲያ እውነታውን መቃረን ለምን አስፈለገ?

17) የክርስቲያን ምሁራን ስለ ሥላሴ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡- *«አብ ያለ ወልድና ያለ መንፈስ ቅዱስ ለዓይን ቅጽበት የምታህል ጊዜ እንኳ ፈጽሞ አልነበረም። ወልድም ያለ አብና ያለመንፈስ ቅዱስ ለዓይን ቅጽበት የምታህል ጊዜ እንኳ ፈጽሞ አልነበረም። መንፈስ ቅዱስም ያለ አብና ያለወልድ ለዓይን ቅጽበት የምታህል ጊዜ እንኳ ፈጽሞ አልነበረም። ነገር ግን ሥሉስ ቅዱስ የተካከሉ ሆነው ዘወትር ለዘለዓለም ያለ መነሻና ያለ ፍጻሜ ነዋሪዎች ናቸው።»*[23]

[22] መሠረተ ስብሐት ለአብ፣ ሥላሴ በተዋህዶ፣ አዲስ አበባ፣1988 ዓ.ም፣ ብርሃንን ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ፣ገጽ 284
[23] ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ፣ገጽ 284

ሀ) አብም ሆነ ወልድ ከመጀመሪያ (ለዘላለም) ከነበሩ እና አንዱ ሌላኛውን የማይቀድም ከሆነ ለምንስ አንደኛው «አባት» ሌላኛው «ልጅ» የሚል የተለያየ መጠሪያ ኖራቸው?

ለ) ለምን ሁለት የተለያዩ ቅድም ተከተልን የሚገልጹ ስያሜዎች ኖራቸው?

ሐ) አንድ ከሆኑ ስያሜያቸውን ልንለዋውጥ እንችላለንን? እንደ ክርስትና አስተምህሮት ወልድ ከአብ ተወልዷል። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ከአብ ወጥቷል። ወልድ ከአብ ሳይወለድና መንፈስ ቅዱስ ከአብ ሳይወጣ አብ ብቻውን ነበር ወይስ ከሁለቱም ጋር? በዕብራውያን 1:5 ላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔር ኢየሱስን (ወልድን) «እግዚአብሔር፣ «አንተ ልጄ ነህ፤ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ» ከማለቱ በፊት ማለትም «ዛሬ» ከተባለችው ቀን በፊት ኢየሱስ ነበርን?

18) መሠረተ ስብሐት ለአብ «ሥላሴ በተዋሕዶ» በተሰኘው መጽሐፋቸው «አብ ልጁን ወልዶታል፤ ነገር ግን ይህን ጊዜ ወይም እንደዚህ ባለ ቀን ወለደው አይባልም። ከአብ መወለዱ ድንቅ ነው ሀላዌውም አይታወቅም ስውር ነውና»[24] ሲሉ ጽፈዋል።በዕብራውያን 1:5 ላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔር ኢየሱስን (ወልድን) «እግዚአብሔር፣«አንተ ልጄ ነህ፤እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ» ከማለቱ በፊት ማለትም «ዛሬ» ከተባለችው ቀን በፊት ኢየሱስ ነበርን? ስለዚህ ኢየሱስ የተወለደው «ዛሬ» በተባለችው ቀን ነው። «ዛሬ ትናንት ነገ» ወዘተ ብለን ጊዜ አመላካች ቃላትን መጠቀም የምንችለው «ጊዜ» ከተፈጠረ በኃላ ነው። ጸሐፊው «ይህን ጊዜ ወይም እንደዚህ ባለ ቀን ወለደው አይባልም።።» በማለት ከጊዜ ዉጭ የሆነ ለማስመሰል ጥረዋል። ታዲያ ኢየሱስ ከአብ «ዛሬ» በተሰኘችው ቀን ከተወለደ «ጊዜ» ፍጡር ስለሆነ ኢየሱስ የተወለደው በጊዜ ውስጥ ነው። ስለዚህ ኢየሱስ ፍጡር ከሆነው «ጊዜ» መፈጠር በኃላ ነው የተወለደው። ታዲያ ኢየሱስ ፍጡር ነው ወይስ ፈጣሪ?

---

[24]ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ፣ገጽ 327

19) ‹ሐዋርያው› የሚባለው ጳዉሎስ እንዲህ ብሏል፦ ‹‹ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም፤ይህም እግዚአብሔር በነጻ የሰጠን እናውቅ ዘንድ ነው።››(1ኛ ቆሮንቶስ 2፡12) እንደ ሥላሴ አስተምህሮት መንፈሱም (መንፈስ ቅዱስም) እግዚአብሔር ነው። እንደዚህ ጥቅስ ‹ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ› ሲል ‹መንፈስ› በሚለው ምትክ ‹እግዚአብሔር› የሚለውን ከተካን (አንድ ናቸው ስለተባለ) ‹ከእግዚአብሔር የሆነውን እግዚአብሔር› የሚል ይሆናል። ታዲያ ስንት እግዚአብሔር ነው ያለው?

20) ዮሐንስ 1፡14 ‹‹ቃልም ሥጋ ሆነ፤›› ይላል። እንደክርስቲያኖች እምነት ‹‹ቃል›› አምላክ ነው። ታዲያ አምላክ ሥጋ ሆነ ማለት ነው?

21) የሐዋርያት ሥራ 12፡24 ‹‹የእግዚያብሔር ቃል ግን እንደገና እየሰፋ ሄደ።›› ይላል። እንደ ክርስትና አስተምህሮት ‹‹ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቃልና ራሱም አምላክ ነው››። የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ አምላክ ከሆነ እንደዚህኛው ጥቅስ የእግዚአብሔር ቃል እያደገና እየሰፋ ሄደ ማለት ነው። ታዲያ ይህ የሚመስል ነውን?

## <u>‹ለኃጢአታችን ሲል ተሰቀለ፤ዳነን›!</u>

‹‹ኢየሱስ ተሰቅሏል›› የሚለው እምነት ለመልስ አዳጋች የሆኑ አያሌ ጥያቄዎችን ያስነሳል። አንዳንዶቹንም እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል፦

1. ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ መስጠቱ ወንጀል ነውን? ለመሆኑ ማን እንደ ይሁዳ መልካም ሠራ? እርሱ ኢየሱስን አሳልፎ ባይሰጠው ይሰቀል ነበርን? ታዲያ በኢየሱስ መሰቀል ክርስቲያኖች «ዳንን» ይሉ የለ? ይህ ሁሉ

ክርስቲያን «ገነት እንዲገባ» ምክንያት የሆነው የይሁዳ ሥራ አይደለምን? ታዲያ ይወገዝ ወይንስ ይወደስ? እንደ ክርስትና አስተሳሰብ ሰው ሁሉ የዳነውና ከገሃነም ነጻ የሆነው በኢየሱስ መሰቀል ነው:: ታዲያ እንደ ክርስትና አስተምህሮት ክርስቲያን ሁሉ በይሁዳ ትከሻ ላይ አይደል ገነት የገባው?

2. በማቴዎስ 9:13 ላይ «ከመስዋዕት ይልቅ ምህረትን እወዳለሁ» ይላል:: አምላክ «ከመሥዋዕት ይልቅ ምህረትን እወዳለሁ» እያለ እንዴት ዓለም በሠራው ኃጢአት ምህረት ማድረግ ሲችል ኢየሱስን በማስቃየት መስዋእት አደረገው?

3. «እግዚአብሔር ወልድ» ሞቷልን? ክርስቲያኖች «አዎን» ይላሉ? ታዲያ አምላክ (እግዚአብሔር) ይሞታል? የአምላክ ክፍልና አካል ይሞታል? እንዲያው አንዴም ቢሆን መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስን «እግዚአብሔር ወልድ» ብሏልን? እስቲ የቱ ጋር?

4. ከ2000 ዓመት በፊት ኢየሱስ ለሰው ልጆች ኃጢአት ቤዛ ሆኖ ከተሰቀለ፣ ዛሬም ከስቅሉ በኋላ እንዴት «የሰው ልጆች ሁሉ በኃጢአት ዉስጥ ናቸው» ይባላል?

5. ኢየሱስ ለዓለም ቤዛ ሆኖ ሰውን ነፃ ለማውጣት ከመጣ ስለ ኢየሱስ ጭራሽ ያልሰሙት ከርሱ መወለድ በፊት የነበሩ ሕዝቦች በምን ሊድኑ ነው?

6. ምንም ቢሠሩ ሁሉም ክርስቲያኖች በኢየሱስ መሰቀል በማመን ብቻ መንግሥተ ሰማያት የሚገቡ ከሆነ የኢየሱስ አስተምህሮት ምኑ ላይ ነው ጥቅሙ? ኢየሱስ «መልካም»፣«እኩይ» እያለ ሲያብራራቸው የነበሩት አስተምህሮቶቹ ሁሉ ምን ይፈይዳሉ? «ይፈይዳሉ» ካላችሁ በኢየሱስ

መስቀል አምነው ኢየሱስ «ከፉ» ያላቸውን ተግባራት ቢፈጽሙና ባይፀፀቱ ገሃነም ይገባሉ ማለት ነውን?

7. ክርስቲያኖች ‹ወደር የለሹና የማይቀየረው አምላክ በመስቀሉ ላይ ስቃይና ሞትን ተቀብሏልን?› የሚል ደረቅ ጥያቄ ሲቀርብላቸው መልሳቸው «የክርስቶስ ሰብዓዊ ሕሊናና ነፍስ ነው የሞትን ጣዕር የቀመሰው እንጂ መለኮታዊ ገጽታው አይደለም» የሚል ነው:: ታዲያ በምን ዓይነት ሁናቴ ነው ወደር የለሽ የሆነው አካል ለኛ ሲል ስቃይና ሞትን ተቀብሏል ለማለት የደፈሩት?

8. ኢየሱስ መስቀል ላይ ሆኖ «አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ?» ብሎ ሲለምን አምላክ ነበር ወይስን ሰው? ሰው ከሆነ የሞተው ኢየሱስ የተባለው ግለሰብ ነበር ማለት ነው::እንዴትስ አምላክ ሌላ አምላክ ይለምናል? የማይሞተው እግዚአብሔር አምላክ ሞተ ይባላልን?

9. ዮሐንስ 13:33 «ልጆቼ ሆይ! ከእናንተ ጋር የምቆየው ለጥቂት ጊዜ ነው፤ እናንተም ትፈልጉኛላችሁ፤ ለአይሁድ፤ «እኔ ወደምሄድበት ልትመጡ አትችሉም» እንዳልኳቸው፤አሁን ለእናንተ ይህንኑ እላችኋለሁ::» ይላል:: በዚህ ጥቅስ ላይ ኢየሱስ ለአይሁዶች «እኔ ወደምሄድበት ልትመጡ አትችሉም» ብሏል::ታዲያ እንዴት ያለበት ድረስ መጥተው «ያዙት» ፤«ሰቀሉት» ሊባል ቻለ? ወይስ ኢየሱስ ዋሸ? አልያም እንደሚያዝ አያውቅም ነበርን?

10. ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ «በዘጠኝም ሰዓት ኢየሱስ፤ «ኤሎሄ፤ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ ትርጓሜውም «አምላኬ ፤ አምላኬ፤ ለምን ተውኸኝ?» ማለት ነው::» (የማርቆስ ወንጌል 15:34 እና ማቴዎስ 27:46) ሲል አምላክ ከስቅላቱ እንዲያድነው በጩኸት ለምኗል:: በማቴዎስ 26:53 ላይ «ካስፈለገ አባቴን ብጠይቀው ከዐስራ ሁለት ክፍል

ሰራዊት የሚበልጡ መላእክት የማይሰድልኝ ይመስልሃል?» ሲል ኢየሱስ ተናግሮ ነበር፡፡ ታዲያ ኢየሱስ «አምላኬ፣ አምላኬ፣ ለምን ተውኸኝ?» ብሎ በጩኸት እየለመነ፣ እንዴት የተባለው ጦር መጥቶ ከስቅለት ሳያድነው ቀረ?

11. ሉቃስ 22:36 «እርሱም እንዲህ አላቸው፣ «አሁን ግን ኮሮጆም ከረጢትም ያለው ሰው ይያዝ፣ ሰይፍ የሌለውም ልብሱን ሽጦ ይግዛ፡፡» ይላል፡፡ ኢየሱስ በዚህ ጥቅስ ላይ «ሰይፍ የሌለውም ልብሱን ሽጦ ይግዛ» ብሏል፡፡ለምን? በሰይፍ እንዳይሰቀል እንዲከላከሉለት? ሊሰቀል «መጣ» የተባለው ሰው እንዴት ሃሳቡን ሊቀይር ቻለ?

12. ማቴዎስ 4:17 «ከዚያ ዘመን ጀምሮ ኢየሱስ፡- መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ፣ እያለ ይሰብክ ጀመረ፡፡» ይላል፡፡ ክርስትና መንግስተ ሰማያትን ለመውረስ «ኢየሱስ ለኛ ሲል ተሰቅሎ መሞቱን ማመን ግዴታና ብቸኛው መዳኛ ነው» ሲል ያስተምራል፡፡ ኢየሱስ «መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» በማለት ከሚሰብክ ብቸኛው መዳኛ እርሱ ለሰው ልጅ ኃጢአት ቤዛ ሆኖ መሰቀሉንና መሞቱን ማመን ከሆነ «መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና እኔ ለናንተ ተሰቅዬ ልሞት መሆኑን እመኑ» በማለት እንዴት ሳይሰብክ ቀረ?

13. በመዝሙር 34፥17 ላይ፡- «ቅኖች» ወደ እግዚአብሔር ይጮኻሉ፣ እርሱም ይሰማቸዋል፣ ከችግራቸውም ሁሉ ያድናቸዋል፡፡» ይላል፡፡ ታዲያ «አምላኬ አምላኬ ስለምን ተውከኝ?» እያለ ኢየሱስ ሲጮህ «ቅን» ስላልሆነ ነው ያልተሰማው? ከሞትስ ያልዳነው? ወይስ ቅን ስለሆነ ከሞት ድኗል?

14. ማቴዎስ 8፥17፣ ኢሳይያስ 53፥12፣ ኢሳይያስ 53፥4፣ ሉቃስ 2፥30፣ ኢሳይያስ 52፥10 እና ሉቃስ 22፥32 ላይ «ይመጣል» ተብሎ የተተነበየው መሲህ ኢየሱስ ከነበረ ይህ መሲህ እንደማይገደልም ተገልጿል፡፡ ታዲያ እንዴት ኢየሱስ «ሊገደል ቻለ» ተብሎ ይታመናል?

15. የሰው ልጅ አዳም በፈጸመው ኃጢአት ምክንያት ኃጢአት የመሥራት ዝንባሌንና ባህሪን ከወረሰ እንዲሁም ይህ ዝንባሌ በኢየሱስ ስቅላት በደሙ ከነጻ፣ ለምን ያ ዝንባሌ አሁንም ቀጥሎ ሰው ወንጀልን እየሰራ ሊቀጥል ቻለ?

16. ሉቃስ 22:44 «እጅግ ተጨንቆ በብርቱ ይፀልይ ነበር፤ ላቡም እንደ ደም ነጠብጣብ ወደ ምድር ይፈስ ነበር::» ይላል:: እንዲሁም «ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዝናለች፤» (ማቴዎስ 26:38) ይላል:: በዚህ ጥቅስ ላይ ኢየሱስ ነፍሱ እስከ ሞት ድረስ እጅግ ማዘኗን እየገለፀ ነው:: ኢየሱስ እጅግ ተጨንቆ ነበርና ላቡም እንደ ደም ነጠብጣብ ወደ ምድር ይፈስ ነበር::

ሀ) ግን ለምን ይህ ሁሉ? ክርስቲያኖች እንደሚሉት ኢየሱስ «አምላክ» አይደለም እንዴ? አምላክ ሞትን እሱ ፈጥሮት እንዲህ ይፈራዋልን?

ለ) ቢሞት እንኳ እንደ ክርስትና እምነት ከሦስት ቀናት በኋላ ይነሳል:: ታዲያ ስንት ሞትን ሳይፈሩ በዚያው ሊቀሩ መስዋእት የሆኑ ጀግኖች አሉ አይደል እንዴ? ታዲያ ምነው ኢየሱስ ይህን ያህል መጨነቁ? ይህስ ባህሪ የአምላክ ነቢይ ባህሪ ነውን?

17. የክርስትና እምነት መሠረቱ «ኢየሱስ ለኛ ኃጢአት ሲል ሞተ፤ ለኃጢአታች ቤዛ ሆነ::» ነው:: ነገር ግን «ቤዛ» ተብዬው በራሱ እኔ ለኃጢአታችሁ ቤዛ እሆናለሁ፤ ኃጢአታችሁን በደሜ አጥባለሁ::» ሲል አስተምሮ ነበርን? የሚል ጥያቄ ቢነሣ ምላሹ አሳፋሪ ነው:: አንዴም አላስተማረም:: ይህ የጳውሎስ ፈጠራና ተጽዕኖ ብቻ ነው:: እንዲያውም እንዳይያዝና እንዳይገደል ሲፀልይ፤ ሲደበቅና ሲጨነቅ ነበር:: አልነበረምን?

18. ኢየሱስ ከአብረሃም ልጅ ያንሳልን? አምላክ አብረሃምን ልጅህን እረድ ሲለው ታዛዥ ሆኖ ሊታረድ ቀረበ:: ኢየሱስ ዓለምን የማዳን ተልዕኮ ይዞ

ከተሰቀለ፣ ከሦስት ቀናት በኋላ እንደሚነሳ እያወቀ ያ ሁሉ መሸሸና መሸበር ይገባው ነበርን?

19. እንደ ክርስቲያኖች አስተሳሰብ ኢየሱስ ለሰው ልጅ ኃጢአት ሲል ተሰውቶ ከሦስት ቀናት በኋላ ነፍሱ ተመልሶለታል:: መስዋዕትነቱ ጊዜያዊ ነበር ማለት ነው:: ምክንያቱም ሰው መስዋዕት ሲያደርግ መስዋዕቱን መልሶ አይወስድም፤ ኢየሱስ ግን ወሰደ:: ከሰው መስዋዕት ያንስ ነበርን?

20. ማቴዎስ 52+53 «መቃብሮችም ተከፍተው ሞተው ከነበሩት ብዙ ቅዱሳን ሰዎች ከሞት ተነሡ:: ከመቃብርም ወጡና ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ በኋላ ወደ ቅድስት ከተማ ወደ ኢየሩሳሌም ገቡ፤ በዚያም ለብዙ ሰዎች ታዩ::» ይላል:: እነዚህ ሰዎች በኋላ የት ገቡ? ይህን እጅግ አስገራሚ ትዕይንት ሊሆን የሚችል ነገር ለምን ሌሎች ወንጌል ጸሐፊዎች ሳይፅፉት ቀሩ? ይህ ክስተት ተፈጽሞ ቢሆን ኖሮ ከኢየሱስ ተዓምር ይተናነስ ነበርን? በዚሁ ሰበብ ብቻ ከከሀዲያን የሚያምን ሰው ይኖር ሁሉ አልነበረምን? ሰዎችስ ሞትና ወዲያኛው ዓለም ምን እንደሚመስል ይጠይቋቸው አልነበረምን? ይገልጹስ አልነበረምን? ሰዎች በትንሳኤ ከሙታን ይቀሰቀሳሉ የተባለው ሳይደርስ መቀስቀሳቸውን ለሰው እንዴትስ አብራሩት?

21. ኢየሱስ የሰየረው የውርስ ኃጢአትን ነው ወይስ በየጊዜው የሚፈፀምን ኃጢአት? ምላሹ የውርስ ከሆነ በየጊዜው ለፈፀሙት ኃጢአቶች ክርስቲያኖች ሊቀጡ ነው ማለት ነው:: ምላሹ ለሁለቱም ከሆነ «መልካም ስራ» መስራት እንደሚገባ የሚያስተምሩ ጥቅሶች ፋይዳቸው ምንድነው?

22. ለሰው ኃጢአት የተሰዋው አምላክ ከሆነ እንዴት አምላክ ራሱን ለራሱ ይሰዋል? ወይስ ከሦስቱ አንዱ ነው ለሁለቱ የሚሰዋው?

23. አምላክ አዳምን እንዲሁ መማር እየቻለ ለምን የኢየሱስ ደም እንዲፈስ ፈለገ? ደም ማፍሰስ የፈጣሪ ባህሪ ነውን?

24. በዮሐንስ 19፥32-36 ላይ «ስለዚህ ወታደሮቹ ሄደው ከኢየሱስ ጋር የተሰቀሉትን ሰዎችን ጭን ሰበሩ፤ ወደ ኢየሱስ በሄዱ ጊዜ ግን እርሱ ቀደም ብሎ እንደሞተ አይተው ጭኑን አልሰበሩም። ነገር ግን ከወታደሮቹ አንዱ ጎኑን በጦር ወጋው፣ ወዲያው ከጎኑ ደምና ውሃ ወጣ። ይህንን ያየ፣ እናንተ እንድታምኑ መሰከረ፤ ምስክርነቱም እውነት ነው፣ የሚናገረውም እውነት እንደሆነ እርሱ ያውቃል። ይህም የሆነው «ከእርሱ አንድ አጥንት እንኳ አይሰበርም» የሚለው የመጽሐፍ ቃል እንዲፈጸም ነው» ይላል። «ትንቢት» የተባለው የሚከተለው ነው «ደግ ሰው በብዙ መከራ ይፈተናል፤ እግዚአብሔር ግን ከዚህ ሁሉ ያድነዋል። እግዚአብሔር በጥንቃቄ ስለሚጠብቀው ከአጥንቶቹ አንዱ እንኳ አይሰበርም» (መዝሙር 34፥19-20)

ሀ. የሞተ ሰው ቢወጋ ደም ይፈሰዋልን ?

ለ. ትንቢቱ «እግዚአብሄር ግን ከዚህ ሁሉ ያድነዋል» ይላል።ግና በተቃራኒው ክርስትና እንደሚለው ኢየሱስ ሳይድን ሞቷል። ታዲያ ጸሐፊው ለምን ያለመሞቱን ትቶ የአጥንቱን አለመሰበር ብቻ ተረከልን?

ሐ. ወይስ ትንቢቱ በትክክል ሳይፈጸም ቀረ?

25. ዕብራውያን 5:8-10 «የእግዚአብሔር ልጅ ቢሆንም እንኳ፣ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ። በዚህም ፍፁም ሆኖ ከተገኘ በኃላ፣ እርሱን ለሚታዘዙ ሁሉ የዘላለም ድነት ምክንያት ሆነላቸው። እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመትም ሊቀ ካህናት ተብሎ በእግዚአብሔር ተሾመ።» ይላል። በዚህ ጥቅስ ኢየሱስ እንደ መልከ ጼዴቅ ሊቀ ካህናት ተብሎ መሾሙ ተገልጿል። ሳይሾም በፊትስ ምን ነበር? ኢየሱስ የዘላለም ድነት ምክንያት የሆነው በርሱ ለሰው ኃጢአት መሰቀል ላመኑት ነው ወይንስ እርሱን ለታዘዙት? ጥቅሱ የሚለው «ለሚታዘዙ ነው»። ታዲያ ክርስቲያኖች ትዕዛዛቱን ጥለው በጳውሎስ

አስተምህሮት ተመርተው «የዘላለም ሕይወት እንገኛለን» በማለት ለምን ተቃረኑ?

26. የዮሐንስ ወንጌል 7:33-34 ‹‹ኢየሱስም እንዲህ አለ፦ ከእናንተ ጋር የምቆየው ጥቂት ጊዜ ነው፤ ከዚያም ወደ ላከኝ እሄዳለሁ፤ *ትፈልጉኛላችሁ፤ ግን አታገኙኝም፤ ወዳለሁበትም ልትመጡ አትችሉም።*›› ይላል። ኢየሱስ ‹ከእናንተ ጋር የምቆየው ጥቂት ጊዜ ነው፤ ከዚያም ወደ ላከኝ እሄዳለሁ፤› አለ እንጂ ‹ከዚያም በኋላ ይዛችሁ ትሰቅሉኛላችሁ፤ ከዚያም በሦስተኛ ቀን እነሳለሁ፤ከዚያም ወደ ላከኝ እሄዳለሁ፤› እንዳላለ ልብ ብለዋልን? ምናልባት ‹‹‹ከዚያም ወደ ላከኝ እሄዳለሁ› ብቻ ማለቱ ፍጻሜዉን በአጭሩ ለመግለጽ ነው›› የሚል የዋህ ክርክር ሊነሳ ይችላል። ኢየሱስ ተይዞ፣ ተፈርዶበት ፣ተሰቅሎ ሞቶ፣ ከዚያም ወደላከው የሚሄድማ ከሆነ ‹ትፈልጉኛላችሁ፤ግን አታገኙኝም፤ ወዳለሁበትም ልትመጡ አትችሉም።›› ማለቱ ትርጉም አልባ አልሆነምን? ወይስ ኢየሱስ እንደሚያዝ አያውቅም ነበር?

27. ኢየሱስ በዮሐንስ 18:37 ላይ ‹‹እኔ ንጉስ እንደሆንኩ መናገርህ ትክክል ነው፤ የተወለድሁት፣ ወደዚህ ዓለም የመጣሁት ስለ እውነት ለመመስከር ነው፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ይሰማኛል።›› ብሏል። ኢየሱስ በዚህ ጥቅስ ‹የተወለድኩት› በማለት ስለራሱ መናገር መጀመሩ ምንን ያመላክታል? የርሱ ሕልውና ከመወለዱ ጋር የጀመረ መሆኑን አያሳይምን? ኢየሱስ ከእናቱ ማርያም ተወልዶ ወደዚህ ዓለም የመጣው ለምንድነው? ክርስቲያኖች እንደሚሉት ለሰው ልጅ ኃጢአት ቤዛ ሊሆን ነውን? እርሱ ግን ምን አለ? ‹‹ወደዚህ ዓለም የመጣሁት ስለ እውነት ለመመስከር ነው፤›› ታዲያ ክርስቲያኖች ምነው ኢየሱስን ተቃረኑ?

28. ሰው ገነት የሚገባው በኢየሱስ በማመን ብቻ ከሆነ ለምን ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 7:8-16 ላይ ያላመነ ሚስት/ባል ያለው ሰው በአመነው ምክንያት ገነት እንደሚገባ ተናገረ?

29. ኦርቶዶክሶች ከነርሱ ውጭ ያሉ ክርስቲያኖችን «መናፍቃን» ይላሉ:: ፕሮቴስታንቶችም ከፕሮቴስታንት ውጭ ያሉትን «አማኝ» አድርገው አይወስዱም:: ካቶሊኮችም፣ ጆሆቫዎችም፣ ሁሉም ክርስቲያን ከራሱ ቡድን ውጭ ያለውን ትክክለኛ አማኝ አድርጎ አያይም:: የራሱን ቡድን ብቻ የገነት አድርጎ ያስባል::በዚህ አካሄድ ከ33 ሺህ የክርስትና አይነቶች ውስጥ የትኛው ነው ትክክለኛው?

30. እግዚአብሔር ለኃጢአታችን ሲል ሞቷልን? የማይሞተው አምላክ ሞተ? ከአምላክ ባህሪ ውስጥ አንዱ አለመሞት ነበር:: ሲሞት ይህንን ባህሪውን ተፃርሮ ነውን? ታዲያ ከሞተ ምኑን አምላክ ሆነ?

31. አምላክ ነው መስዋዕት የሆነው ወይንስ «ልጁ»? ክርስቲያኖች ምን ይላሉ?

32. ኢየሱስ አምላክ ከነበረ እንዴት በሰው ይከዳል? አምላክ በሰው ይከዳልን?

33. አምላክ የሰውን ልጅ ለማዳን የግድ «ሰው» ሆኖ መስዋዕት መሆን ነበረበትን? እንዲሁ በምህረቱ ሊያልፍ አይችልም ነበርን?

34. አምላክ ፍትሃዊ ነው:: ፍትህ ደግሞ በአንዱ ኃጢአት ሌላውን ያለመቅጣትን ይጠይቃል:: «አምላክ እኛን ሊያድን ኢየሱስን መስዋዕት አደረገው» የሚለው አባባል የፍትህን ጽንስ ሀሳብ አይፃረርምን? አንድ ሰው ሌላውን ገድሉ ወይም ወንጀል ፈፅሞ ፍርድ ቤት ቢቀርብና ዳኛው እርሱን በመቅጣት ፋንታ ልጃቸውን ቢቀጡ ፍትሀዊነት ይሆናልን?

35. ሰዎች መስዋእትን ለአምላካቸው ያቀርባሉ። ክርስቲያኖች የሚሉት ደግሞ «አምላክ ኢየሱስን ለኃጢአታችን መስዋት አደረገው» ነው። ታዲያ እግዚአብሔር ኢየሱስን በመስዋዕትነት ለማን ነው ያቀረበው?

36. አብያተ ክርስቲያናት በሚያምኑበት መንገድ የአል-መሲሕ መሰቀል ከአምላክ ፍትህ ከእዝነቱ ከኃይሉና ከጥበቡ ጋር የሚጣጣም ነው ወይ?

37. ከአምላክ በኩል ሆነ በሌላ ሰው በኩል አንድን ግለሰብ ራሱ ያልተካፈለበትን የሌሎች ሰዎች ኃጢአት እንዲያሰርይ ማድረግ ከፍትህ ይቆጠራል ወይ ?

38. ተፈፀመባቸው በተባለው መንገድ ኢየሱስ (ዒሳ) ተዋርደው መገደላቸውን አምኖ መቀበል ከአምላክ ርህራሄና ከጥበቡ ጋር የሚስማማ ነው ወይ ?

39. አምላክ ደጋፊዎቻቸውን ከአደጋ ለመጠበቅና የሚወዳቸውንም ሰዎች ለመከላከል የገባውን ቃል ኪዳን ኢየሱስ (ዒሳ) የአምላክ ጠላቶች ቀላል ሰለባ ሆነው እስኪወድቁ ድረስ ችላ ይላል ወይ? ይህ ደግሞ የገባውን ቃል የማስፈፀሚያ መንገድ ወይም የቃል ኪዳኑ ክቡርነት ቅድመ ሁኔታ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል ወይ?

40. ከሁሉም በላይ መሐሪ የሆነው አምላክ የመጀመሪያውን ኃጢአት ለአዳምና ለዝርዮቹ ይቅር ማለት የማይችልና ነቢዩ ኢየሱስ መጥተው በደማቸው እስኪቤዙ ድረስ በጥርጣሬና በውዥንብር ወስጥ የተዋቸው አድርጎ ማመኑን ምክንያታዊና አሳማኝ ማድረግ ይቻላል ወይ?

41. በስቅላት ወይም  በደም ቤዛነት ማመን ከጥንታውያን የግሪክ ጣኦታውያን ከሮማውያን፣ ከሕንዶችና ከፔርሺያውያን እምነቶች ውስጥ በስተቀር በየትኛውም ሃይማኖት ውስጥ ተከስቶ ያውቃል ወይ?

42. በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ በአፈታሪክ ከሚ.ወሩት ከነባከስ ኦፖሎ አዶኒስ ሆረስና ከሌሎቹም ጥንታዊያን አማልክት በስተቀር ከኢየሱስ ጋር የሚነፃፀር አለ ወይ?

43. ከነቢዩ ኢየሱስ (ዒሳ) የተላኩትን ቃላት የዓለም መጀመሪያና መጨረሻ (አልፋና ኦሜጋ)፣ የሰውን ልጅ በደሚ ወደ ቀጥተኛ መንገድ ለመመለስ ነው የመጣሁት ካለው ከባኮስ ቃላት ጋር ለማነፃፀር ይህ ብሩህ አመለካከት ይሰጠን የለም ወይ? በነዚህ ቃላትና ዘግየት ብሎ በነቢዩ ኢየሱስ ላይ በተላከኩት ቃላት መካከል ያለው መመሳሰል የጉዳዩን ሁለንተናዊ እውነታ ለማጥናት አዲስ ስሜት ሊቀሰቅስ አይችልም ወይ?

44. ሮማውያን ባለስልጣናት በኢየሱስ (ዒሳ) ላይ የነበራቸው ቅራኔ ምንድነው? ለበላይ ስልጣናቸው ተቀናቃኝ አልነበሩም፣ ለመሪ ግለሰቦቻቸውና ለቤተሰቦቻቸው ጥቅም ብዙ ነገሮች ሰርተዋል። ደቀመዛሙርቱንም «የቄሳርን ለቄሳር የእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር» እንዲሰጡ አስተምረዋል፤ ሠላምተኛ ሰባኪ የነበሩ ሲሆኑ በሀገር ውስጥ ሕግና ስርዓትን ለማስጠበቅ ለሮማውያን ባለስልጣኖች ከፍተኛ አጋዥም ነበሩ። ታዲያ ይህን ሰው ሰቅለው እርሱን የመሰለ ሕግ አክባሪና ታዛዥ ዜጋ ለምን ያጣሉ?

45. ስለሮማዊው ገዥ ስለ ጲላጦስ ማንነትና ባህሪ ምን ያህል ነው የምናውቀው? እርሱን በመቃወም ሮም ላይ ከከሰሱት ከዘመኑ አይሁዶች ጋር መልካም ግንኙነት ነበረው ወይ? በይሁዳ ላይ ያሳለፈው ውሳኔ ለእርሱ የነበረውን ጥላቻና ንቀት አያመለክትም ወይ? ጉቦ (መደለያ) እንዲቀበል አላቀረበውም ወይ? ነገሩ እንዲያ ከሆነ ዘንዳ ፍላጎታቸውንና ትዕዛዛቸውን ለማስፈፀም ለምን ይቸኩላል? የኢየሱስ አድናቂ የሆነውን ከበርቴ ጉቦ እንደነዮሴፍ ካሉት ለምን አልተቀበለም? ሉቃስ ባለው መሠረት ይህ ዮሴፍ በጣም ባለፃጋ የሆነ ለነቢዩ ኢየሱስ በጣም ያስብ የነበረ የምክር ቤቱ አባል ሲሆን አል-መሲሕ እንዲሰቀሉ በሚለው የምክር ቤቱ ውሳኔ ላይ ግን ያልተስማማ ሰው ነበር፡፡ለብልሹው ገዥ ጉቦ በማቅረብ እንኳ ቢሆን በምክር ቤቱ ውስጥ ባይሳካለትም የዒሳን ሕይወት ከስቅላት ለማዳን መሞከር ይችል አልነበረም ወይ?

46. የተባለውን የኢየሱስን ስቅለት ሲፈፀም የተመለከቱ ደቀመዛሙርት ቁጥር ስንት ነው? ያሳዩት መስተጋብርስ ምን ነበር? ሐዋርያት በሙሉ ጥለውት ሸሹ የሚለው የማቴዎስ (26፡56) ቃል እውነት ሊሆን ይችላል ወይ? እነዚያ ታላላቅ ሐዋርያት ከታላቁ መምህር ጋር ያላቸው አንድነትና ባህሪ መለኪያው ይህ ነው ወይ? ተወዳጁ ዮሐንስ ብቻ ነበር ይህ ሁኔታ ሲፈጸም በቦታው ተገኝቶ ነበር የሚባለው፡፡ ይሁንና ምን ያህል ጊዜ ነበር በቦታው የቆየው? የተፈረደበት ሰው በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እስኪሞት ድረስ ምን ያል ጊዜ ወሰደ? አስተማማኝ በሆኑ ታሪካዊ ምንጮች መሰረት (ቻምበርስ ኢንሳይክሎፒዲያ፣1950 ስለ መስቀል የተጻፈውን አንቀጽ ይመልከቱ) በመስቀል ላይ እንዲሞት የተፈረደበት ሰው ለመሞት ጥቂት ቀናት ይወስዳል፡፡ ታዲያ ይህ ድርጊት ጥቂት ቀናትን መጠየቁ የተለመደ ሁኔታ ሆኖ ሳለ በኢየሱስ ሁኔታ ለምን ጥቂት ሰዓታትን ብቻ ወሰደ?

ሁለቱ ደቀመዛሙርቶቹ እያሉ እርሱ ለምን ተሰቅሉ ‹‹ሞተ››? ምድርን በሙሉ ለሦስት ሰዓት የሸፈነው ጨለማ ጉዳይስ (ማቴዎስ 27:45፣ ማርቆስ 15:33፣ሉቃስ 23:44) ተሰቃዩን በሌላ ተሰቃይ የመለወጡ ወይም የመተካቱ አፈፃፀም በጨለማውና በትርምሱ ጊዜ በሐምራዊ መጎናፀፊያ ሽፋን ስር ተፈፅሞ ይሆናል ወይ?

47. ኢየሱስን ለመስቀል ለመውሰድ የመጡት ሮማውያን ወታደሮች ለራሳቸው ስለኢየሱስ ያላቸው እውቀት ምን ያህል ነው? ወደ ቦታው የወሰዱት ግለሰብ ተፈላጊው ግለሰብ ለመሆኑ ምን ያህል እርግጠኞች ነበሩ? ለመያዝ ሲሄዱ በተጨባጭ ያውቁት ነበር ወይ? በዚያ ህዝባዊ በዓል በሚከበርበትና የሕዝብ አለመረጋጋት ይፈጠራል ተብሎ በሚፈራበት ጊዜ የዒሳን ማንነት ለማረጋገጥ ልዩ ጥቅም ወይም ግፊት ነበራቸው ወይ?

48. አንድ አማኝ፣ኢየሱስ(ከተከበሩ አምስት ታላላቅ ነቢያት አንዱ የሆኑት) ፀፀትንና መረበሽን በተላበሰ ሁኔታ መስቀል ላይ ሆነው አምላክን በቀቢፀተስፋ ተማጽነዋል በተባለ አኳኋን ይማፀናሉ ብሎ ማሰብ ይቻላል ወይ? እንደ ኢየሱስ ያለ ምርጥ የአምላክ ነቢይ እጅግ በጣም አስቸጋሪ በሆነ የፈተና ወቅት ‹አምላክ ችላ ብሎኛል› ብሎ መናገራቸው ትክክለኛ አባባል ነው ወይ? አምላክን በመማጸን ወይም በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ በሚኖሩ መስተጋብሮች ላይ ይህን እንደፈሊጥ መውሰድ ይገባል ወይ?

49. በጣም ሩህሩህና መሐሪ የሆነው ኃያሉ አምላክ የሰው ልጆችን ኃጢአት፣ ንፁህ ብቻ ሳይሆን አምላክንና የእምነት ጉዳይ ትኩረትን ሊስብ በሚገባ

መንገድ ለማገልገል የሰጠውን ሰው በማስቃየትና በማዋረድ ተፈፀመ የተባለው የስቅለት ድርጊት ሳይኖር ይቅር ለማለት ይችል የለም ወይ? ይህ አምላክ ርህራሄና የመሐሪነቱ ተግባራዊ ገጽታ የፍትህ አስተካካይነቱና የፍቅሩ ነፀብራቅ ነው ወይ?[25]

ኢስላም አል-መሲሕ በጠላቶቻቸው እጅ የመሰቀላቸውን ዶክትሪንም ሆነ የዶክትሪኑን መሠረት በፍፁም አይቀበልም። ይህ እምቢታ አላህ ቁርአን ውስጥ ባለው ላይ የተመረኮዘና የሌሎችን ኃጢአት ለማስረዝ የመሰዋቱን ሁኔታ ከነጭራሹ በመቃወም ላይ የተመሠረተ ነው። የአደም የመጀመሪያ ኃጢአት ራሱ አዳም በፈፀመው ስህተት ተፀፅቶ ምህረት ከለመነ በኋላ የተሰረዘለት መሆኑን ኢስላም ያስተምረናል። ይህም ማለት ማንኛውም ኃጢአ ሰው አላህ ምህረት ካላደረገለት በስተቀር በኃጢአቱ ተጠያቂና ማንም ሰው የሌሎችን ኃጢአት ለማሰረይ በፍፁም አይችልም ማለት ነው። ይህ (የቤዛ ጽንስ ሃሳብ) ግን የሌሎችን ኃጢአት ለማስማር ራሱን መስዋዕት አደረገ የሚለው መርህ አንዳች ቦታ የለውም። ያም ሆነ ይህ አንዳንዶቹ የመጀመሪያ የክርስቲያን ቡድኖች አል-መሲሕ በመስቀል ላይ ተገድለዋል ብለው እያምኑም ነበር። ሌሎች ቡድኖች ደግሞ ሌላ ሰው በቦታቸው መሰቀሉን ያምኑ ነበር። ሌሎች ክፍሎች አል-መሲሕ ሥጋዊ ወይም የተለመደው ዓይነት ነባራዊ አካል አልነበራቸውም። ንፁህ የሆነ አካል እንጂ፣ ስቅለታቸውም ቅርፃዊ እንጂ ይዘታዊ አልነበረም፣ብለው ያምናሉ። የማርሲዮኔት ወንጌል ደግሞ (138 ዓመተ ልደት) አል-መሲህ ከነጭራሹ መወለዱን አስተባብለው በሰው ቅርጽ ብቻ መገለጡን ይናገራሉ። የእንግሊዝኛ ቅጂው ቪየና ባለው የመንግስት ቤተ መጽሕፍት ያለውና

---

25 ከጥያቄ ተራ ቁጥር 36-49 ያለው «ፍኖተ እስላም» ከተሰኘው የዶ/ር ሐሙዳ ዐብዱል ዓጢ መጽሐፍ ከአማርኛው ትርጉም በማሻሻል የተወሰደ ነው።

የዐረብኛ ቅጂው በዐረቡ ዓለም የሚገኘው የቅዱስ በርናባስ ወንጌል በበኩሉ በመስቀሉ ላይ በሌላ ሰው ተተካ የሚለውን አመለካከት ይደግፋል። ቁርአን የኢየሱስን መሰቀልና መሞት ውድቅ አድርጓል። በአንፃሩም ወደ ሰማይ ማረጉን አስታውቋል፡-

*‹‹‹እኛ የአላህ መልእክተኛ የሆነውን የመርየም ልጅ አል-መሲሕ ዒሳን ገደልን› በማለታቸውም ሰበብ (ተረገሙ)። አልገደሉትም። አልሰቀሉትምም። ግን ተመሳሰለባቸው። እነዚህ በዚህ ጉዳይ ላይ የተወዛገቡት ጥርጣሬ ውስጥ ናቸው።በዚህ ላይ ቅንጣት እውቀት የላቸውም።ጥርጣሬን ከመከተል በቀር። በእርግጥም አልገደሉትም።ይልቅአላህ ወደ እርሱ እንዲያርግ አደረገው። አላህ አሸናፊ፣ጥበበኛ ነውና።›› (ሱረቱ ኒሳእ 4:157-158)*

ኢስላም የኢየሱስን (ዒሳን) መሰቀል አይቀበልም።ጌታው አላህ ከስቅላት አድኖት ወደ ሰማይ አሳርጎታል ሲል ይገልጻል። ኢየሱስን ከጠላቶቹ ከከሃዲዎቹ በላይ እንደሚያደርገውም ቃል እንደገባለት እንዲህ ይናገራል፡-

*‹‹አላህም ባለ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)፡- ‹ዒሳ ሆይ! እወስድሃለሁ።ወደኔም አነሳሃለሁ። ከነዚያም ከካዱት ሰዎች (ተንኮሉችም) አፀዳሃለሁ። እነዚያን አንተን የተከተሉትንም ወገኖች እስከ ዕለተ ቂያማ (ትንሳኤ) ድረስ ከነዚያ ከካዱት በላይ አደርጋለሁ። ከዚያም መመለሻችሁ ወደኔ ነው።ትወዛገቡበት የነበረውን ነገር በመካከላችሁ ብይን እሰጣለሁ። እነዚያን የካዱትን ወገኖች በዚህችም በቀጣዩም አለም ብርቱ ቅጣትን እቀጣቸዋለሁ። (ከቅጣት የሚያድን) ረዳት አይኖራቸውም። ለእነዚያ ላመኑትና መልካም ተግባራትን ለፈፀሙት (አላህ) ምንዳቸውን ይሰጣቸዋል። አላህ በዳዮችን አይወድም። (ሙሐመድ ሆይ!) ይህ የምናነበልህ (ታሪክ የምናወሳልህ መልዕክት) የጥበበኛው (መጽሐፍ) ታአምራትና መልዕክቶች አካል ነው። ከአላህ ዘንድ ዒሳ እንደ አደም አምሳያ ነው። (አላህ አደምን) ከአፈር ፈጠረው። ሁን አለው፣ ሆነ።›› (ሱረቱ አሊ-ዒምራን 3:55-59)*

በኢስላም በኩል ክርስቶስ(አል-መሲህ) አለመገደላቸውን፤አለመሰቀላቸውንና አላህ ለክብራቸው ሲል በችሮታውና በእዝነቱ ወደ ሰማያት አንስቷቸዋል የሚል እምነት ነው ያለው።ሙስሊሙ በዚህ ጉዳይ ላይ ያለው አመለካከት በአጠቃላይ ግልጽና የጠራ ነው።በዚህ በኩል ያሉትን ጭቅጭቆች በሙሉ ቁርአን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መፍትሔ ሰጥቷቸዋል።

## ኢየሱስን ማነው ብለው አመኑበት?

የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ላይ አብይ ማስረጃ ሊሆን የሚችለው ያኔ በኢየሱስ ዙርያ የነበሩት ሕዝቦች፣ ሐዋርያትና ድንቅ ተዓምሩን የተመለከቱት ሰዎች «ምን እምነት ነበራቸው?›› የሚለውን ማወቁ ነው። ‹ኢየሱስ ማን ነው?››፣ ‹እንዴት ድንቅ ተዓምራትን ሊያሳይ ቻለ?››፣ ‹አምላክ ስለሆነ ወይንስ የአምላክ ነቢይ ስለሆነ?›፣ወዘተ ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ከነርሱ ከራሳቸው ይገኛል። ስለዚህ እነዚያ አማኞች የነበራቸውን አቋም በጥሞና ማወቁ እጅግ ጠቃሚ ነው። ውድ አንባቢ ሆይ! በማስከተል የሚነሱትን ጥያቄዎች በጥሞና አብረን እንመልከት፦

1. ዮሐንስ 6:14 እንዲህ ይላል፦ «ሰዎቹም ኢየሱስ ያደረገውን ታምራዊ ምልክት ካዩ በኃላ፤ *«ወደ ዓለም የሚመጣው ነቢይ በእርግጥ ይህ ነው» አሉ።»* ይህን የተናገሩት ሰዎች አማኝ ናቸው ወይንስ ከሃዲ? ኢየሱስን ያዩት ሰዎች «ነቢይ ነው» ብለው አመኑ። ልክ እንደ ሙስሊሞቹ! ታዲያ ክርስቲያኖች ይህን ለምን ተቃርነው «አምላክ ነው» አሉት?

2. ማቴዎስ 9:8 «ሕዝቡም ይህን ባዩ ጊዜ በመደነቅ፤በፍርሃት ተሞልተው፤ *እንደዚህ ያለ ሥልጣን ለሰው የሰጠውን እግዚአብሔርን አመሰገኑ።»* ይላል ።ኢየሱስ አስገራሚ ተዓምር ሲያደርግ ኢየሱስ ምንድነው ብለው አመኑ? ተዓምሩስ የማን ነው? አድራጊውስ ማን ነው? ጥቅሱ «እንደዚህ ያለ ስልጣን

ለሰው የሰጠውን እግዚአብሔርን አመሰገኑ።» ይላል። ታዲያ ክርስቲያኖች ለምን ኢየሱስ ተዓምራትን ሲያሳይ በስፍራው ከተገኙት አማኞች ተቃራኒ እምነት ያዙ?

3. ዮሐንስ 17:6-9 እንዲህ ይላል፡- «ለእነዚህ ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገልጬላቸዋለሁ።የአንተ ነበሩ፤ለእኔ ሰጠኸኝ፤ እነርሱም ቃልህን ጠብቀዋል። የሰጠኸኝ ሁሉ ከአንተ እንደሆነ አሁን ዕውቀዋል፤ምክንያቱም የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸው ተቀብለዋል ፤እኔም ከአንተ እንደወጣሁ በእርግጥ ዐውቀዋል ፤አንተ *እንደላክኸኝም*፤አምነዋል። እነርሱ የአንተ ስለሆኑ፤እፀልይላቸዋለሁ፤ ለሰጠኸኝና የአንተ ለሆኑት እንጂ ለዓለም አልፀልይም።» ኢየሱስ .እንደ ነገረን ሐዋሪያት ኢየሱስ ምን መሆኑን አመኑ? ከአምላክ መላኩን! ታዲያ ለምን ክርስቲያኖች በተቃራኒው ተረዱ?

4. የሐዋርያት ሥራ 11:25-26 «ከዚህ በኋላ በርናባስ፤ ሳውልን ለመፈለግ ወደ ጠርሴስ ሄደ፤ባገኘውም ጊዜ ወደ አንፆኪያ አመጣው። ሁለቱም እዚያ ካለችው ቤተክርስቲያን ጋር በመሆን አንድ ዓመት ሙሉ እጅግ ብዙ ሕዝብ አስተማሩ፤ደቀመዛሙርትም *ለመጀመሪያ ጊዜ በአንፆኪያ «ክርስቲያን» ተብለው ተጠሩ።»* እንደዚህ ጥቅስ አገላለፅ ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ በአጾንኪያ «ክርስቲያን» ከተባሉ እንዴት ኢየሱስ ክርስትናን ሰበከ አስተማረ ሊባል ይችላል?

5. ዮሐንስ 17:25 «ፃድቅ አባት ሆይ! ዓለም ባያውቅህም፤ እኔ ዐውቅሃለሁ፤ እነዚህም አንተ እንደ ላከኸኝ ያውቃሉ።» ይላል። በዚህ ጥቅስ ላይ እንደተገለጸው ሐዋርያት ኢየሱስ ምን መሆኑን ያውቃሉ ተባለ? «እነዚህም አንተ እንደ ላከኸኝ ያውቃሉ።» ታዲያ ክርስቲያኖች ይህን አምነው መቀበል ለምን ተሳናቸው?

6. ሉቃስ 24:19 «እነርሱም እንዲህ አሉ፡ «በእግዚአብሔርና በሰው ሁሉ ፊት በተግባርና በቃል ብርቱ ነቢይ ስለ ነበረው ስለናዝሬቱ ኢየሱስ ነው።» ይላል።እነዚያ ኢየሱስ ተዓምር ሲያደርግ የነበሩና የተመለከቱት ኢየሱስን ማን ብለው ገለጹት? «ነብይ ስለ ነበረው ስለናዝሬቱ ኢየሱስ!» «አምላክ ነው» ብለው አሰበው ነበርን? በጭራሽ! ታዲያ ክርስቲያኖች እነዚያ ያላመኑትን ምነው ማመናቸው?

7. ዮሐንስ 6:14 ‹‹ሰዎቹም ኢየሱስ ያደረገውን ታምራዊ ምልክት ካዩ በኋላ፣ ‹ወደ ዓለም የሚመጣው ነቢይ በእርግጥ ይህ ነው› አሉ።›› ይላል። የኢየሱስን ታምራዊ ምልክት አይተው የዛሬ ክርስቲያኖች እንደሚሉት ‹ኢየሱስ ጌታ ነው! አምላክ ነው!›› ነበር ያሉት? ጥቅሱ የሚነግረን ‹‹የሚመጣው ነቢይ በእርግጥ ይህ ነው›› እንዳሉ ነው። ክርስቲያኖች ታዲያ ምነው ይህን ማመን አልፈለጉም?

8. የሐዋርያት ሥራ 2:22 «የእስራኤል ሰዎች ሆይ! ይህን ቃል ስሙ፤ እናንተ ራሳችሁ እንደምታውቁት፤ እግዚአብሔር በመካከላችሁ ታምራትን፤ ድንቅ ነገሮችንና ምልክቶችን በእርሱ በኩል በማድረግ ለናዝሬቱ ኢየሱስ መስክሮለታል።» ይላል። እነርሱ ምንድነው የሚያውቁት? «ኢየሱስ ተዓምራት ያደረገው አምላክ ስለሆነ ነው» ብለው ነው? በጭራሽ! «እግዚአብሔር በመካከላችሁ ታምራትን፤ ድንቅ ነገሮችንና ምልክቶችን በእርሱ በኩል በማድረግ ለናዝሬቱ ኢየሱስ መስክሮለታል።» ነው የሚለው። ታዲያ ክርስቲያኖች ለምን ይህን ተቃረኑ?

9. ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 17:25 ላይ «ፃድቅ አባት ሆይ! ዓለም አላወቀህም፤ እኔ ግን አወቅሁህ፤ እነዚህም አንተ እንደላከኝ አወቁ፤» ይላል። ኢየሱስ ሐዋርያቶቹ ምን እንዳወቁ ተናገረ? «አንተ እንደላከኸኝ አወቁ» በማለት የኢየሱስን በአምላክ መላክ ማወቃቸውን ገለፀ። ታዲያ ሐዋርያት የኢየሱስን

በአምላክ መላክ አውቀው መልዕክተኝነቱን ከተቀበሉ፤ ክርስቲያኖች ለምን የኢየሱስን በአምላክ መላክ መቀበል ከበዳቸው?

10. የኢየሱስ አስተምህሮት በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው ከሆነ ክርስቲያኖች በአረዳድ ላይ እስከዛሬ ሊስማሙ ለምን ተሳናቸው? ለምንስ በሺህ ስፍራዎች ተከፋፈሉ?

11. ዮሐንስ 7:16-17 «ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤«የማስተምረው ትምህርት ከራሴ ሳይሆን፣ከላከኝ የመጣ ነው።ማንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ቢፈልግ፤ <u>የእኔ ትምህርት ከእግዚአብሔር ወይም ከራሴ የመጣ መሆኑን ለይቶ ያውቃል።»</u> ይላል።ኢየሱስ የሚያስተምረው ትምህርት ከራሱ ሳይሆን ከላከው አምላክ መሆኑን እየገለጸ እንዴት ክርስቲያኖች ክርስቶስን «አምላክ» ሊሉት ቻሉ?

12. ዮሐንስ 7:40 እንዲህ ይላል:- «ከሕዝቡ አንዳንዶቹ ቃሉን ሰምተው፤«<u>ይህ ሰው በእርግጥ ነቢይ ነው»</u> አሉ።» የኢየሱስን አስምህሮት ያደመጡት አማኞች ኢየሱስን «ነቢይ» ብለዋል።ሙስሊሞችም ተመሳሳይ አቋም አላቸው። ግና ክርስቲያኖች ይህንን ተቃርነው ኢየሱስን አምላክ አድርገዋል። ታዲያ የኢየሱስን ቃል የሰሙት አማኞች ወይንስ ክርስቲያኖች ናቸው ትክክል?

13. ዮሐንስ 9:17 <u>«ስለዚህ፤ዐይነ ስውር ወደ ነበረው ሰው ተመልሰው፤ «ዐይኝህን ስለከፈተው ሰው፤እንግዲህ አንተ ምን ትላለህ?» አሉት። ሰውየውም፤«እርሱ ነቢይ ነው አለ።»</u>ይላል።በኢየሱስ ተዓምር ዓይነስውርነቱ የተወገደለት ግለሰብ ኢየሱስን «ነቢይ» ካለ ከዘመናት ቆይታ በኃላ የተነሱት ክርስቲያኖች ሙስሊሞች «ኢየሱስ ነቢይ ነው» በማለት ማመናቸውን እንዴት ሊያወግዙ ቻሉ?

14. ዮሐንስ 4:19 እንዲህ ይላል:- «ሴትየዋም እንዲህ አለችው፤ «ጌታዬ ፤አንተ ነቢይ እንደሆንህ አያለሁ!» ይህች ሴት ኢየሱስን በማክበር «ጌታዬ» ብላው «ነቢይ እንደሆንህ አያለሁ» ስትለው እርሱ «አምላክ እንጂ ነቢይ» ባይሆን ኖሮ ለምን «እኔ አምላክ እንጂ ነቢይ አይደለሁም» ሲል አያርማትም ነበር?

15. ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱ ከኢየሩሳሌም 11 ኪሎ ሜትር ወደሚርቀው ኤማሁስ ወደሚባለው መንደር ሲሄዱ ኢየሱስ መጥቶ ይጠይቃቸዋል:: (ሉቃስ 24:13-20ን ይመልከቱ) «እነርሱም እንዲህ አሉት፣ «በእግዚአብሔርና በሰው ሁሉ ፊት በተግባርና በቃል ብርቱ ነቢይ ስለነበረው ስለናዝሬቱ ኢየሱስ ነው፤» (የሉቃስ ወንጌል 24:19) ደቀ መዛሙርቱ ራሳቸው ኢየሱስን «በእግዚአብሔርና በሰው ሁሉ ፊት በተግባርና በቃል ብርቱ ነቢይ» ብለው ለራሱ ለኢየሱስ ሲነግሩት ልክ አልነበሩምን? ኢየሱስን «በእግዚአብሔርና በሰው ሁሉ ፊት ብርቱ ነቢይ» ሲሉት ተሳስተው ቢሆን ኖሮ «የክህደት ንግግር» ተናግራችኃል ብሎ ኢየሱስ ለምን ሳያርማቸው ቀረ? (ሙስሊሞች «ኢየሱስ ነቢይ ነው» ማለታቸውን ክርስቲያኖች እንደ ክህደት ስለሚቆጥሩት ነው::) እርሱም በ «ክህደቱ ንግግር» ተስማምቶ ነውን?

የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ኢየሱስን በአካል አይተዉት፣ አናግረዉት፣ ተዓምራቱን ተመልክተው፣ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፣ ለኢየሱስ ለራሱ «ብርቱ ነቢይ ነህ» ካሉት ክርስቲያኖች ምን ነካቸው? ከደቀመዛሙርቱ በለጡ? ከኢየሱስስ በለጡ?

16. የሉቃስ ወንጌል 7:14-16 «ቀረብ ብሎም ቃሬዛውን ነካ፤ የተሸከሙትም ሰዎች ቀጥ ብለው ቆሙ፤ ኢየሱስም «አንተ ጎበዝ፤ ተነስ እልሃለሁ!» አለው:: የሞተውም ሰው ቀና ብሎ ተቀመጠ፤ መናገርም ጀመረ:: ኢየሱስም ወስዶ ለእናቱ ሰጣት:: ሁሉም በፍርሃት ተውጠው እግዚአብሔርን እየመሰገኑ፤ «ታላቅ ነቢይ በመካከላችን ተነሥቶአል»፤ «እግዚአብሔርም ሕዝቡን ጎብኝቶአል» አሉ::» ይላል:: በአምላክ ለኢየሱስ የተሰጠው ይህን

መሰል ተዓምር ሲፈጸም በሥፍራው የነበሩና በተዓምሩ የተደነቁት ወገኖች እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ***«ታላቅ ነቢይ በመካከላችን ተነሥቶአል»*** በማለት የኢየሱስን ነቢይነት ከመሰከሩ፣ሙስሊሞችም የነዚህን አማኞች አቋም በመያዛቸው ሊተቹ ይገባልን? መተቸት ያለበት ኢየሱስን ያላዩ፣ ተዓምራቱን ሲፈጽም በስፍራው ያልነበሩ፣ ከዘመናት በኃላ ተቃራኒ እምነትን የያዙት ክርስቲያኖች ናቸው ወይስ ሙስሊሞች? ሙስሊሞችን መተቸት ደቀመዛሙርቱን የመተቸት ያህል ነው:: ለምን? ቢሉ ደቀ መዛሙርቱ ራሳቸው ልክ እንደ ሙስሊሞች ኢየሱስን «ነቢይ ነው» ብለዋልና! ታዲያ ክርስቲያኖች ለምን ተቃራኒ ጎዳናን መረጡ?

17. ማቴዎስ 21:11 «ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜም ከተማዋ በመላ፤ ***«ይህ ማነው?»*** በማለት ታወከች:: ***አጅቦት የመጣው ሕዝብም***፤ «ይህ በገሊላ ከምትገኘው ከናዝሬት የመጣው ***ነቢዩ ኢየሱስ ነው»*** አሉ::» ይላል:: ኢየሱስን አጅቦት አብሮት ሲጓዝ የነበረው ሕዝብ «ነቢዩ ኢየሱስ» ሲለው ምነው ክርስቲያኖች «አምላክ» ነው ማለታቸው? አምላክ እንዲሰኝ ፈልገው ይሆንን? አምላክነትስ በፍላጎት ይገኛል እንዴ?

ከሙስሊሞችና ከክርስቲያኖች ልዩነት ዉስጥ አንዱ የኢየሱስ ማንነት ጥያቄ ነው:: ለመሆኑ ኢየሱስ ማን ነው? ኢየሱስ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ «***ይህ ማነው?» ነበር የህዝቡ ጥያቄ::*** ምላሹንም አጅበው አብረው ወደ ኢየሩሳሌም የመጡት አማኞች እንዲህ ሲሉ ነበር የገለጹት «ይህ በገሊላ ከምትገኘው ከናዝሬት የመጣው ነቢዩ ኢየሱስ ነው»:: ታዲያ ክርስቲያኖች ኢየሱስን አጅበው አብረው ሲጓዙ ከነበሩት አማኞች በልጠው ነው ነቢይነቱን ያልተቀበሉት?

## ኢየሱስ ስለራሱ ምን እምነት ነበረው?

ከሙስሊሞችና ከክርስትያኖች ልዩነቶች ውስጥ አንዱና ዋንኛው የኢየሱስ ጉዳይ ነው:: እስካሁን በርካታ ነጥቦችን ተመልክተናል:: በዚህ ምዕራፍ ሥር ኢየሱስ ስለራሱ ምን እምነት እንደነበረው እንመለከታለን:-

18. ዮሐንስ 13:3-4 «ኢየሱስም፣ *አብ ሁሉን ነገር በሥልጣኑ ሥር እንዳደረገለት፤ ከእግዚአብሔር እንደተላከና ወደ እግዚአብሔርም እንደ ሚመለስ ዐውቆ*፣ ከራት ተነሳ፣ መጎናጸፊያውን አስቀመጠ፤ ወገቡንም በፎጣ ታጠቀ» ይላል:: ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ ሁሉም ሥልጣን በራሱ እንዳለው ነው ያወቀው? በጭራሽ! ታዲያ ጥቅሱ ምን ይላል? «*አብ ሁሉን ነገር በሥልጣኑ ሥር እንዳደረገለት፤*» አብ እንዳደረገለት! አምላክ ስለሆነ የሰው ልጅን ለማዳን ወረደ? ወይስ በአምላክ እንዲያስተምር መላኩን ነው ኢየሱስ የሚያውቀው? ጥቅሱ «*ከእግዚአብሔር እንደተላከና ወደ እግዚአብሔርም እንደሚመለስ ዐውቆ*» ይላል:: ታዲያ ክርስቲያኖች ስለ ኢየሱስ ከራሱ ከኢየሱስ በላይ ያውቃሉን?

19. ዮሐንስ 14:24 ኢየሱስ እንዲህ ማለቱን ይገልጻል:- «የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም:: ይህ የምትሰሙት ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም::» ኢየሱስ የተናገረው ከራሱ ነው ወይንስ እንደሌሎች ነቢያት ከአምላክ ተነግሮት? ይህ እንግዲህ ራሱ ኢየሱስ ስለ ራሱ በዚህ ጥቅስ ላይ የነገረን ቃሉ ነው::ታዲያ ክርስቲያኖች ይህንን ኢየሱስን ቃል እየጠበቁ ነውን? ግና «እንወደዋለን» ይላሉ:: ታዲያ ቢወዱት ቃሉን አይጠብቁም ነበርን? ኢየሱስ እንዲህ ብሎ ነበር *«የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም::»* ታዲያ ክርስቲያኖች ምን ነካቸው?

20. ዮሐንስ 12:49 «እኔ ከራሴ አልተናገርሁም፤ ነገር ግን የላከኝ አብ ምን እንደምናገርና እንዴት እንደምናገር አዘዘኝ::» ይላል:: ኢየሱስ አምላክ እንዳዘዘው ተናገረ:: ለአምላኩም ታዛዥ ነው:: «ታዛዥ» የሚለው

የአረብኛው ቃል አቻው «ሙስሊም» የሚለው ቃል ነው:: ስለዚህ ኢየሱስ ሙስሊም ነው! ታዲያ ኢየሱስ ምን እንደሚናገር ሁሉ ከአምላክ መታዘዙን ራሱ እየተናገረ እንዴት ለአምላክ ታዛዥነቱን በማስተባበል ራሱ «አምላክ» ነው ሊባል ተቻለ?

21. የዮሐንስ ወንጌል 7:28-29 «ኢየሱስ በቤተመቅደስ አደባባይ ሲያስተምር ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲህ አለ፤ <u>«አዎን፤እኔን ታውቁኛላችሁ፤</u> ከየት እንደሆንሁም ታውቁላችሁ:: <u>እኔ እዚህ ያለሁት በገዛ ራሴ አይደለም</u>፤ ነገር ግን <u>የላከኝ</u> እርሱ እውነተኛ ነው::እናንተ አታውቁትም፤ እኔ ግን ከእርሱ ዘንድ ስለሆንሁ፤<u>እርሱም ስለላከኝ ዐውቀዋለሁ::</u>» ይላል:: ኢየሱስ ይህን ሲናገር ሰዎች ማንነቱን እንዲያውቁ ፈልጎ ነው? «አምላክነቱን» ወይስ የአምላክ መልዕክተኛ መሆኑን? ድምጹን ከፍ አድርጎ <u>«አዎን፤ እኔን ታውቁኛላችሁ፤</u>» ሲል ስብከቱን የሚያደምጡት ሰዎች ኢየሱስ ምን መሆኑን ነው ያወቁት?

እርሱም በዚህ ጥቅስ ብቻ (የተሰመረባቸውን ልብ ይበሉ) «የላከኝ» እና «እርሱም ስለላከኝ ዐውቀዋለሁ::» በማለት መልዕክተኛ መሆኑን፤«<u>እኔ እዚህ ያለሁት በገዛ ራሴ አይደለም</u>» ሲል ለአምላኩ ታዛዥ መሆኑን ገልጿል:: እንደዚሁም <u>«አዎን፤እኔን ታውቁኛላችሁ</u>» በማለት ተናግሮ የላከውን አምላክ ግን «እናንተ አታውቁትም» በማለት አምላክና ኢየሱስ የተለያዩ መሆናቸውን አስረግጦ ገልጿል:: አንድ ቢሆኑ አልያም ኢየሱስ ራሱ አምላክ ቢሆን አንዱን አውቀው ሌላኛዉን ሳያውቁ አይቀሩም ነበር:: ታዲያ ክርስቲያኖች ምነው ከኢየሱስ አስተምህሮት መራቃቸው?

22. ዮሐንስ 7:16-18 «ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ «የማስተምረው ትምህርት ከራሴ ሳይሆን፤ ከላከኝ የመጣ ነው:: ማንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ ቢፈልግ፤ የእኔ ትምህርት <u>*ከእግዚአብሔር ወይም ከራሴ*</u> የመጣ መሆኑን ለይቶ ያውቃል:: ከራሱ የሚናገር፤ ያን የሚያደርገው

ለራሱ ክብርን ስለሚሻ ነው፤ ስለላከው ክብር የሚሠራ ግን እርሱ እውነተኛ ነው፤ ሐሰትም አይገኝበትም።» ይላል። ኢየሱስ «የእኔ ትምህርት *ከእግዚአብሔር ወይም ከራሴ* የመጣ መሆኑን ለይቶ ያውቃል።» ሲል አምላክና ኢየሱስ የተለያዩ መሆናቸውን ገለጸ። እንደ ክርስትና አስተምህሮት አምላክ ሥላሴ ነው። የአብ፣የወልድና የመንፈስ ቅዱስ የሦስቱ የአንድነት ጥምረት ነው-እግዚአብሔር። ታዲያ ኢየሱስ «*ከእግዚአብሔር ወይም ከራሴ*» ሲል መናገሩ «ኢየሱስ» እና «እግዚአብሔር» የተለያዩ መሆናቸውን አያሳይምን? ይህ የኢየሱስ ንግግር «እግዚአብሔር» የሚለው የሦስቱ ጥምረት ነው የሚለው እሳቤ መሠረተ ቢስ መሆኑን አይገልጽምን? ኢየሱስስ ስለላከው አምላክ ክብር እንደሚሰራ መናገሩ ምንን ያሳያል?

23. የኢየሱስ እምነት ምን ነበር? ከዘመናት በኃላ በአንጾኪያ ኢየሱስ ሃይማኖትን ሰብኳልን? ኢየሱስ ክርስቶስን የተከተሉ ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ከክርስቶስ እርገት በኃላ በአንፆኪያ «ክርስቲያን» ከተባሉ የእርሱ እምነት ምን ይባላል?

## እውን እነኚህ የአምላክ ባህሪያት ናቸውን?

1. ጳዉሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 1፡25 ላይ «ምክንያቱም ከሰው ጥበብ ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባል፤ ከሰውም ብርታት ይልቅ የእግዚአብሔር ድካም ይበረታል።» ብሏል። እንደዚህ ጥቅስ አባባል እግዚአብሔርም ሞኝነት አለበት፤ግን የእርሱ ሞኝነት ከሰው ጥበብ ይጠበባል።ድካምም አለበት፤ነገር ግን ድካሙ ከሰው ብርታት ይበረታል። መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው አምላክ ድካምና ሞኝነት ካለበት ምኑን አምላክ ሆነ? ወይስ ይህ ጥቅስ የጳውሎስ ፈጠራ ነው?

2. መጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት ላይ እንዲህ ይላል፦ «ቀኑ መሸትሸት ሲል፤ እግዚአብሔር አምላክ በአትክልቱ ስፍራ ሲመላለስ አዳምና ሔዋን ድምፁን ሰምተው ከእግዚአብሔር አምላክ ፊት በዛፎቹ መካከል ተሸሸጉ። እግዚአብሔር አምላክ ግን አዳምን ተጣርቶ፤«የት ነህ?» አለው።» አዳምም፤

«ድምጽህን በአትክልቱ ስፍራ ሰማሁ፤ ዕራቁቴን ስለሆንሁ ፈራሁ፤ ተሸሸግሁም» ብሎ መለሰ።» (ዘፍጥረት 3:8-10) «እግዚአብሔር :«ዕራቁትህን መሆንን ማን ነገረህ? «ከእርሱ እንዳትበላ» ብዬ ካዘዝኩህ ዛፍ በላህን?» አለው።» (ዘፍጥረት 3:11) ይህ አንቀፅ እውን የአምላክ ቃል ነውን? ከሆነስ አምላክ እንዴት የት እንደተደበቁ ማወቅ ተስኖት አዳምን «የት ነህ?» ሲል ይጠይቃል? የተከለከለውን ዛፍ ይብላ ወይም አይብላስ ጠይቆ ነው የሚያረጋግጠው?

3. ዘፀአት 31:17 «በእኔና በእስራኤላውያን መካከል ለዘላለም ምልክት ይሆናል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ሰማይ ምድርን በስድስት ቀን ሰርቶ፤ በሰባተኛው ቀን ከሥራ ታቅቦ ዐርፎአልና።» ይላል። እንዲሁም በሌላ ስፍራ «ስለ ሰባተኛውም ቀን በአንድ ስፍራ፤ «በሰባተኛውም ቀን እግዚብሔር ከሥራው ሁሉ ዐረፈ» ብሏልና።» (ዕብራውያን 4:4)

አምላክ እንደሰው ሥራ ሰርቶ ያርፋልን? ድካም ይሰማዋል እንዴ? አንዳንድ ክርስቲያኖች «አምላክ ሊያስተምረን ብሎ ነው» ይላሉ። አምላክ የሚስተምረው ነቢያትንና መጻሕፍትን በመላክ ነው ወይንስ የደካማውን የሰው ልጅ ባህሪ በመላበስ?

4. መዝሙር 44:23-24 «ጌታ ሆይ፤ንቃ! ለምንስ ትተኛለህ? ተነሥ፤ ለዘላለም አትጣለን። ፊትህን ለምን ትሰውራለህ? መከራችንንና መጠቃታችንን ለምን ትረሳለህ» ይላል። አምላክ ተኝቶ ሰው «ንቃ» ብሎ ይቀሰቅሰዋልን? ለመሆኑስ አምላክ ይረሳልን? ታዲያ ይህን አምላክ ነው ሙስሊሞች እንዲያምኑበት ክርስቲያኖች የሚጣሩት? ወይስ ይህ የአምላክ ቃል አይደለም?

5. መዝሙር 78:65 «ጌታም ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሳ፤ የወይን ጠጅ ስካር እንደ በረደለት ጀግናም ብድግ አለ።» ይላል። አምላክ ከእንቅልፍ እንዴት ይነቃል? ኃያሉን አምላክ በዚህ መልኩ መግለፅ ተገቢ ነውን?

6. ዘፍጥረት 32:22-28 «በዚያች ሌሊት ያዕቆብ ተነሣ፤ ሁለቱን ሚስቶቹን እንዲሁም ሁለቱን ሴት አገልጋዮቹን እና ዐሥራ አንድ ልጆቹን ይዞ በያቦቅ መልካ ተሻገረ። ወንዙን አሻግሮ ከሸኛቸው በኋላ፤ጓዙን ሁሉ ሰደደ። ያዕቆብ ግን ብቻውን እዚያው ቀረ፤ አንድ ሰውም እስኪነጋ ድረስ ሲታገለው አደረ። ያም ሰው ያዕቆብን ታግሎ ማሸነፍ እንዳቃተው በተረዳ ጊዜ፤ የጭኑን ሹልዳ ነካው፤ በግብግቡም የያዕቆብ ጭን ከመገጣጠሚያው ላይ ተናጋ። በዚያን ጊዜ <u>ሰውየው፤ «እንግዲህ መንጋቱ ስለሆነ ልቀቀኝና ልሂድ» አለው። ያዕቆብም፤ «ካልባረክኸኝ አልለቅህም» አለው።ሰውየውም፤ «ከእግዚአብሔርም ከሰዎችም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና ከእንግዲህ ስምህ እስራኤል እንጂ ያዕቆብ አይባልም» አለው።»</u> ይላል።

ያዕቆብ ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎዋልን? እንዴትስ ታግሎ አሸነፈ? መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው አምላክ ይህ ነው ማለት ነው?

7. ዘፍጥረት 6:6 «እግዚአብሔር ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ <u>ተፀፀተ፤ በልቡም እጅግ አዘነ።»</u> ይላል።እግዚአብሔር እንደ ደካማው ፍጥረት እንደሰው ባደረገው ይፀፀታልን? በመሰረቱ «ጸጸት» ማለት አንድ ሰው አንድን ድርጊት ያደርግና በኋላ ያደረገው ድርጊት በጠበቀው መልኩ ሳይሆንለት ሲቀር ነው።ይህ ለሰው የተገባ ባህሪ ነው።ምክንያቱም ሰው አስቀድሞ የነገርን ፍጻሜ ማወቅ አይችልምና።አምላክ ግን ሁሉን የሚያውቅ ጌታ ስለሆነ በሚሠራው ሥራ አይጸጸትም።ታዲያ «አምላክ ሰውን በመፍጠሩ ተጸጸተ» ማለት አግባብነት አለውን? ሰውን ሲፈጥር ሰው ምን እንደሚያደርግ አስቀድሞ አያውቅምን? የማያውቅ ከሆነ ሁሉን አዋቂ

አይደለም ማለት ነው። ታዲያ ይህ አምላክ መሆን ይችላልን? ወይስ ይህ የአምላክ ሳይሆን የሰው ቃል ነው?

8. 1ኛ ሳሙኤል 15:35 «ሳሙኤል ለሳኦል ቢያለቅስለትም እንኳ እስከ ሞተበት ዕለት ድረስ ዳግመኛ ሊያየው አልሄደም። እግዚአብሔርም ሳኦልን በእስራኤል ላይ በማንገሡ <u>ተፀፀተ።</u>» ይላል። አምላክ ይፀፀታልን? ፈጣሪን ይፀፀታል ማለት ድፍረት አይሆንምን?

9. ትንቢተ አሞፅ 7:1-6 ላይ «ጌታ እግዚአብሔር ይህን አሳየኝ፤ የንጉሡ የመኸር እህል ከተሰበሰበ በኋላ ገበው መብቀል በጀመረ ጊዜ፣ እርሱ የአንበጣ መንጋ እንዲፈለፈል አደረገ። አንበጦች የምድሩን ሣር ግጠው ከጨረሱ በኋላ «ጌታ እግዚአብሔር ሆይ! ይቅር እንድትል እለምንሃለሁ፣ ያዕቆብ ይህን እንዴት ሊቋቋመው ይችላል? ታናሽ ነው እኮ» አልሁ፤ <u>*እግዚአብሔርም ስለዚህ ነገር ተፀፀተ።*</u> እግዚአብሔርም ይህ አይፈፀምም አለ።

ጌታ እግዚአብሔር ይህንም አሳየኝ፤ ጌታ እግዚአብሔር በእሳት ሊፈርድ ተዘጋጀ፤ እሳቱም ታላቁን ጥልቅ አደረቀ፤ ምድሪቱንም በላ። ከዚያም በኋላ፤ «ጌታ እግዚአብሔር ሆይ! እንድትተወው እለምንሃለሁ፤ያዕቆብ ይህን እንዴት ሊቋቋመው ይችላል? ታናሽ ነው እኮ አልሁ። <u>እግዚአብሔር ስለዚህ ነገር ተፀፀተ</u>፤ጌታ እግዚአብሔር፤ «ይህም ደግሞ አይፈፀምም» አለ።» ይላል። አምላክ ይፀፀታልን?

10. ኢሳይያስ 7:20 <u>«በዚያን ቀን፤እግዚአብሔር ከወንዝ ማዶ በተከራየው ምላጭ በአሦር ንጉሥ፤ የራሱንና የእግሩን ጠጉር ይላጨዋል፤ ምላጩም ጢሙን ደግሞ ይበላል።»</u> ይላል። አምላክ ምላጭ ይከራያልን? ሁሉን የፈጠረና ዓለሙ ሁሉ የርሱስ አይደለምን? ጸጉር ይላጫልን? ተራ የሰው ማህበራዊ

ድርጊቶችን ሁሉ የፈጣሪ እለታዊ ድርጊት እንደሆኑ አድርጎ መግለፅ ለፈጣሪ ያለንን እሳቤ በብዥታ የተሞላ አያደርግምን?

11. ምሳሌ 30:21-23 «ምድር በሦስት ነገር ትናወጣለች፤ እንዲያውም መሸከም የማትችላቸው አራት ነገሮች ናቸው፤ባሪያ ሲነግሥ፤ሰነፍ እንጀራ ሲጠግብ፤ የተጠላች ሴት ባል ስታገባ፤ሴት ባሪያ በእመቤቷ እግር ስትተካ።» ይላል። ምናለ ባሪያ ቢነግስ? ምናለ የተጠላች ሴት ብታገባ? ሴት ባሪያ በእመቤቷ ብትተካስ? ክርስቲያኖች የሚያመልኩት አምላክ በሰው እኩልነት አያምንምን? ወይስ ይህ የአምላክ ቃል አይደለም?

12. በትንቢት ኢሳይያስ 54:4-5 ላይ «አታፍሪምና አትፍሪ፤ አትዋረጂምና አትደንግጪ፤የሕፃንነትሽንም እፍረት ትረሺዋለሽ፤ የመበለትነትሽንም ስድብ ከእንግዲህ ወዲህ አታስቢውም፤<u>ፈጣሪሽ ባልሽ ነው፤ ስሙም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው።»</u> ይላል። እግዚአብሔር ሚስት ያገባልን? ይህ ለዓለም ፈጣሪ አምላክ የሚገባ ነገር ነውን?

13. ዘፍጥረት 18:20-21 «የሰዶምና ገሞራ ሕዝቦች የሚፈፅሙትን በደል ሰምቻለሁ፤ ኃጢአታቸውም እጅግ ከባድ ነው፤ ስለ እነርሱ የሰማሁት ነገር ሁሉ <u>*እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ወደ እነርሱ እወርዳለሁ*</u>» ይላል። እንዲሁም ዘፍጥረት 11:5 «እግዚአብሔርም የአዳም ልጆች የሠሩትን ከተማና ግንብ ለማየት ወረደ» ይላል። ምን ለማለት ተፈልጎ ይሆን? ታዲያ እግዚአብሔር የሰማውን ለማረጋገጥ እንደ ሰው በቦታው መገኘት ካስፈለገው ምኑን አምላክ ሆነ? ሁሉን ማወቅ ተስኖት? በዚህ አምላክ ነው ክርስቲያኖች የሚያምኑት?

14. ዘጸአት 12:12-13 «እኔም በዚያች ሌሊት በግብጽ ሀገር አልፋለሁ፤ በግብጽም ሀገር ከሰው እስከ እንስሳ ድረስ በኩርን ሁሉ እገድላለሁ፤በግብጽም አማልክት

ሁሉ ላይ እፈርድባቸዋለሁ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ፤ ደሙም ባላችሁበት ቤቶች ምልክት ይሆንላችኋል፤ ደሙንም ባየሁ ጊዜ ከእናንተ እልፋለሁ።» ይላል። እስራኤሎች በግብጻዊያን ባርነት ውስጥ ለ400 ዓመታት ቆይተዋል። በስተመጨረሻም እግዚአብሔር እስራኤሎችን በማዳን ግብጻዊያንን ሊያጠፋ ፈለገ።ይህን ዓላማውን ለማሳካት የተጠቀመበት መንገድ እስራኤሎች የራሳቸውን ቤት ለይቶ ማሳየት የሚችል የደም ምልክት ደጃፉን እንዲቀቡና እርሱም ደሙን ባየ ሰዓት ከነርሱ እያለፈ ሌሎችን ሊያጠፋ ነው። ፈጣሪ ሁሉን አዋቂ አይደለምን? እንዴት የደም ምልክት ካልተጠቀመ አያውቅም እንላለን?

15. 2ኛ ሳሙኤል 22:9-11 «በጨነቀኝ ጊዜ እግዚአብሔርን ጠራሁት፤ ወደ አምላኬም ጮህኩ፤እርሱም ከመቅደሱ ድምፄን ሰማ፤ ጩኸቴም ከጆሮው ደረሰ። «ምድር ተንቀጠቀጠች፤ተናወጠችም፤ የሰማያትም መሠረቶች ተናጉ፤ እርሱ ተቆጥቶአልና ራዱ። ከአፍንጫው የቁጣ ጢስ ወጣ፤ ከአፉ የሚባላ እሳት ነደደ፤ከውስጡም ፍሙ ጋለ። ሰማያትን ሰንጥቆ ወረደ፤ ከእግሩም በታች ጥቅጥቅ ያለ ደመና ነበረ። በኪሩቤል ላይ ተቀምጦ በረረ፤ በነፋስም ክንፍ መጠቀ።» ይላል። ይህ የአምላክ ባህሪ ነውን?

16. ኢሳይያስ 7:18 *‹‹በዚያን ቀን እግዚአብሔር ራቅ ካሉት ከግብጽ ወንዞች ዝንቦችን፣ ከአሦርም ምድር ንቦችን በፉጨት ይጠራል።»* ይላል። እንደዚሁም ‹‹የእግዚአብሔር ቁጣ በሕዝቡ ላይ ነዶአል፤ እጁን አንሥቶ መቶአቸዋል፤ ተራሮች ራዱ፤ ሬሳዎችም በመንገድ ላይ እንደ ተጣለ ጥራጊ ሆኑ፤ ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ቁጣው ገና አልተመለሰም፤ እጁም እንደ ተነሣ ነው። ከሩቅ ያሉትን ሕዝቦች የሚጠራበትን ምልክት ያቆማል፤ ከምድር ዳርቻም በፉጨት ይጠራቸዋል፤እነርሱም እየተጣደፉ በፍጥነት ይመጣሉ።›› (ኢሳይያስ 5:25-26) እውን ይህ የአምላክ ባህሪ ነውን?

17. ምሳሌ 31:5-7 ‹‹ለሚጠፉት የሚያሰክር መጠጥ፣ በስቃይ ላሉትም የወይን ጠጅ ስጧቸው፤ ጠጥተው ድህነታቸውን ይርሱ፤ ችግራቸውንም ከእንግዲህ አያስቡ፡፡›› ይላል፡፡ በመጠጥ ውስጥ በመደበቅ ችግርን መርሳት ዘላቂ መፍትሄ ነውን ? ወይስ ጥፋት? እውን ይህ የአምላክ መጽሐፍ የሚያዘው ነገር ነውን ? አምላክ ወደ ጥፋት ያዛልን?

18. መሳፍንት 1:19 ***‹‹እግዚአብሔር ከይሁዳ ሰዎች ጋር ነበር፤ ስለዚህ ኮረብታማውን አገር ያዙ፤*** ነገር ግን በረባዳው ምድር የሚኖሩት ሰዎች ከብረት የተሠሩ ሠረገሎች ስለነበሯቸው ከዚያ አሳደው ሊያስወጧቸው አልቻሉም፡፡›› ይላል፡፡ የይሁዳ ሰዎች እግዚአብሔር ከነርሱ ጋር ስለሆነ ኮረብታማውን አገር ከያዙ እግዚአብሔር አብሯቸው እያለ እንዴት ከረባዳው ምድር ማስወጣት ተሳናቸው? ጥቅሱ እንደሚለው ‹ከብረት የተሠሩ ሠረገሎች ስለነበሯቸው›? አምላክ ‹ከብረት የተሠሩ ሰረገሎች› ይበግሩታልን? እውን አምላክ የሚሳነው ነገር አለን?

19. ትንቢት ሆሴዕ 1:2 ‹‹እግዚአብሔር በሆሴዕ መናገር በጀመረ ጊዜ፣ እግዚያብሔር ‹ምድሪቱ ከእግዚአብሔር ተለይታ ታላቅ ምንዝርና እያደረገች ስለ ሆነ፣ ሂደህ አመንዝራ ሴት አግባ፤ የምንዝርና ልጆችንም ለራስህ ውሰድ› አለው፡፡›› ይላል፡፡ አምላክ በአመንዝራነት ያዛልን? በዝሙት ላይ የፈጣሪ አቋም ይህ ነውን!?

## የመጽሐፍ ቅዱስ ሕልዉና

ኢስላም በቀድሞ ዘመን ከአምላክ ዘንድ በተወረዱት በኦሪትም ሆነ በወንጌል ሙስሊሞች እንዲያምኑ አስተምሯል::ግና ዛሬ «ወንጌል ፣መጽሐፍ ቅዱስ» ወዘተ በመባል የሚታወቁት መጻሕፍት ትክክለኛዎቹ ከአምላክ(አላህ) የተወረዱት አይደሉም::ተበርዘዋል:: ሰዎች እንዲሁ በእጆቻቸው የጻፏቸው ናቸው ሲል ያስተምራል:: ቁርአን እንዲህም ሲል ይተቻል:-«ለነዚያም መጽሐፉን በእጆቻቸው ለሚጽፉና ከዚያም በርሱ ጥቂትን ዋጋ ሊገዙበት ይህ ከአላህ ዘንድ ነው ለሚሉ ውዮላቸው ለነርሱም ከዚያ እጆቻቸው ከጻፉት ወዮላቸው::ለነርሱም ከዚያ ከሚያፈሩት(ኃጢአት) ወዮላቸው::»(ሱረቱል በቀራህ:79)

በማስከተል በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያሉኝን ጥያቄዎች አብረን እንመልከት:-

1.«እውን ወንጌልን ሐዋርያት ጽፈዋልን?» የሚለው ጥያቄ እንዳለ ሆኖ ሐዋርያት ተብለው በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጹት ግለሰቦችን ስብዕናና ባህሪ ስንመለከት ምን ያህል የነርሱ ጽሑፍ ይታመናል የሚል ጥያቄ ይነሳል? ምክንያቱም ኢየሱስ የሚላቸውን መረዳት ሲሳናቸው ለበርካታ ጊዜ ተስተውሏል::ለምሳሌ ማርቆስ 4፥13፣6፥52፣8፥18-17፣9፥32 ሉቃስ 8፥9 እና ሉቃስ 9፥45ን ማየት ይቻላል:: ሐዋርያቱ ያን ሁሉ «አስደናቂ ተዓምራት አይተዋል» እየተባለ አሁንም ግን ይጠራጠሩ ነበር፤ እንዲያውም ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል 8፥26 ላይ «እናንተ እምነት የጎደላችሁ» ብሏቸዋል:: ታዲያ እምነት የጎደላቸውንና መምህራቸው የሚላቸውን በተደጋጋሚ መረዳት የተሳናቸውን ሰዎች ጽሑፍ እንመን? ነቅተው እንዲጠብቁ አዘዛቸው ግን ተኙ (ማቴዎስ 26፥36-43)፤ ኢየሱስ ሲያዝ ዋሽተው «በጭራሽ አናውቀውም» አሉ (ማርቆስ 14፥66-72)፤ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ «ተሰቀለ» ሲባል እንደለመዱት (ወደ ሥራቸው) ዓሳ ለማጥመድ ወደ ወንዝ ወረዱ (ዮሐንስ 21፥2-3)፤ መጀመሪያውኑ ማን ነው ኢየሱስን የከዳው? ሐዋርያው ይሁዳ አይደለምን? (ማቴዎስ 26፥14-16)

ታዲያ እንዲህ ያሉ ሰዎች ያሉትን ሁሉ አምነን ልንቀበል ይገባናልን? ኢየሱስ ከሞት «ተነሳ» ከተባለ በኋላ አንዷ አየሁት ያለችው መግደላዊት ማርያም በሰባት ሰይጣን ተይዛ የነበረች ሴት ነች (ማርቆስ 16፥9) ሆኖም ተከታዮቹ አላመኗትም (ማርቆስ 16፥10)፤ ኢየሱስ «በሦስተኛው ቀን እነሳለሁ» ብሎ ተነሳ ይላሉ ክርስቲያኖች። ሴቶች ከመቃብር ተመልሰው በመቃብሩ ኢየሱስን ማጣታቸውን ለሐዋርያቶች ነገሯቸው። ነገር ግን ሐዋርያቶቹ «ቅዠት» ስለመሰላቸው አላመኗቸውም። (ሉቃስ 24:11) ሰይጣን ወደ ሐዋርያው ይሁዳ ገባ (ሉቃስ 22፥3)፤ ወደ ሲሞንም ሊገባ ሞከረ (ሉቃስ 22፥31)፤ እንዲሁም ዋናውን ሐዋርያ ጴጥሮስን ኢየሱስ «ሰይጣን» ብሎታል። (ማቴዎስ 16፥23) ታዲያ የነዚህ ሰዎች ጽሑፍና ምስክርነት ይታመናልን?

2.መጽሐፍ ቅዱስን ማን እንደጻፈውና እንዴት እንደተጻፈ በአንድነት ለመጀመሪያ ጊዜ መች እንደተጠረዘና በለተያዩ የክርስትና ቡድኖች መካከል መጽሐፍ ቅዱስን አስመልክቶ ስለተነሳው አለመግባባት ምን ያህል ያውቃሉ? እያንዳንዱን መጽሐፍ ማን እንደጻፈው ያውቃሉን? እንኳን እርሶ «በየዋህነት ልመን» ያሉት ይቅሩና አንድም የክርስትና ምሁር እንደማያውቅ ያውቃሉን? ለአብነት ያህል ስለ ኢየሱስ የሚተርኩትን ወንጌሎች ማን ጻፋቸው? መችና እንዴት ተጻፉ? ለአብነት ዐራቱን ወንጌሎች እንመልከት:-

ሀ) <u>የሉቃስ ወንጌል</u>

1. የሉቃስ ወንጌል 1:1-4 «በእኛ መካከል ስለ ተፈፀሙት ነገሮች <u>ብዙዎች ታሪኩን የተቻላቸው ያህል ጽፈውት ይገኛል</u>፤ ይህም ታሪክ ከመጀመሪው አንስቶ የዐይን ምስክሮች የቃሉ አገልጋዮች የነበሩት ያስተላለፉልን ነው። ክቡር ቴዎፍሎስ ሆይ! <u>እኔም በበኩሌ ሁሉን ከመሠረቱ በጥንቃቄ ከመረመርሁ በኋላ፤ታሪኩን ቅደም ተከተሉን በጠበቀ ሁኔታ ልፅፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ</u>፤ይህንንም የማደርገው የተማርከው ነገር እውነተኛ

መሆኑን እንድታውቅ ነው።» ይላል። ታዲያ ሉቃስ መች በመንፈስ ቅዱስ ተነድቶ ጻፈ? እዚህ ላይ «ብዙዎች ታሪኩን የተቻላቸውን ያህል ጽፈውት ይገኛል» ይላል።ይህ የሚያሳየን የቻሉትን ያህል መጻፋቸውን እንጂ «መንፈስ ቅዱስ ያስፃፋቸውን ያህል» እንዳልፃፉ ነው።ከችሎታቸው ጋር ነው የተያያዘው። ሉቃስስ በመንፈስ ቅዱስ ተነድቼ ፃፍኩ መች አለ? በጥንቃቄ እኔው ፃፍኩ ነው ያለው። ታዲያ ክርስቲያኖች ምን ነካቸው?

2.የክርስትና ምሑራን እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል:- «በሃይማኖት አካባቢዎች «ካኖን» <u>በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር ተጽፈዋል የሚባሉትንና</u> በዚህም ምክንያት በመንፈሳዊነት ረገድ በጣም ዋጋ ያላቸውን መጻሕፍት ያመለክታል። ስለዚህም ነው ከሌሎች በርካታ የክርስቲያናዊ ጽሑፎች የተለዩት። የካኖን ሂደት የተጀመረው በ95 ዓ.ም ገደማ ከመጨረሻ ደቀ መዝሙር (ከዮሐንስ) ሞት በኋላ ሲሆን ለብዙ ዓመታትም ቀጥሏል። የአዲስ ኪዳን ካኖን ውሳኔ በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ የተደረገ ሳይሆን የክርስቲያኖች የጋራ ስምምነት ውጤት ነው። በጣም የቆየው የካኖን ዝርዝር የእስክንድርያው ጳጳስ የሆነው አትናቴዎስ በ387 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ ላይ ይገኛል። በደብዳቤው በአሁኑ አዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙትን 27 መጻሕፍት ዘርዝሯል። <u>የካርታጎው ጉባኤ በ397 ዓ.ም በጉዳዩ ላይ ሳይነጋገር የአትናቴዎስን ዝርዝር አጽድቋል።</u> በአሁኑ ጊዜ «ቅዱሳት መጻሕፍት» ብለን የምንጠራው ካኖን የተጀመረው በአይሁዳውያን ሲሆን አሁን «ብሉይ ኪዳን» ብለን የምንጠራውን 39 መጻሕፍትን ያቀፈ ነው። ዛሬ የካቶሊክ ካኖን 80 መጻሕፍት (በ1545 በትሬንት ጉባኤ የታከሉትን 14 መጻሕፍት ጨምሮ)፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካኖን 81 መጻሕፍትን፣ የፕሮቴስታንትና የግሪክ ኦርቶዶክስ ካኖን 66 መጻሕፍትን ያጠቃልላል።»[26]

---

[26] ዶክተር ፓውል እንዝ፣ታሪካዊ ሥነ-መለኮት ስመጣጡና ትንተናው፣ገጽ 13

3. ስለ ሉቃስ ወንጌል የክርስቲያን ምሑራን እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡- «*ምናልባትም የሉቃስ ወንጌል የተፃፈው በ60 ዓ.ም ገደማ ሳይሆን አይቀርም*፡ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ ሉቃስ ክርስቲያን ከሆነ ቢያንስ አስር ዓመት ወይም ከዚያ በላይ በክርስትና የቆየ ሊሆን ስለሚችልና ኢየሱስን በሥጋ የሚያውቁትን ብዙ ሰዎችን ሊያገኝ ወደሚችልበቱ ወደ ፓለስታይን *ሳይሄድ አልቀረም*፡ ምናልባትም ጳውሎስ በእስር ቤት በነበረበትን ዘመን ሉቃስ የኢየሱስን ምድራዊ ሕይወትና እንቅስቃሴ ለመመዝገብ ብዙ ጊዜ *ሳይወስድበት አልቀረም።* ስለእርሱ ብዙ ከሰማው ተነስቶ ስለ ጳውሎስ ሚስዮናዊ አገልሎትም ብዙ ሳይመረምር አልቀረም።*...የማርቆስን ወንጌል መሠረት በማድረግ ሳይፅፍ እንዳልቀረ ስለሚታመን የሉቃስ ወንጌል የተፃፈው በኀለኛው ዘመን ሳይሆን አይቀርም።* በወንጌሎቹ መካከል ያለው የሥነ ጽሑፍ መመሳሰልን በተመለከተም በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክርስቶስ ይሰብክ የነበረው አንድ ዓይነት የሆነ የወንጌል ስብከትን እንደሆነ *ለመገመት ይቻላል።* ዮሐንስ ማርቆስ በመጀመሪያ ከበርናባስና ከሳኦል ጋር ወደ አንፆኪያ በሄደ ጊዜ ሉቃስና ማርቆስ እዚያው ተገናኝተው *የቆየ ትውውቅ ሳይኖራቸው አይቀርም።* *60ኛው ዓ.ም የሉቃስ ወንጌል የተፃፈበት ጊዜ ነው ብሎ በርግጠኝነት መናገር ባይቻልም ተቀራራቢው ዓመት ነበር ብሎ መውሰድ ግን ይቻላል።* *የሉቃስ ወንጌል የት ቦታ እንደተፃፈ የተሰጠ አንዳችም ፍንጭ የለም። ምንም እንኳ ታሪኮቹ በቂሣሪ ሊጠናቀሩ ቢችሉም ከፓለስቲና ውጪ ሳይፃፍ እንዳልቀረ ግን ይገመታል። ሮምን ቂሣሪያን፣ አካይን፣ ትንሹ እስያን እና አሌክሳንደሪያን ጨምሮ የሚሰጡት ከግምታዊ አስተያየትነት አይዘሉም።»*[27]

4. የክርስትያን ምሑራን እንዲህ ይላሉ፡- «የጳውሎስ የወንጌል አገልግሎት ባልደረባ የነበረው ሉቃስ የዚህ ወንጌል ደራሲ መሆኑን ሁሉም የጥንት የቤተ ክርስቲያን አባቶች በአንድ ድምጽ ይስማሙበታል። *ምሑራን ሉቃስ*

---

[27] ቲም ፈሎስ ፣የአዲስ ኪዳን የጥናት መምሪያና ማብራሪያ፣በትምህርተ መስኮተ ማስፋፊያ (ት.መ.ማ) መልክ የተዘጋጀ፣2ኛ መጽሐፍ ጽሑፍ፣ ገጽ 339

<u>የዚህ ወንጌል ጸሐፊ መሆኑን መጠራጠር የጀመሩት ባለፉት 100 ዓመታት ውስጥ ብቻ ነው።</u> እነዚህ ምሑራን ጥርጣሬያቸውን ያቀረቡት ከሉቃስ ዘመን በኋላ ስለ ተነሱት የቤተ ክርስቲያን ችግሮች የሚዘግቡ አሳቦች በመጽሐፉ ውስጥ እንደሚገኙ በመግለጽ ነው።... <u>እንደ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ባለታሪኮች ሁሉ ስለ ሉቃስም ያለን መረጃ የተወሰነ ነው።»</u>[28]

5.የክርስቲያን ምሑራን እንዲህ ይላሉ:- «ሉቃስ አይሁድ አልነበረም፣ ይህም አንድን ሙሉ መጽሐፍ የጻፈ ብቸኛው አሕዛብ ያደርገዋል <u>።የት ተወልዶ እንዳደገ አናውቅም</u>። ... በተጨማሪም ሉቃስ ጥሩ የታሪክ ጸሐፊ ነበር። *<u>ምንም እንኳ ኢየሱስን በዓይኑ ባያየውም፣ ሉቃስ እንደ አንድ የታሪክ ጸሐፊ ስላመነበት ስለ ክርስቶስ ጥንቃቄ የተሞላበትን ጥናት አድርጓል።</u>* ... ሉቃስ ይህንኑ መረጃ ለማግኘት የተጠቀመባቸውን መንገዶችን ይዘረዝርልናል። አንደኛው፣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚናገሩ መዛግብትን አገላብጧል። ምናልባትም ከእነዚህ መዛግብት መካከል የማቴዎስና የማርቆስ ወንጌላት ይገኙበት ይሆናል።ሁለተኛው፣የዓይን ምስክሮችንና የተከበሩ የቤተክርስቲያን መሪዎችን ቃለ መጠይቅ አድርጓል።...*<u>ሁሉንም መረጃ ከሰበሰበና ታሪኮቹን ፈር ካስያዘ በኋላ፣ሉቃስ ስለክርስቶስ በሚጽፈው መጽሐፍ ውስጥ የትኞቹ መካተት እንዳለባቸው ወሰነ።</u>*»[29]

*6.*የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት እንዲህ ይላል:- *<u>«የሉቃስ ወንጌል የተጻፈው በ60 ዓ.ም ገደማ ይመስላል።»</u>*[30]

ከላይ ያየናቸው የክርስቲያን ምሑራን ሁሉም በስምምነት የጻፉት በጥርጣሬና ግምት ላይ ተመስርተው ነው።በመላምት ተንተርሰው ነው። ታዲያ «ይሆናል»፣ «ይገመታል»፣«ሊሆን ይችላል»፣«ይመስላል» ፣ «ሳይሆን

---

[28] ቲም ፊሉስ ፣የአዲስ ኪዳን የጥናት መምሪያና ማብራሪያ፣በትምህርተ መስኮተ ማስፋፊያ (ት.መ.ማ) መልክ የተዘጋጀ፣2ኛ መጽሐፍ ጽሑፍ ፣ገጽ 336

[29]ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ ፣ገጽ 337

[30] የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ገጽ 5

አይቀርም» በሚሉ መላምቶች ተመስርተን እንዲሁም በማንና መቼ እንደተጻፈ ስምምነትና ተጨባጭ ማስረጃ በሌለበት የሉቃስ ወንጌል «የአምላክ ቃል ነው፤ በመንፈስ ቅዱስ ተነድቶ ጻፈ» ወዘተ ብለን በድፍረት መከራከር ከቶ እንደምን ይቻላል?

ለ) <u>የዮሐንስ ወንጌል</u>

ስለ ዮሐንስ ወንጌል በክርስቲያን ምሁራን ከተጻፉት ዉስጥ የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከታለን፡፡

1. የክርስትና ምሁራን እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡- «<u>በዮሐንስ ወንጌልና በሌሎቹ ሦስት ወንጌላት መካከል በግልጽ የሚታይ ልዩነት በመኖሩ የወንጌሉ ተአማኒነት አጠያያቂ እንዲሆን ምክንያት ሆኗል</u>፡፡ መልሱ ያለው ግን በወንጌሉ ምንጭና ዓላማ ላይ ነው፡፡ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ትውፊት መሠረት ይህ ወንጌል የተጻፈው በዘብዴዎስ ልጅ በዮሐንስ እንደሆነ ይታመናል፡፡የዘብዴዎስ ልጅ ዮሐንስ የመጨረሻ የሕይወት ዘመኑን ያሳለፈው በኤፌሶን ሲሆን ከጌታ ሐዋርያት መካከል የመጨረሻው ሰው ነበር፡፡<u>ምንም እንኳ ይህ አባባል ተቃውሞ ቢገጥመውም እስከ ዛሬ ድረስ ከተሰነዘሩ ሌሎች መላምቶች ውስጥ ይሄኛው ይበልጥ ተቀባይነት አለው፡፡ በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት መጨረሻ አካባቢ ስለ ነበረችው የጥንት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሚታወቀው በጣም በጥቂቱ በመሆኑ፤ የዚህን ወንጌል አወቃቀር አስመልክቶ የሚነሱ ጥያቄዎችን ለመመለስ እጅግ አስቸጋሪ ሆኗል፡፡</u>»[31]

2. የክርስትና ሃይማኖት ምሁራን የሚከተለውን ጽፈዋል፡- «<u>ከአራቱ ወንጌሎች የትኞቹም ስለ ጸሐፊው የሚናገሩት ነገር እንደሌለ ቀደም ብለን ተመልክተናል፡፡</u> <u>ነገር ግን ይህ መጽሐፍ ከተጻፈ በኋላ ብዙም ሳይቆይ «የዮሐንስ ወንጌል» የሚል ስያሜ ተሰጠው፡፡</u> በዚህ መንገድ አንባቢያን

---

[31] ሜሪል ሲ. ቴኒ ፣የአዲስ ኪዳን ቅኝት፣አሳታሚ ፡-የኢትዮጵያ ቃ ሕይወት ቤተክስቲያን የኮሚዮኒኬሽንና ሥነ ጽሑፍ መምሪያ፣ገጽ 281

ፀሀፊው ማን እንደሆነ ሊያውቁ ይችላሉ።*ከጥንት ጊዜ አንሥቶ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የዘብዴዎስ ልጅ የሆነው ዮሐንስ አራኛውን ወንጌል እንደጻፈ ያምኑ ነበር። ይህ አመለካከት በአብዛኛው የቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ተይዞ ቆይቷል። ... ዛሬ ግን ብዙ ወንጌላውያን የሆኑ ምሑራን ይህንን ወንጌል ዮሐንስ እንደጻፈው ይጠራጠራሉ።*»[32]

3. ቲም ፌሎስ የተባሉ የክርስትና ምሑር የሚከተለውን ጽፈዋል፡- «በዮሐንስ ወንጌል ፀሀፊ ማንነት ላይ የሚደረገው ክርክር የተጻፈበትን ጊዜና ቦታ ይወስነዋል።*ይህ ወንጌል ወደ በኋላ እንደተጻፈ የሚያስቡ ሰዎች ጊዜውን ወደ 150 ዓ.ም. አከባቢ ይወስዱታል። ሌሎች ደግሞ የዮሐንስ ወንጌል ከ50-70 ዓ.ም. መጀመሪያ ከተጻፉት መጻሕፍት አንዱ እንደሆነ ይናገራሉ። ነገር ግን ደራሲው አዛዉንቱ ዮሐንስ ነው የሚሉትን ጨምሮ አብዛኛዎቹ ምሑራን ከ85-95 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ እንደተጻፈ ይስማማሉ።*»[33]
ስለዮሐንስ ወንጌል ካሉት አለመግባባቶች መካከል ለአብነት ከላይ አይተናል። ነገር ግን ተራው አማኝ እርግጠኝነት እንዲሰማው ስለተደረገ በጭፍን ሲከራከር ይስተዋላል።ወንጌሉ በማንና መቼ እንደተጻፈ ቁርጥ ያለ መረጃ በሌለበት ተዓማኒነቱ አጠያያቂ በሆነበት ሁኔታ «የአምላክ ቃል ነው። በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ጻፉት» ወዘተ ማለት ምን ያህል ያዛልቃል? የወንጌሉ ተአማኒነት ላይ ጥያቄ እያለ እንዲህ ያለውን መረጃ በመሰወር «ተራውን አማኝ» ማደናገር ለምን አስፈለገ?

## ሐ) የማቴዎስ ወንጌል

1. ስለ ማቴዎስ ወንጌል በክርስቲያን ምሑራን የሚከተለው ተጽፏል፡- «የማቴዎስ ወንጌል፡- *«ወንጌሉን የፃፈው ማቴዎስ ነው»» ያሉት የቀደሙ የቤተክርስቲን አባቶች ናቸው እንጂ የፃፊው ስም አልተፃፈበትም። መቼ*

[32] ቲም ፈሎስ ፡የአዲስ ኪዳን የጥናት መምሪያና ማብራሪያ፡ በትምህርተ መስኮተ ማስፋፊያ (ት.መ.ማ) መስክ የተዘጋጀ፡1ኛ መጽሐፍ ጽሑፍ ፡ገጽ 440
[33] ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ፡ገጽ 444

እንደተጻፈ ደግሞ አልታወቀም። ቲቶ (ጥጦስ) በሚባል በሮማ መንግስት የጦር መሪ እጅ ኢየሩሳሌም የፈረሰችው በ70 ዓ.ም ሲሆን ወንጌሉ ከዚያ በፊት ወይም ከዚያ በኋላ ተፅፎ እንደሆነ መምህራን አልተስማሙበትም። በ60 ዓ.ም እና 80 ዓ.ም መካከል ሳይፃፍ አይቀርም ይባላል።»[34]

2.ስለ «የማቴዎስ ወንጌል» ጸሐፊ ክርስቲያን ምሁራን ሲገልጹ ፡- «ከስሙ እና ከሚሰራው ሥራው በቀር ስለዚህ ሰው በውል የታወቀ ነገር የለም። ይህ ሰው በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ከሐዋርያት የስም ዝርዝር ውስጥ ከመጠቀሱ በስተቀር (የሐዋ.ሥራ 1:13) ታሪኩን በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በግልጽ አናገኘውም። በአፈ-ታሪክ ጽሑፎች ውስጥ ግን የተባሉ ነገሮች መኖራቸውን ልብ ይሏል። በወንጌሉ ውስጥ ማቴዎስ ጸሐፊው እንደሆነ በግልጽ አልተነገረም።»[35]

3. ስለዚሁ ወንጌል የሚከተለውም ተጽፏል፡- «ወንጌሉ የተጻፈበት ሥፍራ አንጾኪያ ሊሆን ይችላል። ... በተጨማሪም በአንጾኪያ የነበረችይቱ ቤተ ክርስቲያን በአመዛኙ አሕዛብን በውስጧ በማቀፏ የመጀመሪያዋ ስትሆን ወንጌሉም የት ተጻፈ ለሚለው ሁነኛ ማረጋገጫ ባይገኝለትም ከአንጾኪያ የተሻለ ተስማሚ ቦታ ግን አይታሰብም፤ ...ስለዚህ ወንጌሉ ከ50-70 ዓ.ም. ባሉ ጊዜያት መካከል ሳይጻፍ እንዳልቀረና በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚሰሩትና በዚያች ቤተ ክርስቲያን በሆኑቱ መካከል እንደተሰራጨ ይገመታል።»[36] ታዲያ እንዴት በግምትና በ «ሊሆን ይችላል»፣ በአፈ-ታሪክና የክርስቲያን ምሁራን ራሳቸው ባላወቁትና ባልተስማሙበት ጽሑፍ እንዴት «የአምላክ ቃል ነው፤ እመኑ።» ይባላል?

---

[34] የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፤የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ፤ገጽ 41
[35] ሜሪል ሲ. ቴኒ ፡የአዲስ ኪዳን ቅኝት፡ ገጽ 217
[36] ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ፡ገጽ 220

መ) <u>የማርቆስ ወንጌል</u>

4. የክርስቲያን ምሁራን ስለ «የማርቆስ ወንጌል» የሚከተለውን ጽፈዋል:- <u>«ከሌሎች ጋር ሲነጻጸር ስለዚህኛው ወንጌል ጸሐፊ ብዙ የሚታወቅ ነገር የለም:: መጽሐፉ በየትኛውም ሥፍራ ስሙን አይጠቅስም!</u>...የቤተክርስቲያን ታሪክ እንደሚገልጸው ጸሐፊው የክርስቲያን ቤተሰብ አባል የሆነ ዮሐንስ ማርቆስ መሆኑንና የጳውሎስ፣ የበርናባስና ምናልባትም የጴጥሮስ ረዳትና ተማሪ <u>ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል::»</u>[37]

5. ስለማርቆስ ወንጌል የሚከተለውን ምሁራን ጽፈዋል:- «የማርቆስ ወንጌል ደራሲው (ጸሐፊው) በሮማይስጥ ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ ነው (የሐዋ 12፤12:25..15:37):: <u>መጀመሪያ የተፃፈው ወንጌል ይህ ሳይሆን አይቀርም::</u> የቀደሙት የቤተክርስቲያን አባቶች በሮሜ ተጽፎአል ! <u>የተጻፈውም በ60ዓ.ም ገደማ ይመስላል ይላሉ::»</u>[38]

የተጨበጠ ማስረጃ በሌለበት በመላምትና በግምት «የማርቆስ ወንጌል የአምላክ ቃል ነው» ማለት ይቻላልን? «ወሳኝ» የሚባሉት አራቱ ወንጌላት ይህን ያህል አጨቃጫቂ፣ ስምምነት የሌለባቸውና ፀሀፊያቸው እንኳ ያልተወቀ ከሆነ የሌሎቹ መጻሕፍት እጣ ፈንታ ምን ሊሆን ይችላል?

6. ለመሆኑ «መጽሐፍ ቅዱስ» (ብሉይና አዲስ ኪዳን) የሚባለው መጽሐፍ ከየት ተገኘ? የክርስቲያን ምሁራን እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል:- <u>«ከመጀመሪያ ጀምሮ ቤተክርስቲያን አይሁድ ያወቋቸውን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ተቀበለች:: በሐዋርያት ወይም በሐዋርያት ሥልጣን የተፃፉትን መጻሕፍት ሰብስባ እንደ እግዚአብሔር ቃል ተቀበለቻቸው:: የቤተክርስቲያን አባቶች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን እየጠቀሱ አስተማሩ:: ቅዱስ አትናቴዎስ በ367</u>

---

[37]ሚሪል ሲ. ቴኒ ፣የአዲስ ኪዳን ቅኝት፣ገጽ 236

[38]የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፤የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ገጽ 39

<u>ዓ.ም[39] በፃፈው በፋሲካ ዕለት ቃል በረከት የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሃያ ሰባት ብቻ መሆናቸውን ተናግሮአል። እንደዚሁም በ397 ዓ.ም በካርታጎ (በካርቴጅ) የተደረገው ሲኖዶስ ሃያ ሰባቱን መጻሕፍት አፀደቀ።»[40]</u>

ከዚህ የምንረዳው ቤተክርስቲያን ከመጽሐፉ ቀድማ መመሥረቷን፣«ብሉይ ኪዳን» የሚባለው ከአይሁድ እንደተገኘና ሃያ ሰባቱ (የአዲስ ኪዳን) መጻሕፍት በ397 ዓ.ል በካርቴጅ ጉባኤ መጽደቃቸውን ነው። ለመሆኑ ክርስቲያኖች «ብሉይ ኪዳን» የሚባለውን መጽሐፍ ከአይሁድ ሲቀበሉ («እነርሱ መጽሐፉን ጠብቀው ስላቆዩ») በብሉይ ኪዳን ስለ ሥላሴ፣ ስለ ኢየሱስ መሰቀልና ሌሎችም ክርስቲያኖች የሚያምኑባቸውን እንዲሁም «መጽሐፉን ጠብቀው ያቆዩት» አይሁዶች የማይቀበሉትንና ፈጽሞ ሐሰት በማለት የሚያስተባብሉትን እምነት እንዴት «መጽሐፉን ጠብቀው ካቆዩት» ልቀው ክርስትናን በትንቢቱ አረጋግጠው ተቀበሉ? ሃያ ሰባቱን መጻሕፍት የአምላክ ቃላት ናቸው ብሎ በምን መስፈርት ሊቀበሉ ቻሉ? ይህ ራሱ አቋም ከያዙ በኃላ መጻሕፍቱን እንደተቀበሉ አያሳይምን?

ይህ ጉባኤ በ397 ዓ.ል መካሄዱ ራሱ ከዚያ በፊት «የትኞቹ መጻሕፍት የአምላክ ቃል ናቸው?» «የአዲስ ኪዳን አካል ናቸው?» የሚለው በውል አለመታወቁን አይገልጽምን? የኒቂያ ጉባኤ ራሱ የተካሄደው በ325 ነው። ይህም ማለት ይህ መጽሐፍ በ397 የጸደቀበት የካርቴጅ ጉባኤ ሳይካሄድ 72 ዓመታት አስቀድሞ ነው። እምነቱ በ325 ተወሰነ።መጽሐፉ በ397 ተቀባይነት አገኘ! በ 325 ከተወሰነው እምነት ጋር የሚሄደውን (የሚስማማውን) ብቻ መርጠው እንደሆነስ?

---

[39] ከላይ እንዳየነው በዶክተር ፓውል እንዝ የተጻፈው «ታሪካዊ ሥነ-መለኮት አመጣጡና ትንተናው» የሚለውን መጽሐፍ አትናቴዎስ በ387 ዓ.ም እንደጻፈ ገልጸዋል። ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ጊዜውን 367 ያደርገዋል። ይህ የሚያሳየው 27ቱን የአዲስ ኪዳን መጻሐፍት በደብዳቤው ላይ ጻፈ የሚባለው አትናቴዎስ የጻፈበት ጊዜም በውል አለመታወቁን ነው። ይህንን ነው እንግዲህ የካርቴጅ ጉባኤ ሳይወያይ ያጸደቀው።
[40] የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ገጽ 35

7. የክርስቲያን ምሁራን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚከተለውን ጽፈዋል:- «መጽሐፍ ቅዱስ፤ የተቀደሰ ወይም የተለየ ማለት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ የቅዱሳት መጻሕፍት መዝገብ ነው::የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን ናቸው:: ብሉይ ኪዳን ከ1400-400 ከክርስቶስ በፊት በልዩ ልዩ ቦታዎች፣አርባ በሚያህሉ ልዩ ልዩ ጸሐፊዎች እንደተጻፈ ይነገራል::»[41] አርባ ሰዎች የጻፉት የመጻሕፍቶች ስብስብ ከክፍለ ዘመናት በኃላ በአንድነት ተጠረዘ:: እንዲያው የአንዱ መጽሐፍ ጸሐፊ «በመንፈስ ቅዱስ ተነድቶ» መጽሐፉን ቢገልፅ ይህ በሌሎች 39ኙ ሰዎች ተጽፈው በኋላ ላይ በአንድነት አብረው የተጠረዙትን ሁሉንም ሊወክል ይችላልን? መጽሐፍ ቅዱስ በአርባ ሰዎች የተጻፉ መጻሕፍት ስብስብ አይደለምን?

8. ለአብነት «የማቴዎስ ወንጌልን የጻፈው ቀረጥ ሰብሳቢው ማቴዎስ ነው» ተብሎ ይታመናል:: ነገር ግን በቀላሉ በእርሱ እንዳልተጻፈ መረዳት ይቻላል:: በማቴዎስ 9፥9 ላይ «ኢየሱስ ከዚያ ቦታ ተነስቶ ሲሄዱ ሳለ ማቴዎስ የተባለውን ቀራጭ በቀረጥ መቀበያ ስፍራ ተቀምጦ አየውና «ተከተለኝ!» አለው:: ማቴዎስም ተነስቶ ተከተለው» ይላል:: ማቴዎስ ይህን ቢጽፍ «ተቀምጦ አየው» ሳይሆን «ተቀምጬ አየኝ» ፣«ተነስቶ ተከተለው» ሳይሆን «ተነስቼ ተከተልኩት» ወዘተ እያለ ነበር የሚጽፈው:: እንዴት ራሱን ሦስተኛ ወገን አድርጎ ያቀርባል?

9. የመጽሐፍ ቅዱስን ግርጌ ልብ ብለን ብናይ (በተለይ የ1980ውን የቀላል ትርጉም እትም) በተለያዩ መጽሐፍ ቅዱሳት መካከል ልዩነት መኖሩን አንዱ ጥቅስ በሌላኛው መጽሐፍ ቅዱስ አለመኖሩን፣በጥንት ቅጂ ያለው ከዚህኛው እንደሚለይ፣ ተጨማሪ ቃል፣ ሀረግ፣ ዐረፍተ ነገር እንዳለው አልያም እንደተጨመረ በብዛት ይገልጻል:: ይህ ምንን ያሳየናል? በመጽሐፍ ቅዱስ መካከል ልዩነት፣ ቅራኔ እና ግጭት መኖሩን አያሳምን? ታዲያ ይህ ሁሉ እያለ ክርስቲያኖች እንዴት በየዋህነት ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥብቅና ይቆማሉ?

---

[41] የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፤የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤ገጽ 34

10. የዛሬዎቹን አራቱን ወንጌሎች ስናይ በአብዛኛው «የኢየሱስን ታሪክ» ነው የሚተርኩት። ስለ አወላለዱ፤ስለ አሰባበኩ እና ስለደረሰበት ችግር ወዘተ. ያወራሉ።ነገር ግን ኢየሱስ በሚከተሉት ስፍራዎች የሚያስተምረው (የሚሰብከው) ከአምላክ እንደሰጠው ገልጿል:-

- «እኔ ከራሴ አልተናገርሁም፤ነገር ግን የላከኝ አብ ምን እንደምናገርና እንዴት እንደምናገር አዘዘኝ።የእርሱ ትእዛዝ ወደ ዘላለም ሕይወት እንደሚያደርስ አውቃለሁ፤ስለዚህ የምለው ሁሉ አብ እንድናገረው የነገረኝን ነው።» (ዮሐንስ 12:49-50)
- «ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ «የማስተምረው ትምህርት ከራሴ ሳይሆን፤ከላከኝ የመጣ ነው። ማንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ቢፈልግ፤የእኔ ትምህርት ከእግዚአብሔር ወይም ከራሴ የመጣ መሆኑን ለይቶ ያውቃል።» (ዮሐንስ 7:16-17)
- «ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ «የሰው ልጅን ከፍ ከፍ ባደረጋችሁ ጊዜ፤ ያ ያልሁት እርሱ እኔ እንደምናገር፤ በራሴም ፈቃድ ምንም እንደማላደርግ ታውቃላችሁ፤» (ዮሐንስ 8:28)
- «ይህ የምትሰሙት ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም።» (ዮሐንስ 14:24)
- «እግዚአብሔር ለእርሱ የሰጠው የኢየሱስ ክርስቶስ ራዕይ ይህ ነው» (የዮሐንስ ራእይ 1:1)

«ወንጌል» ማለት ለኢየሱስ ከአምላክ የተሰጠውና የሰበከው ከሆነ እንዲሁም ዛሬ ያሉት ወንጌሎች «ትክክለኛ ናቸው» ከተባለ ኢየሱስ ከአምላክ የተሰጠውና የሰበከው ስለ አወላለዱና የሕይወት ታሪኩ ነበርን? እንዴት እንደተወለደ፣ እንዴት እንደሚሰቃይ ወዘተ. ነበርን? ምክንያቱም አራቱ «ወንጌሎች» ይህንን ነው በአብዛኛው የሚተርኩት።

11. ዮሐንስ 20:30-31 «ኢየሱስ በዚህ መጽሐፍ ያልተፃፈ ሌሎች አያሌ ታምራዊ ምልክቶችን በደቀ መዛሙርቱ ፊት አድርጓል ። ነገር ግን ኢየሱስ

እርሱ ክርስቶስ፤ የእግዚአብሔርም ልጅ እንደሆነ እንድታምኑ ዘንድ ፤ አምናችሁም በስሙ ሕይወት እንዲኖራችሁ ይህ ተጽፎአል» ይላል:: ታዲያ የኢየሱስ ታሪክ በሙሉ አልተፃፈም ማለት ነውን? ታዲያ ሙሉ ሳይሆን ይህ የተጻፈው ለምን ይሆን? ወይስ ሌሎች በርካታ በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ያልተጻፉ ታሪኮች ኢየሱስ ተዓምር ሲያሳይ ስለ አምላክ የተናገራቸውና ጸሐፊዎቹ እንዳናውቅ የፈለጉት ነገር ኖሮ ይሆን?

12. የትኞቹ መጽሐፍት ናቸው «ቅዱሳን» በሚለው ላይ ብርቱ ክርክር ነበር፤ በመጨረሻም ጉዳዩ በድምጽ ብልጫ ነው የተወሰነው:: ክርክር መነሳቱ በራሱ ዛሬ ባሉት መጻሕፍት ላይ ጥቂትም ቢሆን ጥርጣሬን አያጭርምን?

13. በማቴዎስ 16:28 ላይ «እውነት እላችኋለሁ፣ የሰው ልጅ በመንግስቱ ሲመጣ እስኪያዩ ድረስ እዚህ ከሚቆሙት ሞትን የማይቀምሱ እንዳንዶች አሉ::» ይላል:: ነገር ግን እንኳን ኢየሱስ ተመልሶ ሲመጣ ሊያዩ ይቅርና ያኔ ከነበሩት ውስጥ አንድም ሰው ያን ክፍለ ዘመን የተሻገረ የለም:: በዚያው ክፍለ ዘመን ሞትን ያልቀመሰ የለም:: ሁሉም ያኔ ጥንት ነው! ከ1900 ዓመታት በፊት ነው ሁሉም ያለቁት:: ታዲያ ጥቅሱ ስህተት ነውን?

14. በቀላል ትርጉም የ1980 እትም መጽሐፍ ቅዱስ የማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 16 ቁጥር 8 ሥር በቀረበው የግርጌ ማስታወሻ ላይ «በአንዳንድ የጥንት መጽሐፍት በዚህ ምዕራፍ በቁጥር 8 ቀጥሎ ያለው ቃል ይገኛል» ይልና የሚከተለውን አስፍሯል:- «ሴቶቹ ወደ ጴጥሮስና ወደ ጓደኞቹ ሄደው መልእክቱ የነገራቸውን ሁሉ አወሩላቸው፤ ከዚህ በኋላ _ኢየሱስ ራሱ ለዘላለም ድነት የሆነውን የማይለወጠውንና ቅዱስ ወንጌል ከፀሐይ መውጫ እስከ መጥለቂያው ድረስ በደቀ መዛሙርቱ አማካኝነት ላከ::»_ ይላል:: ያ የተላከው ወንጌል የት ሄዶ ነው ሌላ የተጻፈው? ጠፋ? በጉባኤና በድምጽ ብልጫ ዉድቅ ተደረገ?

15. የኢየሱስ ተከታዮች ጠላት የነበረው ሳዉል(በኃላ ጳውሎስ የተሰኘው) አማኞን አሳዷል። እንዲታሰሩ ተስማምቷል። በኃላ ላይ ጳውሎስ «ኢየሱስ ተገልጦልኛል፣ሐዋርያ ነኝ» ብሎ ስለ ራሱ ተናገረ።ተቀበሉት።ግና በ1ኛ ቆሮንቶስ 8:40 ላይ «እኔም ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ያለ ይመስለኛል።» ብሏል። እምነት በይመስለኛል ያስኬዳልን?

16. ጳውሎስ በ2ኛ ጢሞቲዎስ 2:8 ላይ «ከሙታን የተነሣውን፣ከዳዊት ዘርም የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን አስብ፣ የእኔም ወንጌል ይኸው ነው።» ብሏል። ጳውሎስ «የእኔም ወንጌል ይኸው ነው።» ሲል እርሱም ወንጌል አለው እንዴ? የሌሎቹ ወንጌልስ? እንዲሁም ጳዉሎስ «በክርስቶስ ፀጋ የጠራናችሁን እርሱን ትታችሁ፣ወደ ተለየ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ መዞራችሁ ደንቆኛል።»(ገላትያ 1:6) ብሏል።ጳዉሎስ ይህንን ሲናገር ዛሬ የምናውቃቸው አራቱም «ወንጌላት» (የማቴዎስ ፣የማርቆስ፣የሉቃስና የዮሐንስ ወንጌላት) አንዳቸውም አልተጻፉም ነበር። ይህንን ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትም ሆነ ስለ መጻሕፍቶቹ አጻጻፍ ቅደም ተከለትል ከሚገልጹ መጻሕፍት መረዳት ይቻላል።ታዲያ ጳውሎስ «የእኔም ወንጌል» እና «ወደ ተለየ ወንጌል» ሲል የጠራቸው ወንጌላት የትኞቹ ናቸው? ሉቃስ 1:1-4 ላይ «በእኛ መካከል ስለ ተፈፀሙት ነገሮች ብዙዎች ታሪኩን የተቻላቸው ይህል ጽፈውት ይገኛል፣ይህም ታሪክ ከመጀመሪያው አንስቶ የዐይን ምስክሮች የቃሉ አገልጋዮች የነበሩት ያስተላለፉልን ነው። ክብር ቴዎፍሎስ ሆይ! እኔም በበኩሌ ሁሉን ከመሠረቱ በጥንቃቄ ከመረመርሁ በኃላ፤ታሪኩን ቅደም ተከተሉን በጠበቀ ሁኔታ ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ፤ ይህንንም የማደርገው የተማርከው ነገር እውነተኛ መሆኑን እንድታውቅ ነው።» ብሏል።በዚሁ ጥቅስ ላይ «ብዙዎች ታሪኩን የተቻላቸው ይህል ጽፈውት ይገኛል» ያለው ይሁን ሌላኛው ወንጌል? ወንጌሎቹ አንድ አይነት ከሆኑና ልዩነት ከሌላቸው ጳውሎስ ለምን «ወደ ተለየ ወንጌል» ሲል ወቀሳቸው? ሉቃስ «ብዙዎች ታሪኩን የተቻላቸው ይህል ጽፈውት ይገኛል» ሲል ብዙ ሰዎች የኢየሱስን ታሪክ እንደጻፉ ነግሮናል። ታዲያ እነዚያ ብዙዎቹ የጻፉት የት ገቡ?

17. እውን መንፈስ ቅዱስ ነድቶ የወንጌልን ጸሐፊዎች እንዲጽፉ ካደረገ ለምን አራት ጊዜ ስለ አንድ ታሪክ መጻፍ አስፈለገ? አንዱ የረሳውን ሌላኛው እንዲሞላው? ወይስ ወንጌሎች ሲጋጩ እንድናነብ ፈልጎ ይሆን?

18. የሐዋርያት ሥራ 20:35 ላይ «በጉልበታችን ደክመን ችግረኞችን መርዳት እንዳለብን ባደረግሁት ሁሉ አሳይቻለሁ፤ «ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው» ያለውን የጌታ የኢየሱስን ቃል እናስታውስ።» ይላል። ነገር ግን ኢየሱስ ይህንን ያለበት ሥፍራ በአራቱም ወንጌሎች ውስጥ ቢፈለግ አይገኝም። ታዲያ ጳውሎስ ከየትኛው ወንጌል ይሆን ይህን ያገኘው? ምናልባት በጉባኤና በድምፅ ብልጫ ካልተመረጡት ወንጌላት መካከል ይሆንን?

19. ወንጌሎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተጻፉ ብለው ያምናሉን? ወንጌሎቹ ይህንን ያረጋግጣሉን? እንደውም በተቃራኒው ቢያረጋግጡስ?

20. ጳውሎስ ደብዳቤዎቹን ያኔ ጽፎ ሲልክ ዛሬ እንደሆነው ለዓለም አስቦ ነበርን? ቢሆንማ ለምን አንዱም ቢሆን ለኢትዮጵያ/አፍሪካ ወዘተ አልላከም? የተጻፈው ለዓለም ከሆነ ለምን «ለቆሮንቶስ»፣ «ለሮሜ»፣ «ለገላትያ»፣ «ለኤፌሶን ሰዎች» ወዘተ ተላከ?

21. እውን ክርስቲያኖች እንደሚሉት እያንዳንዱ መጻሕፍት በመንፈስ ቅዱስ መጻፉን ቢያረጋግጡ ኖሮ የትኞቹን መቀበል እንዳለባቸው ለመወሰን ለምንስ በቀደምት ቤተክርስቲያን በርካታ ጭቅጭቅና ጉባኤ ተደረገ? ለምንስ ሰው ሰራሽ መስፈርት ለአምላክ ቃል ተቀመጠ? ለምንስ በድምፅ ብልጫ ፀደቀ? ለምን ዛሬም ድረስ የልዩነት ምንጭ ሆነ?

22. እውን መጻሕፍቶቹ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፉና ይህንንም የሚያረጋግጡ ከሆኑ ለምን ዛሬም ድረስ በኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክ እና ፕሮቴስታንት የተለያየ መጽሐፍ ቅዱስ አገልግሎት ላይ ዋለ? ለምንስ ነው ዛሬም ድረስ ስምምነት ላይ ሊደረስ ያልተቻለው?

23. ኦሪጂናል መጽሐፍ ቅዱስ እንደሌለ ያውቃሉን? ይህንንማ ለነገሩ ክርስቲያኖችም አያስተባብሉም:: ቢኖርማ ለምን ከበርካታ መጻሕፍት መካከል ለመለየት የድምፅ ብልጫ ይደረግ ነበር? ክፍፍል ጭቅጭቅ፣ ልዩነት ይከሰት ነበርን?

24. ከበርካታ መጻሕፍቶች መካከል ዛሬ የሚገኘውን ሲመርጡ የአምላክን ቃል በምን ሚዛን ለዩት? እውነትና ሐሰት የሚለየው አምላካዊ አስተምህሮት የሚረጋገጠው ያ የሚመረጠው መጽሐፍ ሆኖ ሳለ ለምን ወደ ድምፅ ብልጫ ተገባ?

25. ክርስቲያኖች ስለእምነታቸው አቋም ይዘው ነው መጻሕፍቶችን የመረጡት ወይስ መጽሐፍቶቹን ከመረመሩ በኋላ ነው አቋም የያዙት?

26. «አጭሩ»ና «ረጅሙ» የሚባሉ የማርቆስ ወንጌሎች እንዳሉ ያውቃሉን? አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሶች የማርቆስ ወንጌልን በ16:8 ሲያቆሙ ረጅሙ ደግሞ በ16:20 ይጠቃለላል:: ይህ ለምን ሆነ? እንዴት ተለያዩ?

27. የዮሐንስ ወንጌል ፀሀፊ «ዮሐንስ የተባለው የኢየሱስ ደቀመዝሙር ነው» ተብሎ ይገመታል: የዮሐንስ ወንጌል 21:24 ላይ «... ስለዚህ ነገሮች ሁሉ የመሰከረና እነዚህን ነገሮች የጻፈ ይህ ደቀመዝሙር ነው:: _የእርሱም ምስክርነት እውነት እንደሆነ እናውቃለን::_» ይላል:: ይህ የማን ንግግር ነው? «እናውቃለን»» የሚለውን እያለ ያለው ማነው? ዮሐንስ ስለራሱ ነው እንዲህ የሚለው? ወይስ ሌላ የዮሐንስ ደቀማዝሙር ነው ይህን እየጻፈ ያለው?

28. ዘዳግም 31:24-29 ‹‹ሙሴ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የዚህን ቃል በመጽሐፍ ጽፎ እንዳበቃ፣ የእግዚአብሔርን የኪዳን ታቦት የሚሸከሙ ሌዋውያንን እንዲህ ሲል አዘዛቸው፤...የቱን ያህል ዐመፀኞችና አንገተ ደንዳኖች እንደሆናችሁ ዐውቃለሁና። እኔ በሕይወት ከእናንተ ጋር እያለሁ እንደዚህ ካመጻችሁ፣ከሞትሁ በኃላማ የቱን ያህል ልታምፁ!... እኔ ከሞትሁ በኃላ ፈጽማችሁ እንደምትረክሱ፣ካዘዝኃችሁም መንገድ ዘወር እንደምትሉ ዐውቃለሁና።›› ይላል።ታዲያ ሙሴ ይህን ተናግሮ ሳለ እንዴት መጻሕፍቶቹን አይሁድ ጠብቀው አቆዩ ይባላል?

29. የኦርቶዶክስ መጻሕፍ ቅዱስ ስለ ሴት እንዲህ ይላል፡- «ከደረቅ ሴት ጋራ ከምትኖር ከምድር አውሬዎችና ከአንበሳዎች ጋር መኖር ይሻላል።» (መጽሐፈ ሲራክ 25:16)

- «በቤትህ አጠገብ ለውሃ መፍሰሻ አታብጅላት፤ ለሴት የልብህን ሚስጢር አታውጣላት።»(መጽሐፈ ሲራክ 25:24)
- «ምስጢርህን እንዳታወጣብህ ለሴት ልብህን አትስጣት» (መጽሐፈ ሲራክ 9:5)
- «ከሴት ቸርነት የወንድ ንፉግነት ይሻላል። ውሽማዋንና ባሏን የምታቃና ሴት አፍረት ናት።» (በመጽሐፈ ሲራክ 42:14)
- «ከልብስ ብል ይገኛል፤ ኃጢያትም ሁሉ ከሴቶች ይገኛል» (መጽሐፈ ሲራክ 42:13-14)
- «ጥንቱንም ኃጢአት ከሴት ተገኘች፤ ስለ እርሷም ሁላችንም እንሞታለን።» (መጽሐፈ ሲራክ 25:23)

እውን ይህ የአምላክ ቃል ነውን? መጽሐፍ ቅዱስ የሚስተምረው አምላክ ሴቶችን እንዲህ ይጠላልን? ወይስ ይህ የሰው ቃል ነው?

## ማጠቃለያ

በመጽሐፍ ቅዱስ በየጊዜው በሰው እየተጨመረና እየሰፋ መሄድ የተማረሩት ኢትዮጵያዊው ዓለማየሁ ሞገስ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡-

‹‹ዛሬ ዓለም ሁሉ በቀድሞ ዘመን ባለመግባባት የተነጣጠሉ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በሃይማኖት ካልሆነ በሥርዓት የተለያዩት ሁሉ ለመገናኘት በሚጥሩበት ጊዜ በሁለት ባሕርይ ምክንያት ያልነበረ እያወራችሁ ልዩነትን በልበ ንጹሓን የምትተክሉ፣ ሰማንያ አሐዱ መጻሕፍትን ገድላገድሉን ሁሉ ጨምራችሁ ከ 83፡89 ያገባችሁ፣ ቃለ እግዚአብሔርን ከእናንተ ሐሳብ ጋራ ካልተስማማ ስትደልዙና ስትሰርዙ የማታፍሩ ሰዎች ምናችሁ ክርስቲያን ናችሁ ተብሎ ይመሰከርላችኋል?››[42]

እንዲሁም በዚሁ መጽሐፋቸው የሚከተለውን ብለዋል፡-

‹‹ከቀድሞ ጀምሮ በፍትሐ ነገሥቱ የታዘዘው የ81 መጻሕፍት ቁጥር ይህ ሲሆን አሁን ግን በግዕዝ የተጻፉ አዋልድና ሊቃውንት ለምን ይቀራሉ ብለው ነው መሰለኝ በ1980 በሲኖዶሱ ፈቃድ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር አሳታሚነት የታተመው መጽሐፍ ቅዱስ 93 ደርሷል። በዚሁ እትም ላይም ሴላም አሻሽለን እንጨምራለን ብለው ቃል ስለገቡ፣ እነሰይፈ መለኮት፣ እነሠኔ ጎልጎታ፣ እነ አጋኖርን፣ እነ ዉዳሴ አምላክ ወዘተ... የመሳሰሉትም ቢሆን እንደሚጨመሩ ባለሙሉ ተስፋ ነን። መጽሐፈ ባልቴትስ ቢሆን ከልፉፈ ጽድቅ ጋራ በገዛ ሀገሩ ቢጨመር ምን አለበት?››[43]

ዛሬ ‹መጽሐፍ ቅዱስ› በሚል የሚታወቀው የክርስትና መጽሐፍ ኦሪጂናሉ ስለሌለ በዘርፈ ብዙ ችግሮች እንደተሞላ ይገኛል። ‹ይህ የመጽሐፉ ክፍል

---

[42] ሁሉም ሁሉን ይወቅ፣ከ(ቀደስ) ዓለማየሁ ሞገስ ደረሰ፣1987፣ በሌ ማተሚያ ድርጅት፣ገጽ 240

[43] ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ፣214

አይደለም፡፡›፣‹እነዚህ ጥቅሶች ድሮ አልነበሩም›፣ ወዘተ ውዝግቦች ለተራው አማኝ ባይነገሩም በሊቃውንት መካከል አነታራኪ እንደሆኑ ቀጥለዋል፡፡ ይህ በብሉይ ኪዳን ብቻ ሳይሆን በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት መካከልም ይገኛል፡፡ ‹እንዲህ አይልም፣ጠፍቷል፣የወንጌሉ ክፍል አይደለም›› እና ወዘተ ከተራው አማኝ የተደበቁ የውዝግብ ምንጮች ሆነዋል፡፡ ለአብነት ከኢትዮጵያውያን ክርስቲያን ጸሐፍት አንዱ ተስፋዬ ሮበሌ ‹የማርቆስ ወንጌል› ተብሎ ከሚታወቀው መጽሐፍ የተወሰነው የወንጌሉ ክፍል እንዳልሆነ እንዲህ ጽፈዋል፡-

‹‹በርካታ ሊቃውንት የማርቆስ ወንጌል የመጨረሻዎቹ ዐሥራ ሁለት ቁጥሮች (ማርቆስ 16፡9-20) የማርቆስ ወንጌል ክፍል አይደሉም የሚል አቋም አላቸው፡፡... <u>ስመጥር የቤተክርስቲያን አበው፣ የማርቆስ ወንጌል የመጨረሻ ክፍል እንደጠፋ እንዲሁም በማርቆስ 16፡9-20 ያለው ክፍል የማርቆስ ወንጌል አካል እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡››</u>[44]

እኒሁ ጸሐፊ በዮሐንስ ወንጌል ስለተነሳው ክርክር እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹መገንዘብ ያለብን መሠረታዊው ቁም ነገር፣ በዚህ መልክ አከራካሪነት ያለው የሐዲስ ኪዳን ምንባብ ዮሐንስ 7፡53-8፡11 ብቻ ነው፡፡››[45]

እስካሁን ያየናቸው የሚያስረዱት ‹መጽሐፍ ቅዱስ› በርካታ ችግሮች እንዳሉበት ነው፡፡ እንደ ቁርአን አስተምህሮት ዛሬ ያለው ‹መጽሐፍ ቅዱስ› ሙሉ ለሙሉ የአምላክ ቃል አይደለም፡፡ የሰዎች፣ የታሪክ ጸሐፊዎች፣

---

[44] ተስፋዬ ሮበሌ፣ዉሃውና ስሙ፣ ገጽ 21
[45] ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ፣ገጽ 23

የነቢያት፣ተናጋሪዎቹ ያልታወቁ ንግግሮችና ሌሎችም የማይመስሉ ንግግሮች አሉበት።ግን አብዛኛው ሰው ይህንን ሁሉ አያውቅም። ይህን ሁሉ መጣረስና ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ይዞ ‹ሙሉ ለሙሉ የአምላክ ቃል ነው› ማለት ግልጽ ስህተት ነው። በሰው እጅ ተጽፈው የአምላክ እንደሆኑ ማመን ከባድ ቅጥፈት አይሆንምን? ሰዎች እየጻፉት ‹ከአምላክ የተወረደ ቃል ነው› የሚባሉ መጽሐፍት እንደሚገኙ ቁርአን ይናገራል፡፡ቁርአን፡-‹ከነሱም (ንባቡን እንጂ) መጽሐፉን የማያውቁ መሃይማን አሉ፤ግን ከንቱ ምኞቶችን (ይመኛሉ)። እነርሱም የሚጠራጠሩ እንጂ ሌላ አይደሉም።ለነዚያም መጽሐፉን በእጆቻቸው ለሚጽፉና ከዚያም በርሱ ጥቂትን ዋጋ ሊገዙበት ይህ ከአላህ ዘንድ ነው ለሚሉ ውዮላቸው! ለነርሱም ከዚያ እጆቻቸው ከጻፉት ወዮላቸው! ለነሱም ከዚያ ከሚያፈሩት (ኃጢአት) ወዮላቸው።›› ይላል።*(ቁርአን ሱረቱል በቀራህ፣ 2:78-79)*

ከመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት መካከል ደግሞ ከግማሽ በላዮቹ ማን እንደጻፋቸው፣የት እንደ ተጻፉና መች እንደ ተጻፉ በውል አይታወቁም። ግምትና መላምት ብቻ ነው ያለው። በአጭሩ ስለመጻሕፍቶቹ ስምምነት የለም።

ታዲያ እንዲህ ያለው መጽሐፍ እንዴት ‹የአምላክ ቃል ነው›፤ ‹እኛ ክርስቲያኖች የአምላክ ቃል ስላለን ዐዋቂዎች ነን›፤ ‹ክርስቲያን ያልሆነ አይጸድቅም› ፣ ‹የእግዚአብሔር መጽሐፍና ሕግ አለን› ወዘተ ይባላል?

ትንቢተ ኤርሚያስ እንዲህ ይጠይቃል፡- <u>*‹‹የጻሐፊዎቻችሁ ሐሰተኛ ብዕር ሐሰት እያስተናገደ እንዴት ‹ዐዋቂዎች ነን፣ የእግዚአብሔር ሕግ አለን› ትላላችሁ?›› (ኤርሚያስ 8:8)*</u>

## ማስተንተን ይበጃል!

በጭፍን የራሳችን ወገን ስለሆኑ ብቻ የምናምናቸውና የምንቀበላቸው ከሆነ መጨረሻው ላያምር ይችላል።ሙስሊሞችና ክርስትያኖች ያላቸውን ልዩነት በሰከነ ሁኔታ እውነትን ከመፈለግ አንጻር ብቻ ቢወያዩ፣ ቢነጋገሩና ማስረጃቸውን ቢለዋወጡ መልካም ነው።አንዱ ስለሌላኛው ከተቃራኒ ወገኖች የሚጻፉትን ሳይሆን ከራሱ ከእምነቱ መሪዎች የሚፃፈውን ቢያገናዝብ እሰየው የሚያስብል ነበር።

እጅግ የሚያሳዝነው ግን ክርስቲያኖች ስለ ኢስላም ያላቸው ግንዛቤ ሙሉ ለሙሉ ከኢስላም መዛግብት አልያም ሊቃውንት የተገኘ አለመሆኑ ነው። ክርስቲያን ጸሐፍት ከጻፏቸውና ከነርሱ በሰሙት ላይ ተንተርሰው አቋም ይዘዋል።አዕምሮ እያለን ማመዛዘንና ማስተዋል ስንችል የራሳችንን ወገን ብቻ እያዳመጥን ሌሎችን ቸል እንላለን። አስተዉሎታችንን እንዳንጠቀምና የቤት አምልኮዎቻችንን እምነት ለመረዳት እንዳንሞክር በመምህራን ተነግሮናል።እንድናምን የተጠየቅነውን ነገር ለመረዳት ከአምላክ የተሰጠንን የአስተውሎት ኃይል እንድንጠቀምም አልተፈቀደልንም። ብንሞክር እንኳ ወደ ‹ክህደት› ልናመራ እንደምንችል ስለተነገረን ያለአስተውሎት ፣ ማስተንተንና ጥያቄ ‹አሜን› ብለን መቀበልን መርጠናል።

በርካታ ተቃራኒ አስተምህሮት ያላቸው አማኞች በእለተ ትንሳኤ ከአምላካቸው ፊት ይቀርባሉ። በዚያ ወቅት እውነትን በትኩረት አንሰማም የሚሉት ወይ ከሳራቸው! በጭፍን የተከተሉትና ትክክለኛውን ጎዳና የሳቱት ገሀነመ እሳት መጨረሻቸው ይሆናል። ያኔ ይቆጫሉ፣አዕምሯቸውን ተጠቅመው የሚነገራቸውን ባለመመርመራቸው ጥልቅ ሀዘን ይሰማቸዋል። የዛሬውን ጥፋታቸውን ይረዱታል። ቁርአን እንደሚነግረን ፡- ‹‹ይላሉም፡- ‹(የሚነገረንን እውነት ትኩረት ሰጥተን) የምንሰማ፣በአዕምሯችን የምንጠቀም

(የምናስብ) ቢሆን ኖሮ ከእሳት ሰዎች ባልሆንን ነበር።››(ቁርአን ሱረቱል ሙልክ 67፡10) ይላሉ።

ሰሚ ጆሮ፣ አስተዋይ አዕምሮ ያለው ሰው ራሱን ለእንዲህ ዓይነቱ ውድቀት አያዘጋጅም፤ፈጽሞ ጭፍን ተከታይ አይሆንም፤ የማያውቀውን ሊከተል አይደፍርም። የሰው ልጅ ከእንስሳ የሚለየው ማሰብና መምረጥ፣ሕይወቱንም በመረጠውና ባመነበት ጎዳና ማስኬድ፣መረጃዎችን መዝኖና ፈትሾ፣ አይቶና አስተንትኖ ያሳመነውን መቀበል በመቻሉ ነው። ይህን ባህሪውን ካጣ ወደ እንስሳት ደረጃ ማሽቆልቆል ብቻ ሳይሆን ከዚያም የባሰ ይሆናል። ምክንያቱም እንስሳት በተፈጥሮአቸው የተለገሳቸውን ውስን ችሎታ ተጠቅመው ሕይወታቸውን አላህ በፈለገላቸው መልኩ ይመራሉ።ስለሆነም ማስተዋል ግድ ይላል።ከውድቀት ለመታደግ ጎዳናችን ማስተዋል የተሞላበት ሊሆን ይገባል።መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ *‹‹የማስተዋልን መንገድ የሚስት ሰው፣በሙታን ጉባኤ ያርፋል።››(ምሳሌ 25፡16)* እንዲሁም ‹‹ማስተዋልን ገንዘቡ ላደረጋት የሕይወት ምንጭ ናት፣ ቂልነት ግን በተላሎች ላይ ቅጣት *ታመጣባቸዋለች*።››(ምሳሌ 16፡22)

የነቢያት መልዕክት አንድ ነበር፤ ግና ከነርሱ በኋላ ህዝቦች ተከፋፈሉ። ለፈጣሪ ሙሉ ለሙሉ መታዘዝ ቀረ፤ በአንዱ ጎዳና ምትክ ብዙ ሃይማኖቶች ተፈጠሩ።ሰው በሙሉ የተለያየ እምነት ተከታይ ሆነ።የራሱን እንጅ ‹‹ያኛው ትክክል ይሆን?›› ሳይል፣ለመመርመር ሳይፈቅድና የሕሊና መስኮቶቹን ሁሉ ዘግቶ በያዘው እምነት ደስተኛ ሆኖ ይኖራል።እምነቶቹ ምንም ይሁኑ ምን ስለማይመረምሩና ስለማያስተነትኑ ተከታዮቹ በእምነታቸው ደስተኛ ሆነዋል።አምላካችን አላህ (ሱ.ወ) ይህንን እውነታ እንዲህ ይነግረናል፦ *‹ሁሉም ቡድኖች ከነርሱ ዘንድ ባለው(እምነት) ይደሰታሉ)››(ቁርአን አል-ሙእሚኑን 23፡53)*

ማስተዋልና ብስለት ከሌለ ተከታዮቹ በያዙት ‹ማስተዋል በጎደለው› እምነታቸው ደስተኞች ናቸው፡፡መጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ይላል ፡-‹‹*እናንተ ብስለት የሌላችሁ ማስተዋል የሌለበት መንገዳችሁን እስከ መቼ ትወዱታላችሁ?›› (ምሳሌ 1:22)*

አንዳንዱ ከንቱ ስሜቱን ተከታይ ሆኗል፡፡መረዳት የሚያስችል አዕምሮ እያለው ባለመጠቀሙ የሚነገረውን አይሰማም፡፡ አይረዳም፤አዕምሮ ሳለው እንስሳ ሆኗል፡፡አዕምሮን ተጠቅሞ አስተንትኖ ትክክለኛውን አምላክ አውቆ ትዕዛዛቱን መከተል ሲገባው እንዲሁ ከንቱ ስሜቱን ይከተላል፡፡ ቁርአን እንዲህ ይላል፡-‹‹ከንቱ ስሜቱን አምላኩ አድርጎ የያዘውን ሰው አየህን? አንተ የርሱ ጠባቂ ትሆናለህን? ወይስ ብዙዎቹ ይሰማሉ? ወይም (የሚነገራቸውን) ይረዳሉ ብለህ ታስባለህ? እነርሱ ልክ እንደ እንስሳ ሆነዋል! ከነርሱም በባሰ (ደረጃ) መንገድ የሳቱ ናቸው፡፡››(አል-ፉርቃን 25:43-44)

መጽሐፍ ቅዱስ በመዝሙር 32:9 ላይ እንዲህ ይላል፡-‹‹*ማስተዋል እንደሌላቸው፣ እንደ ፈረስና እንደ በቅሎ አትሁኑ፡፡››*

ይህ የሚያስገነዝበን በጭፍን መከተል(በተለይ በእምነት ጉዳይ) ምን ያህል የተወገዘ እንደሆነ ነው፡፡ጥሩ አስረጅ የሚሆን ሌላ በቁርአን ዉስጥ የተጠቀሰው ታሪክ የኢብራሂም (አብረሃም) ታሪክ ነው፡፡ ማህበረሰቡ ጣኦት አምላኪ በነበረበት ሁኔታ አብረሃም በአዕምሯቸው ይመራመሩ ነበር፡፡በምክንያታዊነት የአጋሪዎችን እምነት ከንቱነትም ይረዳሉ፡፡ቁርአን እንዲህ አስፍሮታል፡-

*«እንደዚሁም ኢብራሂምን (እንዲያውቅና ከአረጋጋጮችም ይሆን ዘንድ) የሰማያትንና የምድርን መለኮት አሳየነው፡፡ ሌሊቱም በርሱ ላይ ባጨለመ ጊዜ ኮከብን አየ፣ «ይህ ጌታዬ ነው» አለ፣ በጠለቀም ጊዜ፣«ጠላቂዎችን አልወድም» አለ፡፡ ጨረቃንም ወጪ ሆኖ ባየ ጊዜ፡- «ይህ ጌታዬ ነው» አለ፣*

*በገባም ጊዜ «ጌታዬ (ቅኑን መንገድ) ባይመራኝ በእርግጥ ከተሳሳቱት ህዝቦች እሆናለሁ» አለ:: ፀሐይንም ሙራዋን ዘርግታ ባየ ጊዜ:- «ይህ ጌታዬ ነው» አለ:: በገባችም ጊዜ «ወገኖቼ ሆይ! እኔ ከምታጋሩት ሁሉ ንጹህ ነኝ» አለ::» (ሱረቱል አንዓም 6:75-79)*

በሚያሳዝን መልኩ በሃይማኖት ጉዳይ ጭፍን ተከታይነት ተንሰራፍቷል። በዓለማዊ እውቀት አንቱ የተባሉ ዶክተሮች፣ ‹‹እርቆ አሳቢ ናቸው›› የሚባልላቸውና በተለያዩ የሞያ መስኮች የተሰማሩ ግለሰቦች፣ በየዘርፋቸው በርካታ ጥናት ያካሄዱ ፣ አዳዲስ ግኝቶች ያገኙ፣ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ምክንያታዊነትን ተላብሰው በሚመስጥ መልኩ ሀሳባቸውን የሚያቀርቡ ሁሉ ማን እንደፈጠራቸው፣እውነተኛው አምላካቸው ማን እንደሆነ፣ለምን እንደሚኖሩ፣አምላካቸው ከነርሱ ምን እንደሚፈልግ ለማወቅ ከልብ አይጥሩም። ያላቸውን ያን ጥልቅ የማስተንተን ችሎታ ተጠቅመው ሲያስቡ አይስተዋሉም። በጭፍኑ የሆነን ሃይማኖት ያለ ምክንያታዊነት ሲከተሉ ይታያሉ። የመገኘታችንን ሚስጢር፣ የመኖራችንን ዓላማና ትክክለኛውን እምነት ከማወቅና ያወቅነውን ደግሞ በመከተል ራሳችንን ከማዳን የሚበልጥ በዚህች ዓለም ምን ፀጋስ አለ?

ያለንን ማንኛውንም ተሰጥኦና የታደልነውን አዕምሮ ለዚህ ካላዋልን ሌላ ለምን ይውላል? ብዙ ሰዎች በሃይማኖት ጉዳይ ቸልተኛ በመሆናቸው እንጂ ትክክለኛዉን ጎዳና ለመፈተሽ የሚችል ብሩህ አዕምሮ፣ ጥሩ ተሰጥኦ፣ እምቅ ችሎታ ወይም ጥሩ አጋጣሚዎች ሳይገጥማቸው ቀርቶ አይደለም።ያላቸውን አዕምሮ ተጠቅመው ለማስተንተን ባለ መሞከራቸው ግን ከአምላክ እገዛ አያገኙም።ሁሌም እዚያው ናቸው። እዉነትን ለማወቅ ትጉና ጉጉ የሆነ ሰው ግን የእውነት መንገድን ያገኛል። በሮች ሁሌም የሚከፈቱት ለእንዲህ አይነቱ ሰው ነው። አስታውስ!

የአብዛኛው ሰው ችግር የእውቀት ማጣት አይደለም። ቸልተኝነት እንጂ! ስለሆነም የማያውቁትን ይከተላሉ።አምላክ ሰውን ሁሉ ከማሰብ ችሎታ ጋር ፈጥሯል።ስለ ሃይማኖት ማሰብና መመራመር ‹ዉስብስብ› እንደሆነ አድርገን በራሳችን አንቀልድ። ‹ዉስብስብ› እንደሆነ በመናገርም ምክንያት አንደርድር። መክብብ እንዲህ ብሏል፡-

*‹‹ይህን አንድ ነገር ብቻ አገኘሁ፡-እግዚብሔር ሰውን ቅን አድርጎ መስራቱን፣ ሰዎች ግን ውስብስብ ዘዴ ቀየሱ።›› (መክብብ 7:29)*

በጭፍን መከተል ሞኝነት ነው።አለመመርመርና አለማጥናት ደግሞ እብደት ነው።መክብብ እንዳለው፡-*‹‹ስለዚህ ጥበብንና የነገሮችን አሰራር ለመመርመርና ለማጥናት የከፋትን መጥፎነት፣የሞኝነትም እብደት ለማስተዋል አእምሮዬን መለስሁ።››(መክብብ 7:25)*

ጌታችን አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ሲል ጭፍን ተከታይነትን ኮንኗል፡-*«የማታውቀውን ነገር አትከተል።ጆሮ፣ዓይንና ልብና ሁሉም (በዕለተ ትንሳኤ በድርጊታቸው) ተጠያቂዎች ናቸውና።» (አል-ኢስራእ 17:36)*

ያለ ጥያቄና ያለ ማስተዋል በተገኘ ጭፍን ተከታይነት ላይ የተመረኮዘ እምነትን ኢስላም ፈጽሞ አይቀበልም። የሰውን ምሁራዊ (አእምሯዊ) ሕይወት አስመልክቶም የራሱ የሆነ ግንዛቤ አለው።ኢስላም በአላህ ማመንን ይጠይቃል። በአላህም እንድናምን ጥሪ የሚያደርጉ አንቀጾችን ቁርአን ውስጥ ይደጋግማል።ታዲያ የነዚህ አንቀጾች አስፈላጊነት በቤተ መጻሕፍት ወይም በአእምሮ ውስጥ ለማኖር ብቻ ሳይሆን አእምሮ እንዲነቃና እንዲያስብ ሞቅ ያለ ግብዣና አስቸኳይ ጥሪ በመመስረቱ ላይ ነው።በተመሳሳይ ሁኔታ የሰው ልጅ በበኩሉ ምንም ጥረት እንደማያደርግ ሰነፍ ወራሽ ዓይነት እንዲሆንም አይፈልግም።ቁርአን፣ከምሁራዊነት (ከአእምሮ) አኳያም አማኝ እንድንሆን በብርቱ ትጋትና በፍፁማዊ ጥረት አማካይነት የሰው ልጅ ምሁራዊ ሃብቱን

እንዲያበለጽግ ይፈልጋል። በቀላሉ የሚመጣ ነገር በቀላሉ የሚጠፋ ስለሆነ በቀላሉ ሊጠፋ በሚችል ቀላል እምነት ኢስላም አይስማማም።

## ታዲያ ክርስቶስ ማን ነው?

የመጨረሻው የአምላክ አላህ (ሱ.ወ) ቃል የሆነው ቁርአን ስለ ኢየሱስ (ዒሳ) በሚገባ ተናግሯል። ቁርአን አምላካችን አላህ (ጥራትና ልዕልና ይገባውና) ‹ልጅ ወለደ››፣ ‹‹ልጅ ያዘ››፣ ‹‹ልጅ አለው›› እና ‹‹ኢየሱስ የአምላክ ልጅ ነው›› ወዘተ የሚሉ እምነቶችን ክፉኛ ኮንኗል። እንዲህም ይላል፦ ‹‹አላህም ልጅ አለው አሉ። (ከሚሉት) ጥራት ተገባው። አይደለም፤ በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የርሱ ነው። ሁሉም ለርሱ ታዛዦች ናቸው። ሰማያትና ምድርን ያለብጤ ፈጣሪ ነው። ነገርንም (ማስገኘት) በሻ ጊዜ ለርሱ የሚለው ኹን ነው፤ ወዲያውም ይኾናል።›› (ቁርአን ሱረቱ አል-በቀራህ 2፡116-117)

በሌላም ምዕራፍ ላይ አላህ (ሱ.ወ) ልጅ ከመያዝ የተብቃቃ መሆኑን ይገልጻል። ክርስቲያኖች ለዚህ አባባላቸው አሳማኝ ማስረጃ እንዳላቸውም ይጠይቃቸዋል። እንዲህ ይላል፦ ‹‹አላህ ልጅን ያዘ (ወለደ) አሉ። (ከሚሉት) ጥራት ተገባው፤ እርሱ ተብቃቂ ነው፤ በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የርሱ ነው፤ እናንተ ዘንድ በዚህ (በምትሉት) ምንም አስረጂ የላችሁም፤ በአላህ ላይ የማይታውቁትን ትናገራላችሁን?›› (ሱረቱል ዩኑስ 10፡68)

አምላካችን ‹‹አላህ ልጅ ያዘ›› ማለት እጅግ የተሳሳተ እምነት ነው። ፍጥረተ ዓለሙ ሁሉ የርሱ የሆነው አምላክ እንደ ፍጡሩ ‹‹ልጅ ያዘ›› ‹‹ወለደ›› ወዘተ ብሎ ማሰብ የፈጣሪን ሉአላዊነትና ፍፁምነት የሚፃረር ነገር ነው። በቀደምት ነቢያት አስተምሮት የሌለ፣ ለአምላክ የማይገባ ነገር ነው።

አላህ እንዲህ ይላል፡- ‹‹አልረሕማንም ልጅን ያዘ (ወለደ) አሉ፤ ከባድ መጥፎን ነገር በእርግጥ አመጣችሁ፤ ከርሱ (ከንግግራቸው) ሰማያት ሊቀደዱ፤ ምድርም ልትሰነጠቅ፤ጋራዎችም ተንደው ሊወድቁ ይቃረባሉ። ለአልረሕማን ልጅ አለው ስላሉ።ለአልረሕማን ልጅን መያዝ አይገባውም።በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ (በትንሣኤ ቀን) ለአል-ራሕማን ባሪያ ኾነው የሚመጡ እንጂ ሌላ አይደሉም።›› (ሱረቱል መርየም 19:88-93)

አይሁዶች ‹ዑዘይር የአላህ ልጅ ነው› አሉ። ክርስቲያኖች ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ‹አል-መሲህ› ‹‹የአላህ ልጅ ነው አሉ።››። ቁርአን ይህንን ጠንከር ባለ መልኩ እንዲህ ተችቶታል፡- ‹‹አይሁድ ዑዘይር የአላህ ልጅ ነው አሉ፤ ክርስቲያኖችም አልመሲሕ የአላህ ልጅ ነው አሉ፤ይህ በአፎቻቸው (የሚናገሩት) ቃላቸው ነው፤የነዚያን ከነሱ በፊት የካዱትን ሰዎች ቃል ያመሳስላሉ፤ አላህ ያጥፋቸው፤ (ከእውነት) እንዴት ይመለሳሉ? ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለው አንድን አምላክ ሊገዙ እንጂ ያልታዘዙ ሲኾኑ ሊቃውንቶቻቸውንና መነኩሳቶቻቸውን የመርየምን ልጅ አልመሲሕንም ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ። ከሚያጋሩት ሁሉ የጠራ ነው። የአላህን ብርሃን በአፎቻቸው ለማጥፋት ይፈልጋሉ፤ አላህም ከሓዲዎች ቢጠሉም እንኳን ብርሃኑን መሙላትን እንጂ ሌላን አይሻም። እርሱ ያ አጋሪዎቹ ቢጠሉም መልክተኛውን (ሙሐመድን) በቅን መንገድና በእውነተኛ ሃይማኖት ላይ ከሃይማኖት ሁሉ በላይ ይፋ ያደርገው ዘንድ የላከው ነው።›› (ቁርአን ሱረቱ አት-ተውባ 9:30-32)

እስካሁን ባሳለፍነው እንደተመለከትነው በኢየሱስ ላይ ክርስቲያኖች ያላቸው አቋም ይህ ብቻም አይደለም።‹‹አምላክ ነው፤ ከሥላሴዎቹ አንዱ ነው፤››

የሚለውም ይገኝበታል፡፡እናቱን ቅድስት ማርያምን ‹‹ወላዲት አምላክ /የአምላክ እናት›› በማለት ያመልካሉ፡፡ ይሰግዱላታል፡፡ ይማጸኗታል፡፡ ታማልደናለች ወዘተ በማለት ‹‹አማልክት›› አድርገው ይዘዋታል፡፡[46] ኢየሱስ ይህንን ፈጽሞ አላስተማረም፡፡ ‹‹አምልኩኝ፤ እናቴንም ተገዙ፤ የአምላክ ልጅ ነኝ!›› የሚለው የርሱ አስተምህሮት አይደለም፡፡ ጌታችን አላህ (ክርስቲያኖች ከሚሉት ጥራት ይገባውና) ኢየሱስ (ዒሳ) ይህን አለማለቱን እያወቀ ነገ በእለተ ትንሳኤ ቀን እርሱን ያመለኩ ሰዎች ላይ በራሱ በኢየሱስ እንደበት ያስመሰክርባቸዋል፡፡ ይህንንም ዛሬውኑ በመጨረሻው የአምላክ መጽሐፍ-በቁርአን ይነግረናል፡፡ ኢየሱስ በአምላኩ በአላህ በትንሳኤ እለት ሲጠየቅ በክርስቲያኖች ላይ ምን ብሎ እንደመሚሰክር ቁርአን እንዲህ ይነግረናል፡-

*‹‹አላህም፡- ‹የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! ሰዎችን፣ እኔንና እናቴን ከአላህ ውጪ አማልዕክት አድርጋችሁ ያዙኝ ብለሀልን?› በሚለው ጊዜ (የሚሆነውን አስታውሱ)፡፡(ዒሳም)፡- ‹ክብርና ልዕልና ላንተ ይሁን! ለኔ ልለው የማይገባኝን ነገር ማለቴ ፈፅሞ አግባብ አይደለም፡፡ይህን ተናግሬ ከሆነ ታውቀዋለህ፡፡ በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ፡፡ ግን አንተ ዘንድ ያለውን አላውቅም፡፡ አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም ዐዋቂ አንተ ብቻ ክሀና ይላል፡፡አንተ ሩቅ ሚስጥራትን አዋቂ ነህና› ይላል፡፡(ይላልም)፡- ‹የነገርኳቸው ያዘዝከኝን ብቻ ነው፡፡የኔም የናንተም ጌታ የሆነውን አላህን ብቻ አምልኩ(ነው ያልኳቸው)፡፡ከመካከላቸው በነበርኩበት ወቅት ስለነርሱ መስካሪ ነበርኩ፡፡እንዳረግ ካረከኝ በኋላ ግን የነሱ ጠባቂና ተቆጣጣሪ አንተው ነበርክ፡፡ አንተ በሁሉን ነገር ላይ መስካሪ ነህ፡፡› (ይላልም)፡-*

[46] ኦርቶዶክሶችና ካቶሊኮች ማርያምን ያመልካሉ፡፡ ምን ያህል ማርያምን እያመለኩ እንዳሉ በስፋት ለመገንዘብ ‹‹በዉኑ በማርያም ማመን ይገባሃልን?›› የሚለውን የመጋቢ ጥበብ ሰሎሞን መጽሐፍን ያንብቡ፡፡

ብትቀጣቸው ባሮችህ ናቸው፡፡ብትምራቸውም አንተ ኃያልና ጥበበኛ ነህ፡፡›› (ቁርአን ሱረቱል ማኢዳህ 5:116-118)

ይህ እየተነገራቸው ወደዚያው ውድቀት የሚያመሩ ካሉ በእርግጥ የሚገርም ነው፡፡ይህ በእለተ ትንሳኤ የሚሆን ክስተት ነው፡፡ በኢየሱስ (አል-መሲህ ዒሳ) ላይ የተሳሳተ እምነት የያዙትን ክፉኛ ኮንኖ ተግባራቸው ክህደት መሆኑን ግልጽ አድርጓል፡፡ ‹‹ኢየሱስ አምላክ ነው›› መባሉን እንዲህ ሲል በፅኑ ይቃወማል፦ ‹‹እነዚያ አላህ እርሱ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ነው ያሉ በእርግጥ ካዱ፤ የመርየምን ልጅ አልመሲሕን እናቱንም በምድር ያለንም ሁሉ ለማጥፋት ቢሽ ከአላህ ማዳን የሚችል ማነው? በላቸው፡፡ የሰማያትና የምድር በመካከላቸውም ንግሥና የአላህ ብቻ ነው፡፡ የሚሻውን ይፈጥራል፡፡ አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው፡፡›› (ሱረቱል ማኢዳህ 5:17) በዚሁ ምዕራፍ ላይ የኢየሱስ አስተምህሮት ምን እንደነበረ ይገልጻል፡፡ ኢያሱስ በአንዱ አምላክ (አላህ) ብቻ እንዲያምኑ ማስተማሩን ያስታውሳል፡፡ በአላህ ያጋራ ሰው መጨረሻው የገሃነም እሳት መሆኑንና ገነት በርሱ ላይ እርም መሆኗን እንዲህ ይገልጻል፡- ‹‹‹እነዚያ አላህ እርሱ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ነው ያሉ በእርግጥ ካዱ፤ አልመሲሕም አለ፤ የእስራኤል ልጆች ሆይ! ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ፡፡ እነሆ በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ፡፡ መኖሪያውም እሳት ናት፡፡ ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም፡፡ ›› (ቁርአን ሱረቱል ማኢዳህ 5:72) የክርስቲያኖች እምነት ይህ ብቻ አይደለም፡፡ከላይ ስናይ እንደነበረው ‹‹ሥላሴ›› የሚሉት እምነት አላቸው፡፡ አምላክ ሥላሴ ነው (በአካል ሦስት ናቸው/አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ/ በግብር አንድ ናቸው›› ይላሉ፡፡አላህ ከሦስቱ አማልክት አንዱ (የሦስት ሦስተኛ) ነው ይላሉ፡፡ቁርአን ይህንን የሥላሴን አስተምህሮ በጽኑ ይቃወማል፡፡ ይህንን እምነታቸውን ‹‹ክህደት››

ይለዋል። ከዚህ እምነታቸው ቢታቀቡ መልካም እንደሆነ ያስጠነቅቃል። የማርያም ልጅ ኢየሱስ እንደ ቀደምት ነቢያት አንዱ ነቢይ እንጂ ሌላ እንዳልሆነ በመግለጽ ክርስቲያኖችን ይገስጻል።ምህረትን ጠይቀው ከአድራጎታቸው እንዲጸጸቱ ይጋብዛል። እንደሚከተለው ይገልጸዋል፡-

<u>‹‹እነዚያ አላህ የሦስት ሦስተኛ ነው ያሉ በእርግጥ ካዱ፤ ከአምላክም አንድ አምላክ እንጂ ሌላ የለም። ከሚሉት ነገር ባይከለከሉ ከነሱ እነዚያ የካዱትን አሳማሚ ቅጣት በእርግጥ ይነካቸዋል። ወደ አላህ አይመለሱምና ምሕረትን አይለምኑትምን? አላህም መሓሪ አዛኝ ነው። የመርየም ልጅ አልመሲሕ ከበፊቱ መልክተኞች በእርግጥ ያለፉ የኾነ መልክተኛ እንጅ ሌላ አይደለም። እናቱም በጣም እውነተኛ ናት። (ሁለቱም) ምግብን የሚበሉ ነበሩ። አንቀጾችን ለነርሱ (ለከሓዲዎች) እንዴት እንደምናብራራ ተመልከት፤ ከዚያም (ከእውነት) እንዴት እንደሚመለሱ ተመልከት። ›› (ቁርአን ሱረቱል 5:73-75)</u>

ቁርአን ክርስቲያኖችን ‹‹የመጽሐፉ ባለቤቶች›› ሲል ይጠራቸዋል። እንዲህም ይመክራቸዋል፡-

‹‹እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ ፤ በአላህም ላይ እውነትን እንጅ አትናገሩ ፤ የመርየም ልጅ አል-መሲሕ ዒሳ የአላህ መልክተኛ፤ወደ መርየም የጣላት (የኹን) ቃሉም፤ ከርሱ የኾነ መንፈስም ብቻ ነው፤በአላህና በመልክተኞቹም እመኑ፤ (አማልክት) ሦስት ናቸው አትበሉም፤ተከልከሉ፤ለናንተ የተሻለ ይኾናልና፤ አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው። ለርሱ ልጅ ያለው ከመኾን የጠራ ነው። በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የርሱ ነው። መመኪያም በአላህ በቃ። አልመሲሕ ለአላህ ባሪያ ከመኾን ፈጽሞ አይጠየፍም፤ቀራቢዎች የኾኑት መላእክትም (አይጠየፉም)። እርሱን ከመገዛት የሚጠየፍና የሚኮራም ሰው (አላህ) ሁሉንም ወደ እርሱ በእርግጥ ይሰበስባቸዋል።እነዚያማ ያመኑት መልካሞችንም የሠሩት

ምንዳዎቻቸውን ይሞላላቸዋል። ከችሮታውም ይጨምርላቸዋል። እነዚያን የተጠየፉትንና የኮሩትንማ አሳማሚን ቅጣት ይቀጣቸዋል።ከአላህም ሌላ ለነሱ ዘመድንና ረዳትን አያገኙም።›› (ቁርአን ሱረቱ ኒሳእ 4:171-173)

አላህ እውነትን ተናገረ! ከአላህስ በላይ ማን እውነትን ይናገራል!?
የአላህ ውዳታና ሰላም የነቢያት መደምደሚያ በሆኑት በሙሐመድ ላይ ይሁን!
መንገዶች ሁሉ ወደ ኢስላም ያመራሉ!
ኢስላምን ሳይቀበሉ ሞት እንዳይቀድምዎት!!

## ተፈጸመ

አህመዲን ጀበል Hijri1430/2001 E.C.

## ዋቢ መጻሕፍት


1. ኪዳነ ማርያም ጌታሁን (መምህር)፤ ክርስቶስ በኢስላም (በቁርዓን) ክርስቶስን ከቁርዓን ጋር ምን አገናኘው? (ለሸህ አህመድ ዲዳት የተሰጠ መልስ)፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ ብርሃንና ሠላም ማተሚያ፤ ሁለተኛ ዕትም፤ 1999።
2. መስመር ሰለሞን፣ ይድረስ ለሙስሊም ወገኖቼ፤
3. በልሁ ደሳለኝ፤ እኔን ማን ትሉኛላችሁ? የክርስቶስ ማንነትና ሥራዎች፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ ሕይወት ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት፤ 1996።
4. የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣ ፲፱፻፸፪
5. ምህረቱ ጼ. ጉታ፤ መልስ ይኖረው ይሆን?፤ አዲስ አበባ ኢትየጵያ፤ ኤስ ኣይ ኤም ማተሚያ ቤት፤ 4ኛ ዕትም 1998
6. የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የጽ/ጠ/ጽ/ቤት ሐዋርያዊ ሥራ መምሪያ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ የሕያው አብ ቃል እና የዓለም መድኃኒት፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ ማስተር ማተሚያ ቤት፤ 1989።
7. ፓውል እንገዘ (ዶክተር)፤ ታሪካዊ ሥነ-መለኮት አመጣጡና ትንተናው፤ በምኒሊክ አሰፋውና በሰሎሞን ጥላሁን የተተረጎመ፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ አርቲስክ ማተሚያ ቤት፤ 1993።
8. መሠረት ስብሐት ለአብ፤ ሥላሴ በተዋህዶ፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፤ 1988።
9. ቲም ፌሎስ፤ የአዲስ ኪዳን የጥናት መምሪያና ማብራሪያ፤ ትምህርተ መለኮት ማስፋፊያ (ት.መ.ማ) መልክ የተዘጋጀ፤ 2ኛ መጽሐፍ፤ በግርማዊ የተተረጎመ፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ ኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል ፤2ኛ እትም፤ ኅዳር 1998 ዓ.ም

10. ሚሪል ሲ. ቴኒ፤ የአዲስ ኪዳን ቅኝት፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተክስቲያን የኮሚዮኒኬሽንና ሥነ ጽሑፍ መምሪያ፤ 1998 ዓ.ም

11. መጽሐፍ ቅዱስ፤ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤ ቀለል ባለ አማርኛ የተተረጎመ፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ 1980

12. መጽሐፍ ቅዱስ፤ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የታተመ፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ በመጀመሪያ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ፤ 1980

13. መጽሐፍ ቅዱስ፤ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤ ለኢትዮጵያ ሚሊኒየም የታተመ፤ የተተረጎመ፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ 2000

14. የቅዱስ ቁርአን ትርጉም፤ ነጃሺ ኢስላሚክ አሣታሚ ድርጅት፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ ነጃሺ ኢስላሚክ አሣታሚ ድርጅት፤ አንደኛ እትም፤ 1997

15. ሐሙዳህ ዐብዱል ዓጢ (ዶ/ር)፤ ፍኖተ እስላም፤ በሁዳ ፐሬስ ሊሚትድ የተተረጎመ፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ 1987

16. ጌርሃርድ ኔልስ፤ ለሙስሊሞች ጥያቄዎች የክርስቲያኖች መልሶች፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ የሕይወት በር።

17. ተስፋዬ ሮበሌ፤ ዉሃውና ስሙ፤ ቅጽ2፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ ራዕይ አሳታሚ፤1 999

18. ገዛኢ ዮሐንስ፤ ኤልሻዳይ /ያህዌህንሲ/ መጽሔት፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ ገዛኢ አሳታሚ፤ ግንቦት 1999።

19. ዓለማየሁ ሞገስ ደረሰ (ቀደስ)፤ ሁሉም ሁሉን ይወቅ፤ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፤ ቡሌ ማተሚያ ድርጅት፤ 1987።

20. Encyclopedia Britannica 2006\Ultimate Reference Suite DVD\ Electronic versions

21. Shaikul-Islam Ibn Taimiyah /1263-1328 A.D/. Answering those who altered The Religion of Jesus Christ. Al-Mansura, Egypt. English translation from Arabic. First Edition 2003.

22. PC Study Bible V3.1.The Bible, New International version. Seattle, USA. 2000.

23. __________. New King James Version. Seattle, USA. 2000.

24. __________. New American standard bible Updated edition. Seattle, USA. 2000.

25. __________. American Standard Version. Seattle, USA. 2000.

26. __________. New American Standard. Seattle, USA. 2000.

27. __________. Revised Standard Version. Seattle, USA. 2000.

28. __________. The Living Bible. Seattle, USA. 2000.

29. James and Deb Flint. One God or a Trinity? Hyderabad, India. Thomas Nelson Inc.

30. Dr. NAJI I. AL-ARFAJ. God in Christianity what is his nature? www.sultan.org

31. Robert A. Wagoner. THE GREAT DEBATE - Father, Son, Holy Spirit. Santa Ana, California. 1998

32. Harun Yahya. PROPHET JESUS (pbuh): A PROPHET, NOT A SON, OF GOD. www.harunyahya.com

**33.** **www.saaid.net.** عادل محمد نقض النصرانية موسوعة

**34.** Osama Abdella, **www.answering-christianity.com**